# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ትንታኔ

# ክፍል ስድስት (Volume - 6)

## የምርጫ ሥርዓትን በተመለከተ
## ኢዴፓ የሚከተለው አቋም

(ረቂቅ - ፩)

**ሰኔ 1995 ዓ.ም**

## <u>ብርቱ ማሳሰቢያ፣</u>

ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው በሰኔ ወር 1995 ዓ.ም ነው። ፖለቲካ በባህሪው የተለዋዋጭ ሂደቶች (Political Dynamism) ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ከተዘጋጀ ወዲህ ባሉት ጊዜአት በሀገሪቱ በርካታ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንደ ፖለቲካ ኃይል፤ ኢዴፓም የዚሁ ዳይናሚዝም ውጤት ነው። ስለሆነም፣ ፓርቲው ይህንን ሰነድ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመጨረሻውን Version እስከሚያወጣ ድረስ፤ ይህንን ሰነድ የሚያነቡ ሁሉ የተጻፈበትን ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና ስነልቡና ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

**(የኢዴፓ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ)**

# ክፍል - 6

# የምርጫ ስርዓትን በተመለከተ ኢዴፓ የሚከተለው አቋም

## 1. የዴሞክራሲ ሥርዓትና ምርጫ

### 1.1 መግቢያ

*በማንኛውም የፖለቲካ ሥርዓት ቁልፍ የሆነው ጥያቄ የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ ነው:: እያንዳንዱ መንግሥት ሥልጣኑን በሥራ ላይ በሚያውልበት ዘይቤና ሕዝቡ ደግሞ የመንግሥትን ፖሊሲ በመምራት በሚጫወተው ሚና አንፃር አንደኛው ዓይነት መንግሥት ከሌላው ዓይነት መንግሥት እንደሚለይ የታወቀ ነው::*

*በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕግ ሲሆን ይኸውም በዜጎች ፈቃድና ስምምነት ላይ በተመሠረተ ምርጫ የሚገኝ ነው:: በዚህ ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት መሪዎችና መንግሥትን የመሠረተው ሕዝብ የየራሣቸው መብትና ግዴታ አላቸው:: በሕዝብ ምርጫ ውክልና ያገኙ መሪዎችና ፓርቲዎች በጊዜያዊነት የያዙት ሥልጣን አላቸው:: ሌሎች ይህ ጊዜያዊ የሥልጣን ውክልና ያልተሰጣቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ሥልጣን ላይ ያለውን ፓርቲና መሪዎች ለመቆጣጠር የሚያስችል መብት፣ ድርጅት፣ እውቀት፣ የግል ንብረትና የመሳሰለው ሪሶርስ አላቸው:: መንግሥት ኢኮኖሚውን የመቆጣጠር ሳይሆን የመምራት ኃላፊነት ሲወስድ ዜጎች ደግሞ በሚመሠርቷቸው የንግድ፣ የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች፣ የገበያ ሥርዓት በሚፈቅደው መሠረት እየተወዳደሩ የመሥራት መብት አላቸው:: በዚህ አኳኋን የሚመሠረት ፖለቲካዊ ሥልጣን ጥቅም ላይ ሲውል ሞራላዊ ባልሆነ የዘፈቀደ አሠራር ሳይሆን በዴሞክራሲያዊ የጨዋታ (የአሠራር) ሕግጋት ላይ በመመሥረት ነው::*

*የዴሞክራሲ ሥርዓት የፖለቲካ ጨዋታ ከሚመራባቸው መርሆዎች መካከል ነፃና ግልጽ ምርጫ ማካሄድ፣ ለብዙሃኑ ውሣኔ መገዛትና የአናሳዎችን መብት ማክበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: በዴሞክራሲ ሥርዓት የመንግሥት ሥልጣን ግልፅነትና ተጠያቂነትን አጣምሮ የያዘ ነው:: በዚህ ሥርዓት ውስጥ ጥያቄ የማይቀርብበት የመንግሥት ሥልጣንና በመታዘዝ ላይ ብቻ የተገደበ የዜጎች መብት እንዲኖር አይፈቀድም:: መንግሥት የያዘውን ሥልጣን ከመጠን በላይ ሲጠቀምበት ዜጎች የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው:: የመሠረቱትን መንግሥት ጉድለቶች የመቃወም ብቻ ሳይሆን ጉድለቶችን ለማጥፋት የሚያስችል እርምጃ የመውሰድ ግዴታም አለባቸው:: በድምፃቸው የመሰረቱትን የመንግሥት ሥልጣን በድምፃቸው ሊሽሩትና በሌላ ሊተኩት ይችላሉ::*

*በተቃራኒው ፈላጭ ቆራጭ መንግሥታት ሥልጣናቸው የሚመነጨው ርዕዮተ-ዓለማዊና ግላዊ ከሆነ መሠረት ነው:: ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ሥርዓት ሥልጣን ላይ የሚወጡ መሪዎች የመግዛት መብት የሚመሰረተው ለመግዛት የሚያበቃ ርዕዮተዓለማዊ ምክንያት እንዳላቸው በማመን ነው:: ዜጎች ቢመርጧቸውና ባይመርጧቸው ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነገር አይደለም:: ዋናው ነገር ለመግዛት የሚያበቃ ርዕዮተዓለማዊና ግላዊ ምክንያት እንዳላቸው ማመናቸው ነው:: በዚህ ዓይነት መንገድ ሥልጣን በሚመሠረትበት ጊዜ አስፈላጊው ነገር ኃይል እንጂ ሕጋዊነት አይደለም:: በአንድ ገዥ ፓርቲ እጅ ውስጥ የተከማቸ ኃይል ይመሰረታል:: ይኸ ኃይል ደግሞ የማይጠየቅ፣ የማይሻርና ዘለዓለማዊ የሆነ የመንግሥት ሥልጣንና የፓርቲ አመራር እንዲሰፍን ይጥራል:: የተከማቸና በኃይል ላይ የተመሰረተውን ሥልጣን የሚቃወሙና የተለየ አመለካከት ያላቸውን ዜጎችና የፖለቲካ ፓርቲዎች አይቀበልም:: ወይንም ለእነዚህ የተለየ አመለካከት ላላቸው ዜጎችና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሊኖር የሚገባውን ትዕግሥትና ሆደ-ሠፊነት*

አያሳይም። ትምህርትን፣ መገናኛ ብዙሃንን፣ ኪነ-ጥበብና ሥነ-ጽሑፍን፣ ፖሊስና ደህንነትን ሙሉ በሙሉ በተፅዕኖው ሥር በማስገባት ወጥ የሆነ ርዕዮተ-ዓለም ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። ሹማምንቱ በሕግ የማይዳኝ ከፍተኛ ኃይል ስለጨበጡ ይህንኑ ሕግ የማይገዛው ኃይላቸውን የሞራል ሕግ ከሚፈቅደው ውጪ በዘፈቀደ ይጠቀሙበታል። ዋነኛው ግባቸው በእጅ ያስገቡትን ሥልጣን ላለማጣት በኃይል መጠበቅ ስለሆነ ለዚህ የሚረዳቸውን ማንኛውንም ዓይነት የጭካኔ ተግባር ሁሉ ካለማመንታት በዜጎችና በተቃዋሚች ላይ ይፈጽማሉ። በዚህ መንገድ በሚፈጠር አስጨናቂና ዋስትና የሌለው ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች ሥልጣን በኃይል ለያዘው መንግሥት ታዛዥ እንዲሆኑ ይገደዳሉ። ዜጎች የፈለጉትን ሰው መርጠው ለመንግሥት ሥልጣን ማብቃት ይቅርና የማይፈልጉትን ለመቃወም እንኳ መብት የላቸውም።

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በዜጎች ፈቃድና ስምምነት በተመረጠ የመንግሥት ሥልጣንና በፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ውስጥ በርዕዮተ-ዓለማዊና ግላዊ ምክንያት በተያዘ የመንግሥት አገዛዝ መካል ያለው መሠረታዊ ልዩነት በአንድ በኩል የዜጎችን ንቁና የተሟላ ተሳትፎ በማረጋገጥና በሌላ በኩል ደግሞ ተቃውሞ በማይቀርብበት መንገድ የሚገለጽ ፍጹም የሆነ ታዛዥነትን በማስፈን መካከል ያለ ልዩነት ነው። ከዚህ አጠቃላይ መሠረተ ሀሣብ በመነሳት በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ያለውን የምርጫ እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል ለመረዳት የሚያግዙ መሠረታዊ ጉዳዮች ቀጥሎ በሚቀርቡት ነጥቦች ይዳሰሳሉ።

## 1.2. ምርጫ ምንድን ነው?

ምርጫን በሚመለከት የሚሰጠው ትርጉም ብዙ ዓይነት በመሆኑ አንድ ወጥ ትርጉም ማስቀመጥ ባይቻልም ከሞላ ጎደል ተቀባይነት ያገኘውን ብቻ በመውሰድ ስለምርጫ ምንነት መጠነኛ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል። በዚህም መሠረት ምርጫ ማለት ለተወሰነ ሥራና ኃላፊነት ከሚወዳደሩ ግለሰቦች ቡድኖችና ተቋሞች መካከል እንደ አስፈላጊነቱ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሚሆኑትን አስቀድሞ በተዘጋጀ የምርጫ ሕግና ሥርዓት ላይ ተመሥርቶ መምረጥ ማለት ነው። እዚህ ላይ ትኩረት መስጠት የተፈለገው ለፖለቲካ ሥልጣን የሚወከሉ ግለሰቦችንና ቡደኖችን አስመልክቶ የሚካሄደውን ምርጫና የምርጫ ሥርዓት ነው።

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት የመሠረቱ አገሮች የፖለቲካ መሪዎችንና የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ኃላፊነት ቦታ ላይ ለማስቀመጥ ሙሉ በሙሉ የተቀበሉትና በተግባር የሚያውሉት አሠራር ቢኖር ምርጫ ነው። እዚህ ላይ መጠንቀቅ የሚያስፈልገው በምርጫና በዴሞክራሲ መካከል ሁልጊዜ የግድ አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት እንዳለ አድርጎ መረዳት የማይገባ መሆኑን ነው። በሚገዙት አገርና ሕዝብ ላይ አምባገነን፣ ዘረኛና ጨካኝ አገዛዝ እንዳሰፈኑ አለም የሚያውቃቸው የፖለቲካ መሪዎችና ፓርቲዎች ሳይቀሩ መጥፎ ስማቸውንና ተግባራቸውን ለመደበቅ ያግዛል በሚል በተለያዩ ጊዜያት የተጭበረበሩ ምርጫዎችን ያካሂዳሉ። ንጉሦች የሕዝብ ድጋፍ እንዳላቸው ለማሳየት ምርጫ ያደርጋሉ። የአንድ ፓርቲ ሥርዓት የመሠረቱ መንግሥታት ምርጫ ያካሂዳሉ። መራጩ አንድ ብቸኛ ንጉስ ወይም አንድ ብቸኛ ፓርቲ እንዲመርጥ በሚገደድበት ሁኔታ የሚከናወን ምርጫ አላማው በሕዝባዊ ምርጫ የተደገፈ የመንግሥት ሥርዓት የተቋቋመ ከማስመሰል የሚያልፍ አይደለም።

በዴሞክራሲ አመለካከት ትክክለኛ ምርጫ ሊኖር የሚችለው የምርጫ እንቅስቃሴ በአንድ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም የተሰወነ ሕጋዊነት ለማግኘት በሚፈልግ ማንኛውም አካል የተናጠል ፍላጎት ላይ ብቻ ያልተመሠረተ ሲሆን ነው። ወይም በሌላ አገላለፅ በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ በተግባር ተፈትነው ተቀባይነት ባገኙት መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ ሲካሄድ ነው። ትክክለኛ ምርጫ ተካሄደ የሚባለው ምርጫው ቀጥተኛ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ነፃ፣ እኩል፣ ትክክለኛና ምስጢራዊ በሆነ መንገድ፣ በገለልተኛ የምርጫ አፈፃፀም ሕግና ተቋም ሲካሄድ ነው።

የፖለቲካ ሥልጣን ውክልና ለመስጠት የሚደረግ ምርጫ የዜጎችን መብትና ነፃነት ማረጋገጥ ከሚቻልባቸው ዴሞክራሲያዊ አሠራሮች አንዱና ዋነኛው በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው። ይሁን እንጂ ምርጫ ማካሄድ እጅግ የተወሳሰበና ከፍተኛ ድካም የሚጠይቅ ሥራ ነው። ምርጫ ለማካሄድ በቅድሚያ የመራጩን ሕዝብ ቁጥር፣ አሰፋፈር፣ የትምህርት ደረጃ፣ ባህል፣ የዕድሜም ሆነ የፆታ ጥንቅርና የመሳሰሉትን ማወቅ ይጠይቃል። በዚህ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የምርጫ ክልሎችን መወሰን፣ የምርጫ ክልል ካርታዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። መራጩን ሕዝብ መመዝገብ፣ ስለምርጫው ዓላማና ስለድምፅ አሰጣጡ ልዩ ልዩ ቴክኒኮች ማስተማርና

ማሠልጠን ይጠይቃል። በገለልተኝነትና በታማኝነት የሚሠሩ የምርጫና የዳኝነት ተቋሞችን በየደረጃው በማደራጀት፣ በአስፈፃሚነት የሚሠማራ የሰው ኃይል መመልመል፣ ማሰልጠንና ማሰማራት፣ ለምርጫው አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን በበቂ መጠንና በጥራት አዘጋጅቶ በወቅቱ ማሰራጨት፣ ለምርጫው ውጤታማነት የሚያግዙ የመገናኛ ብዙሃንን ለሥራ በሚስማማ መንገድ ማቀናጀትና ማሰለፍ፣ ገለልተኛ ታዛቢዎችን ማሰማራት ያስፈልጋል። ይኽ ሁሉ ሥራ ከፍተኛ ወጪ፣ እውቀትና ሠፊ ጊዜ የሚጠይቅ ሥራ ነው።

ከዚህ ሌላ ምርጫ በሕግ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መከናወን የሚገባው ሲሆን ወቅቱን ሳይጠብቁ ምርጫ ማካሄድ የሚያስፈልግበትም ሁኔታ ያጋጥማል። በአካባቢ፣ በክልልና በሀገር ደረጃ የሚቋቋሙ የውክልና ሥልጣን አካላት በሕግ የተደነገገውን ጊዜ ጠብቀው እንዲከናወኑ የሚደረግበት አሠራር መደበኛ ምርጫ የሚባለው ነው። ይሁን እንጂ በሕዝብ ቀጥተኛ ምርጫ የመንግሥት ሥልጣን ውክልና የተሰጠው የሀገር መሪ ወይም የምክር ቤት አባል በፈቃዱ ሥራን ቢለቅ፣ ቢሞት በሌላም ምክንያት መቀመጫውን ቢያዞር እርሱን በሌላ ሰው ለመተካት የሚከናወን ምርጫ ልዩ ወይም የማሟያ ምርጫ ሊያጋጥም ይችላል። ሕዝብ የመረጠውን ተወካይ እምነት በሚያጣበት ጊዜ እንደገና ተመራጩን የሚጠራበት ምርጫም አለ። በሕዝብ ምርጫ የተቋቋመ ፓርላማ ወይም ምክር ቤት የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት ሕግን በተከተለ አሠራር ቢበተን ወቅቱን ያልጠበቀ ምርጫ[1] ሊካሄድ ይችላል። የጠቅላላውን ሕዝብ ቀጥተኛ ውሣኔ የሚጠይቅ ከፍተኛ አገራዊ ጉዳይ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሕዝበ-ውሣኔ ማሰጠት ይኖራል። እነዚህና የመሣሰሉት የምርጫ እንቅስቃሴዎች ውድና አድካሚ ቢሆኑም በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የዜጎች ፖለቲካዊ ተሳትፎ መገለጫዎች በመሆናቸው ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣቸዋል።

በፖለቲካ ውስጥ ዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎ ከሚያደርጉባቸው መስመሮች መካከል በግለሰብ ደረጃ በምርጫ የሚያደርጉት ተሣትፎ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎችና በተለያዩ የፖለቲካ ግፊት ማድረጊያ አካላት ደግሞ በቡድን ደረጃ የሚያደርጉት ተሳትፎ ዋነኞቹ ናቸው። በብዙዎቹ የዴሞክራሲ ሥርዓቶች «ሁሉም የመንግሥት ሥልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ ነው» የሚለው መሠረታዊ መርህ ተግባራዊ የሚሆነው ዜጎች በምርጫ ወቅት በሚሰጡት ውሣኔ ነው። ሕዝቡ የሥልጣን ምንጭ፣ ሥልጣን የሚሠጥና ሥልጣን መልሶ የሚቀማ መሆኑን ተግባራዊ የሚያደርገው በምርጫ ወቅት በሚሰጠው ቀጥተኛ ውሳኔ ነው። ምርጫ የዜጎች ቀጥተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ መገለጫ ብቻ ሳይሆን የመሠረቱትን የውክልና ሥልጣን የሚቆጣጠሩበትም ዘዴ ነው። ፈቅደው ሥልጣን እንደሰጡ ሁሉ ፈቃዳቸው ባልሆነ ጊዜ ደግሞ የሰጡትን የውክልና ሥልጣን መልሰው ይወስዳሉ። አሊያም ከነአካቴው ለማይፈልጉት ግለሰብና ቡድን ሥልጣን ከመስጠት ይቆጠባሉ። ይኸንን የሚያደርጉት በምርጫ ወቅት በሚኖራቸው ተሳትፎ ነው። በዚህም ምክንያት ምርጫዎች የመንግሥት ባለሥልጣናትን በመምረጥና የመንግሥትን ፖሊሲ ይዞታ በመወሰን ቁልፍ በሆኑ ተግባሮች ዜጎች እንዲሳተፉ የሚያስችሉ መድረኮች ናቸው። ምርጫዎች የመንግሥት ሥልጣን የያዙ መሪዎች ለአጠቃላይ ሕዝቡ ተጠሪ የሚሆኑበትን ሂደት የሚፈጥሩ በመሆናቸው ሉዓላዊ ሥልጣን በመራጩ ሕዝብ እጅ ውስጥ እንዳለ የሚረጋገጥባቸው ናቸው። መንግሥታትና የመንግሥት መሪዎች በሚሰሩት ሥራ ለሕዝብ ተጠያቂ እንደመሆናቸው የሕዝቡን የምርጫ ድጋፍ በሚያጡበት ጊዜ በሌላ ድጋፍ በሚያገኝ ተመራጭ ይተካሉ። ስለዚህ ምርጫ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል መሠረታዊ ግንኙነት የሚዘረጋበት መስመር ነው።

የመንግሥት ሥልጣን የያዙ ሰዎች የሚያራምዱት ፖሊሲ ከአጠቃላዩ ሕዝብ ፍላጎት ጋር የሚስማማ መሆኑ የሚመዘነውም በምርጫ አማካይነት ነው። ሕዝቡ የፖለቲካ ሥልጣን ምንጭ እንደመሆኑ የመረጣቸው ሰዎች ሕግ የሚያወጡት፣ አገር የሚመሩትና የሚያስተዳድሩት በመራጩ ሕዝብ ስም ነው። ስለሆነም ምርጫ የዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚረጋገጥበትና ሉዓላዊ ሥልጣን የሚገለጽበት የውክልና ዴሞክራሲ መመሥረቻ መንገድ ነው።

ምርጫ ቀጥተኛ የሕዝብ ተሣትፎ ማረጋገጫ ብቻ ሳይሆን የውክልና ሥልጣን መመስረቻም በመሆኑ የተነሳ የተወሰኑ ሰዎች በዚህ ረገድ ቅራኔ ያለ ሊመስላቸው ይችላል። ከዚህም በላይ የውክልና ሥልጣን መፍጠር በጠቅላላው ሕዝብ ስም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ውሳኔ የሚሰጡበትን አሠራር ስለሚያስከትል የመራጩን ፍላጎት የመጠበቅ ጉድለት ሊያጋጥመው ይችላል የሚል ሥጋት ያላቸው ጥቂት አይደሉም። እንዳውም የውክልና ሥልጣን የተሰጣቸው ሕግ-አውጭዎች የምርጫ አካባቢያቸውን ስለሚወክሉ ውክልናቸው ክልላዊ ብቻ የመሆን

[1] ***ወቅቱን ያልጠበቀ ምርጫ*** = *pre-mature election*

*ድክመት አለበት የሚሉ መኖራቸው አይካድም፡፡ ዋናው ነገር የውክልና ሥልጣን በዜጎች ፈቃድ፣ ስምምነትና ነፃ ውሣኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡ አብዛኛው ሕዝብ ነፃ ውሣኔውን ያሳለፈበት የምርጫ ሥርዓት ተዘርግቶ እስከተፈፀመ ድረስ ውክልናው የሚያስከትለው ችግር የለም፡፡ ዞሮ ዞሮ በመራጬና በተወካዩ መካከል የጥቅምና የፍላጎት ግጭት ሲፈጠር መፍትሔው ሁልጊዜም በመራጩ ሕዝብ መዳፍ ሥር መገኘቱ የማይቀር ነው፡፡*

## *1.3 ፓርላማና የውክልና ሥርዓት*

*የምርጫ ቀዳሚ ዓላማ መንግሥት የሚባል የተደራጀ ተቋም ከመፍጠር ጎን ለጎን በሕዝብ ስም የመንግሥት ተከታታይ ሥራዎችን የሚያከናውን፣ በሕዝብ ቦታ ሆኖ ሕግና መመሪያዎችን የሚያፀድቅና ለሕዝብ ተጠያቂነት ያለው ፓርላማ መመሥረት ነው፡፡ ፓርላማ ሲባል ብዙውን ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚባለውን ተቋም የሚመለከት ሲሆን በዚህ ዓይነት የሚመሠረት የፖለቲካ ሥርዓት ደግሞ የውክልና ዴሞክራሲ የሚባለውን የዴሞክራሲ ዓይነት የሚያመለክት ነው፡፡ እዚህ ላይ ውክልና ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት እንዲቻል እያንዳንዱ የውክልና ሥርዓት ከዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ጋር ያለውን ግንኙነት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ውክልና የሚለው አስተሳሰብ ከሕዝባዊ የሥልጣን ቁጥጥር መርህ ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ የፖለቲካ ውክልና ያላቸው ሰዎች የመራጩ ሕዝብ ባለአደራ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ወይም የፖለቲካ ተወካዮች የሚሾሙት በሕዝብ ፈቃድ መሆኑን፣ ተጠሪነታቸው ለሕዝብ መሆኑንና የሚወገዱትም በሕዝብ ውሣኔ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡*

*በዚህም መሠረት የምርጫ ሥርዓቶች በአንድ በኩል የፖለቲካ ሥልጣን ውክልና የሚያገኙ ሰዎች ለመረጣቸው ሕዝብ ያላቸውን ተጠሪነት በማረጋገጥ ረገድ በሚያስገኙት ብቁ ውጤትና በሌላ በኩል መራጩ ሕዝብ የማይፈልጋቸውን ለማስወገድ እንዲችል ቀላልና ምቹ አማራጭ ከመሆናቸው አኳያ ሊመዘኑ ይገባል፡፡ ይኸንን መመዘኛ በበቂ ሁኔታ ሥራ ላይ ለማዋል የፖለቲካ ተወካዮች ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠሪ የሚሆኑት እንዴት ነው የሚለውን ጥያቄ በቅድሚያ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያዎቹ የዴሞራሲ ምስረታ ወቅቶች እንደታየው ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለምርጫ የሚቀርቡት በግለሰብ ደረጃ ራሳቸውን ችለው ነበር፡፡ የሚመረጡትም የተወሰነ አካባቢን ሕዝብ ጥቅም ለማራመድ ባላቸው ግለሰባዊ ችሎታ ብቻ እየተመዘኑ ነበር፡፡ ነገር ግን ከፓርቲ ሥርዓት መጠናከር ጋር በተያያዘ መንገድ ምርጫዎች በብሔራዊ ደረጃ የሚወዳደሩ ፓርቲዎች ባቀረቧቸው ፕሮግራሞችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል የተሻለውን መምረጥ የሚቻልባቸው ሥርዓቶች እየሆኑ መጡ፡፡ ዕጩዎች በግለሰብ ደረጃ ያላቸው ብቃትና ችሎታ ብቻ ሳይሆን በዕጩነት ያቀረባቸውንም ፓርቲ ብቃትና ምንነት መመዘን ተጀመረ፡፡ ይህ ሲባል ግን አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ካቀረበው ፓርቲ ማንነትና ምንነት ባሻገር የግለሰቡ ችሎታና ብቃት የሚታይበት ዕድል ጨርሶ ተዘግቷል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የፓርቲ ውክልና የያዘ ዕጩ ተወዳዳሪ ከመራጩ ሕዝብ ፊት የሚቀርበውና በመራጩ ሕዝብ የሚመዘነው በቅድሚያ ግለሰቡ ራሱ ነው፡፡ እንደውም መራጩ በፓርቲው ማንነት ላይ ተመሥርቶ አንድን ዕጩ በመምረጥ ፋንታ በግለሰቡ ብቃትና ማንነት ላይ ተመሥርቶ ፓርቲውን በምርጫ የሚደግፍበት ሁኔታ እንደሚያጋጥም የታወቀ ነው፡፡*

*እዚህ ላይ በግለሰብ ብቃትና ማንነት ላይ ብቻ ተመሥርቶ የነበረው የምርጫ ሥርዓት በፓርቲ ማንነትና ደረጃ ላይ ወደተመሰረተ ምርጫ መለወጡ የሕዝብ ተወካዮች ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠያቂ በመሆናቸውም ሆነ በመረጣቸው ሕዝብ ሊሻሩ በመቻላቸው ላይ ምን እንደምታ ያስከትላል የሚለውን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ በፓርቲ ማንነትና ብቃት ላይ የተመሠረተ ምርጫ በሀገር ደረጃ ለመራጩ ተጠያቂ የሚሆነው አንድ ግለሰብ ተመራጭ ብቻ ሳይሆን ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነ ተቋምም እንዲኖር ያስችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ተጠያቂነት ሲኖር በአገር ደረጃ የመራጩ ሕዝብ ድጋፍ ሊጨምርም ሆነ ሊቀንስ የሚችለው በፓርላማ ውስጥ የተሰጣቸውን ውክልና በትክክል ለመወጣት በሚያሳዩት ጥንካሬ መሆኑን የሚገነዘቡ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡ ሕዝብ የሰጣቸውን ድጋፍ እንዳይነፍጋቸው በፓርላማ የተወከሉ ፓርቲዎች በሚያካሂዱት የተቀነባበረ ተግባርና መራጩ ሕዝብ በፓርቲዎቹ ተግባራዊ ብቃት ላይ በሚኖረው ምዘና መካከል ግልጽና ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖር ያስችላል፡፡ በዚህ ዓይነት አሠራር የምርጫ ሥርዓቱ የሥልጣን ውክልና ያገኙ ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎችንም በኃላፊነት ዘመናቸው ለሠሩት መልካም ተግባር እንዲያበረታታቸው፣ ለፈፀሙት መጥፎ ተግባር ደግሞ እንዲገስፃቸውና እንዲቀጣቸው ለመራጩ ሕዝብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡*

የፖለቲካ ውክልና የመጀመሪያ ገጽታ ተወካዮች የመራጩ ሕዝብ ባለአደራ መሆናቸው ሲሆን ምርጫ ደግሞ እነዚህን ባለአደራዎች ለመመደብ፣ ለመጠየቅና ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው። ተወካዮች ምክር ቤት የሚባለው ተቋም መጠነ ሰፊ የሆነውን የአገሪቱን መራጭ የሚወክል መድረክ ነው። ይኸኛው አገላለፅ የፖለቲካ ውክልናን በሚመለከት ብዙ ጊዜ ወደሚነሳው መሠረታዊ ክርክር የሚወስድ ነው። በአንድ በኩል ሕዝቡ የራሱን ሥልጣን በውክልና አሳልፎ መስጠት አይገባውም ወይም የራሱን ሥልጣን ራሱ በቀጥታ መጠቀም ይኖርበታል የሚለውን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሕዝብ ቁጥር እድገትና ከአገሮች ስፋት ጋር በተያያዘ እያንዳንዱ ዜጋ በአካልና በቀጥታ እየተሳተፈ አገራዊ ውሣኔ ለማዘጋጀትና ለማሳለፍ እጅግ አስቸጋሪና በመብት አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን በሪሶርስ አጠቃቀም አባካኝ ስለሚሆን የጠቅላላውን ሕዝብ ባህሪ የሚያንፀባርቁ ተወካዮችን የያዘ የውክልና ተቋም መፍጠር ይሻላል የሚሉትን ክርክሮች ለረጅም ጊዜ ይዞ የቆየ ነው። አሁን በተደረሰበት የግንዛቤ ደረጃ የውክልና ሥልጣን የያዘ ተቋም መፍጠር ከሞላ ጎደል ተቀባይነት ያገኘ አሰራር ሆኗል። በዚህም መሠረት የምርጫው ሥርዓት መገምገም የሚገባው የውክልና ሥልጣን የሚረከበውን ፓርላማ የሕዝብን አጠቃላይ ባሕሪይ የሚያንፀባርቅ እንዲሆን በማስቻል ረገድ ምን ያክል ጠቃሚ ነው በሚል መሠረታዊ መመዘኛ ነው። የምርጫ ሥርዓት መመዘን ያለበት በዚህ ዓይነት መመዘኛ ከሆነ ለመሆኑ የውክልና ሥልጣን በሚይዝ ፓርላማ ውስጥ መንፀባረቅ አለበት የሚባለው አጠቃላይ ባሕሪይ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ማንሣት ተገቢ ነው። የውክልና ሥልጣን የሚሠጠው ፓርላማ በአብዛኛው ሦስት ዓይነት ባሕሪያትን ማንፀባረቅ ይኖርበታል።

በመጀመሪያ ፓርላማው እንዲያንፀባርቅ የሚጠበቅበት ባሕርይ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን መራጭ ሕዝብ ጂኦግራፊያዊ ሥርጭት ነው። ይህ አስተሳሰብ የሚያጠቃልለው መራጩ በአካባቢና በክልል የሚኖረው ውክልና አንድ ጠቃሚ ቁምነገር መሆኑን ነው። እናም የፓርላማውን ጥንቅር በተወሰኑ ማዕከላት ወይም ክልሎች ከማተኮር፤ ወይም የአካባቢና የክልል ልዩነቶችን ችላ ከማለት ሕዝቡ የሚኖርበትን አካባቢ ሙሉ በሙሉ በሚያቅፍ ደረጃ የሚያንፀባርቅ ውክልና እንዲኖረው አድርጎ መገንባት ያስፈልጋል።

ሁለተኛው መንፀባረቅ የሚገባው ባሕሪይ ደግሞ የመራጩ ሕዝብ አመለካከት ነው። ይኸ አመለካከት ታሳቢ የሚያደርገው ነጥብ መራጩ ሕዝብ የተለያዩ ፓርቲዎችን በመምረጥ ያለውን የአመለካከት ልዩነት እንደሚያንፀባርቀው ሁሉ ፓርላማውም በመራጩ ሕዝብ መካከል ያለውን የአመለካከት ሥርጭት የሚያንፀባርቅ ሆኖ መገንባት ይኖርበታል። ፓርላማው በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ አመለካከት ማንፀባረቅ አለበት የሚለው አስተሳሰብ የፓርላማ መድረክ ሰፊውን መራጭ ሕዝብ በሚገባ የሚወክል መለስተኛ አገር ነው ከሚለው ማዕከላዊ ነጥብ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። ይኸንን አባባል ግልጽ ለማድረግ ፓርላማው የሚያሳልፈው ሕጋዊ ውሣኔ ሁሉም ሕዝብ በጠቅላላ ተሰብስቦ ሊወስን ቢችል የሚወስነውን፤ ሕዝቡ ራሱ በቀጥታ እንዲመካከርና እንዲወያይ ቢደረግ መጨረሻ ላይ ሊደርስበት የሚችለውን መደምደሚያ ሊያንፀባርቅ የሚችል መሆን አለበት ማለት ነው። እንዲህ አይነቱን ፓርላማ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያስገኝ የሚችለው የምርጫ ሥርዓት «የተመጣጠኝ ውክልና[2]» ሥርዓት የሚባለው ነው። የዚህ ዓይነቱ የምርጫ ሥርዓት ዓላማ ለተለያዩ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድምፅ ብሔራዊ ሥርጭት በተቻለ መጠን ተቀራራቢ መሆኑን በፓርላማው ውስጥ መንፀባረቁን ማረጋገጥ ነው። ለአንድ የተለየ ፓርቲ ድምፅ መስጠት በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ልዩ ልዩ የፖለቲካ አስተያየቶች ለመጠቆም ከሚያስችሉት መንገዶች መካከል የተሻለው መንገድ እስከሆነ ድረስ ለፓርቲው የተሰጠ ድምፅ በፓርላማው ውስጥ ተቀራራቢ በሆነ የተመጣጣኝነት ደረጃ እንዲንፀባረቅ የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ ሀገሪቱ ያለውን የፖለቲካ አስተያየት ውክልና እንዲያገኝ የሚጠቅም ነው።

ሦስተኛው መንፀባረቅ የሚገባው ባሕሪይ የመራጩ ሕዝብ ማህበራዊ ጥንቅር ነው። ይህ አስተሳሰብ ፓርላማው የመራጩን ሕዝብ ፆታ፤ ጎሣ፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሃይማኖት፣ የኢኮኖሚ ይዞታ፣ ባህልና የመሳሰሉትን ገፅታዎች ማቀፍ አለበት የሚለውን መሠረታዊ ነጥብ የሚመለክት ነው። ከሌሎች በተነፃፃሪ ደረጃ ሲታይ ፆታና አናሳ ጎሣዎች ተገቢ ውክልና አልተሰጣቸውም የሚለው አስተሳሰብ በመላው አለም በሰፊው የሚስተጋባ ሲሆን በመራጩ ሕዝብ መካከል ካላቸው የሥርጭት መጠን ጋር በሚመጣጠን ደረጃ ሴቶችና አናሣ ብሔረሰቦች በፓርላማ ውስጥ የተሻለ ውክልና ሊሰጣቸው ይገባል የሚል ክብደት የሚሰጠው ጥያቄ ነው።

---

[2] ***ተመጣጣኝ ውክልና = Proportional Representation***

ይህ ጥያቄ ፓርላማ የተለያዩ ማህበራዊ ቡድኖችን ማንነት በፖለቲካ አስተያየት ካለው ክፍፍል በተለየ መንገድ ማንፀባረቅ ይገባዋል ከሚለው እምነት ጋር ተያይዞ የሚነሣ ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ መፍትሔ ከመፈለግ አኳያ የሚቀርበው ሀሳብ በአንድ የምርጫ ክልል በርካታ አባላት የሚመረጡበትና የዕጩዎች ዝርዝር የሚቀርብበት የምርጫ ሥርዓትን መከተል ነው የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፓርቲዎች የመራጩን ሕዝብ ማህበራዊ ጥንቅር ሚዛን የጠበቀ የዕጩዎች ዝርዝር አዘጋጅተው በግልፅ ካላቀረቡ በስተቀር ቀደም ሲል ተገቢ ውክልና አላገኙም የሚሉትን ቡድኖች በፓርላማ ውስጥ በደንብ እንዲወከሉ የሚያስችል ብቸኛ የምርጫ ሥርዓት ማቅረብ እንደማይቻል መገንዘብ የተሻለው መፍትሔ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

እስከአሁን ድረስ የምርጫ ሥርዓቶች ከመራጩ ሕዝብ ጋር በተያያዘ መንገድ በፓርላማ ውክልና ጥንቅር ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ መገምገም በሚቻልባቸው መመዘኛዎች ረገድ ዋና ዋና የሚባሉ ታሳቢዎች ተብራርተዋል፡፡ ከእነዚህ ታሣቢዎች መገንዘብ የሚቻለው መሠረታዊ ሀሳብ የፖለቲካ ሥልጣን ቁጥጥር ሊደረግበትና የእኩልነት ማረጋገጫ ዴሞክራሲያዊ ተቋም ሊሆን የሚችለው የውክልና መድረክ በሆነው ፓርላማ ውስጥ የገቡ ግለሰቦችና ፓርቲዎች ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠሪነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የምርጫ ሥርዓት መርጦ በሥራ ላይ በማዋል መሆኑን ነው፡፡ ከላይ በተገለፁት የምርጫ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ መመዘኛዎች አንፃር የአብላጫ ሕግና ዝርዝር የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት የሚባሉትን ያላቸውን ደካማና ጠንካራ ጎን በተሻለ ግልፅነት መገምገም እንዲቻል ከዚህ በታች ጥቂት የማወዳደሪያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ከብዙ የምርጫ ሥርዓቶች መካከል ሁለቱን ብቻ መርጦ ለማየት የተፈለገው እነዚህ የምርጫ ሥርዓቶች ማንበብና መፃፍ የማይችሉ መራጮች በበዙበት አገር ጭምር በሠፊው ሥራ ላይ የዋሉ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በአገራችንም አሁን ባለው ሕገ-መንግሥት እንደተደነገገውም የተወካዮች ምክር ቤት አባላት የሚመረጡት በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት በመሆኑ ያስገኘውን መጥፎና ጥሩ ውጤት ለመመዘን እንዲቻል በማሰብ ነው፡፡

# 1.4 የድምፅ አሠጣጥ (የምርጫ) ሥርዓቶች

ትክክለኛ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ነፃ፣ ሕዝቡን በቀጥታና በተሟላ ሁኔታ የሚያሳትፍ፣ በታወቀ ሥርዓት የተመዘገበና ይፋ ለማድረግ በሚያስችል አሠራር ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ ከአብላጫ ሕግ አንስቶ እስከ ተመጣጣኝ ውክልና የድምፅ ሥርዓት ድረስ ብዙ ዓይነት የምርጫ ሥርዓቶች ያሉ ቢሆንም ሁሉም የሚጋሩት የጋራ ፀባይ ከተለያዩ መስኮች የቀረቡ አንድና ከዚያ በላይ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ለመምረጥ የሚቻልበትንና ዜጎች እያንዳንዳቸው የሰጡት ድምፅ እየተቆጠረ አንድ ላይ የሚደመርበትን አሠራር የሚከተሉ መሆናቸው ነው፡፡ አገሮች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ የምርጫ ሥርዓቶችን መሠረት አድርገው ከራሣቸው ልዩ ሁኔታ ጋር የሚጣጠመውን አንድ ዓይነት ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓቶችን አቀናጅተው ሥራ ላይ ያውላሉ፡፡

እዚህ ላይ ለማሳየት የተፈለገው መሠረታዊ ቁምነገር የተለያዩ አማራጮች መኖራቸውንና እያንዳንዱ አገር የራሱን ሕዝብ ማኅበራዊ አደረጃጀት፣ ጥንቅር፣ ባህልና ልምድ መሠረት አድርጎ ለተሻለ ውክልናና ዴሞክራሲያዊ አሠራር የሚበጀውንና የሚመቸውን ሊጠቀም መቻሉን ነው፡፡ ለአንድ አገር ሕዝብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም የሚመጥኑት ለሌላው ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ለአንድ አገር መልክዓ ምድራዊ ስፋትና የሕዝብ ብዛት የሚስማሙት ለሌላው ተስማሚ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ የእያነዳንዱን አማራጭ ጥቅምና ጉዳት ከእያንዳንዱ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እያመዛዘኑ ይበልጥ ውጤታማና ጠቃሚ የሆነውን መርጦ በሥራ ላይ ማዋል የእያንዳንዱ አገር ጉዳይ ነው፡፡

በተለያዩ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓቶች መካከል ያሉትን ደካማና ጠንካራ ጎኖች ለማየት ከመሞከር በፊት በቅድሚያ ትኩረትና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱ የድምፅ አሠጣጥ ሥርዓት የሚመዘንበት ዴሞክራሲያዊ መለኪያ እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ ሁሉም ዴሞክራሲያዊ መመዘኛዎች ለሁሉም ዓይነት የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓቶች በእኩል ደረጃ ላያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ከዴሞክራሲ አመለካከት አንፃር አንድም የምርጫ ሥርዓት ብቸኛና በራሱ የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ በራሱ የተሟላ የምርጫ ሥርዓት የማግኘት ሳይሆን የተሻለ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል ቅንብር የሚኖርበትን ሥርዓት የመመዘንና የመምረጥ ጉዳይ ስለሆነ ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ እነዚህ የተለያዩ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓቶች በተለያየ መንገድ ሥራ ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ መረዳት ተገቢ ነው። የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት በሚነደፍበት ጊዜ እንደየአገሩ ልዩ ሁኔታ የሚስማማውን አቅጣጫ ለመከተል በርካታ አማራጮችንና ቅንብሮችን መገምገም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። እያንዳንዱ ስርዓት እንዳለ ጥቅም ላይ ቢውልና ወይንም የተወሰነ ማስተካከያ ቢደረግበት ምን ጥቅምና ጉዳት እንደሚኖረው በቅድሚያ ጥልቅ ጥናት ማድረግ ይገባል።

የመጨረሻው ጥንቃቄ ደግሞ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓቱ ሥራ ላይ የሚውልበት ሥልት ራሱ የሚወሰነው በእያንዳንዱ አገር ውስጥ በመሬት ላይ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ መሆኑን የማወቅ ጉዳይ ነው። በእያንዳንዱ አገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሥርዓት ዓይነትና ባህርይ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀትና ሥርጭት ሁኔታ፣ የምርጫው ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቅንጅት፣ የዜጎች ፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ገፅታዎች የድምፅ አሰጣጡ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ የሚወስኑ መሠረታዊ ነገሮች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል።

በበርካታዎቹ የተሳካ ዴሞክራሲ በመሠረቱ አገሮች በሠፊው የሚሠራባቸው ሁለት ዓይነት የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓቶች አሉ። የመጀመሪያውና በታሪክም ቅድሚያ ያለው የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት ወይም የመጀመሪያ-አላፊ-አሸናፊ የሚሆንበት ነው። በዚህ ዓይነቱ የድምጽ አሠጣጥ ሥርዓት መሠረት ለውድድር የቀረቡ ዕጩዎች ያገኙት ድምፅ ተመጣጣኝነት ከግምት ውስጥ ሳይገባ አብላጫ ድምፅ ያገኘው አሸናፊ ይሆናል። በሌላ አገላለፅ በዚህ ድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት መሠረት «50%+1» የሚባለው የብዙሃን ድምፅ መገኘት የግድ አስፈላጊ አይደለም። የውድድሩ አሸናፊ ለመሆን የሚያስፈልገው ከተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ማግኘት ብቻ ነው። ይህ የምርጫ ሥርዓት አንድ ተመራጭ ብቻ በሚመረጥበት የምርጫ ክልል ውስጥ ሥራ ላይ የሚውል ነው። ይኸንን የምርጫ ሥርዓት ከሚጠቀሙበት አገሮች መካከል አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ካናዳና ኒውዚላንድ ይገ ኙበታል። በዚህ የምርጫ ሥርዓት ላይ ከሚቀርቡት ቅሬታዎች መካከል አንዱና ዋነኛው አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የመራጩን ብዙሃን ድምፅ ሳያገኝ አሸናፊ እንዲሆንና የመንግሥት ሥልጣን እንዲይዝ ያደርጋል የሚለው ነጥብ ነው። ምክንያቱም በዚህ የምርጫ ሥርዓት መሠረት አብላጫ ድምፅ በማግኘቱ አላፊ የሚሆነው ግለሰብ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ያገኘው የድምፅ መጠን የሌሎቹ ተወዳዳሪዎች ድምፅ አንድ ላይ ሲደመር ከሚገኘው ውጤት ያነሰ ስለሚሆን ነው። በዚህ መንገድ አሸናፊ የሆነ ግለሰብና ፓርቲ የመራጩን ሕዝብ ብዙሃን ድምፅ ባለማግኘቱ በየጊዜው የሚነሳውን ክርክር ለመቀነስ አገሮች የተለያዩ አማራጮችን በተጨማሪ ሥራ ላይ በማዋል የአብላጫ ድምፅ ሥርዓትን ውክልና የሚያሠፉ ጥረቶችን እያደረጉ ናቸው። ይኸም ቢሆን በሥራ ላይ በሚውልበት መንገድ የተለየ የራሱ ባሕሪይ ቢኖረውም ዞሮ ዞሮ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ አንድ ተመራጭ ብቻ የሚመረጥበት እንደመሆኑ በመሠረቱ ከአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው።

ሁለተኛው የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት የሚባለው ነው። ይህ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት የአብላጫ ድምፅ ሕግ የመራጮችን ድምፅ ያልተመጣጣነ ዋጋ እንዲኖረው የሚያደርግበትን ደካማ ጎን ከመሠረቱ በማስወገድ በፓርላማና በሌላም የውክልና አካል እያንዳንዱ ወገን ካገኘው ድምፅ ጋር የተመጣጣነ ውክልናና መቀመጫ እንዲያገኙ የሚያስችል ነው። ከተመጣጣኝ የውክልና ሥርዓት ዓይነቶች ውስጥ በስፋት በጥቅም ላይ የዋለው የዝርዝር ተመጣጣኝ ውክልና[3] የሚባለው ነው። ይህንን ሥርዓት ከሚጠቀሙበት አገሮች መካከል ስዊድን፣ ኖርዌይ፣ ፊንላንድ፣ዴንማርክ፣ ቤልጂየም፣ ሆላንድ፣ ኦስትሪያ፣ ስዊትዘርላንድ፣ ሉክሰምበርግ፣ ግሪክ፣ ፖርቱጋል፣ ስፔይን፣ አይስላንድ፣ እስራኤል፣ ኮስታሪካና ኮለምቢያ፣ ይገኙበታል።

ዝርዝር ተመጣጣኝ ውክልና ዝግ-ዝርዝርና ክፍት-ዝርዝር በሚባሉ ለሁለት የተከፈለ ነው። ይሁን እንጂ ከሁለቱ አማራጮች ውስጥ ዝግ-ዝርዝር ተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት በጣም አመቺና ቀላል በመሆኑ በብዙ አገሮች በሥራ ላይ ውሏል። የዝግ-ዝርዝር ተመጣጣኝ ውክልና (ከዚህ በኋላ ተመጣጣኝ ውክልና በማለት የሚጠቀስ ይሆናል) አመራረጥ ሥርዓት መራጮች በተለያዩ ፓርቲዎች አማካይነት ተዘጋጅቶ በሚቀርበውና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ደረጃ ቅደም ተከተል በያዘው የዕጩዎች ዝርዝር ላይ ተመሥርተው አንድ ድምፅ ብቻ እንዲሰጡ የሚደረግበት አሠራር ነው። ለተሻለ ግንዛቤ አንዲረዳ እነዚህን ሁለት ዋና ዋና የምርጫ አይነቶች በተናጠል ዘርዘር አድርጎ ማየት ይጠቅማል።

---

[3] *ዝርዝር ተመጣጣኝ ውክልና = List Proportional Representation*

## 1.4.1 የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ሥርዓት

አብላጫ ድምፅ ሕግ የሚባለው የምርጫ ሥርዓት አንድ ዕጩ ብቻ አላፊ በሚሆንበት አንድ የምርጫ ክልል ግለሰብና የፓርቲ ተወዳዳሪዎች ለምርጫ ተወዳድረው የሚመረጡበት ሥርዓት ነው:: ከዚህ ሥርዓት ጥቅሞች መካከል የሚጠቀሰው የመጀመሪያ ነጥብ በፓርላማ ውስጥ በአብዛኛው የአንድ ፓርቲ አብላጫነት እንዲኖር ስለሚያደርግና የሚመሠረተውም መንግሥት በተገኘው የምርጫ ድምፅ አብላጫ ውጤት ላይ የተመረኮዘ ስለሚሆን በፓርላማው ውስጥ ወጥ አመለካከት እንዲኖር ማስቻሉ ነው:: እንደዚህ ባለው ፓርላማ ውስጥ ብዙ የሚያከራክሩ አስተያየቶች ስለማይነሱ ውሣኔዎችን ለማሳለፍ ቀላል ነው:: ሌላው ጠቃሚ ጎኑ በተነፃፃሪነት የተሻለ ጂኦግራፊያዊ ውክልና እንዲኖር ስለሚያስችል በምርጫ ክልሎችና በተወካዮች መካከል ግልፅና ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር ይረዳል:: ይሁን እንጂ በርካታ ጉድለቶች እንዳሉት ማስተባበል አይቻልም::

የአብላጫ ድምፅ ከሚታዩበት ድክመቶች መካከል በመጀመሪያ የሚነሳው በመራጩ ሕዝብ ድምፅ መጨመርና መቀነስ እንዲሁም የፓርላማ መቀመጫ በማግኘትና በማጣት መካከል ያለው ግንኙነት ጥብቅ ባለመሆኑ ፓርቲዎችና ግለሰብ ተወዳዳሪዎች ለመራጩ ያላቸውን ተጠሪነት ይቀንሰዋል:: ምክንያቱም በአብላጫ ድምፅ ብቻ አላፊ መሆን ስለሚቻልና ምርጫውን ለማሸነፍና የፓርላማ መቀመጫ ለማግኘት የብዙሃን ድምፅ ማስመዝገብ አስፈላጊ ባለመሆኑ ነው:: ሌላው ድክመት በአንድ ፓርቲ ዕጩዎች መካከል ምርጫ ለማድረግ ዕድል ስለማይሰጥና በፓርቲ የቀረበው አንድ ዕጩ ብቻ እንዲመረጥ ስለሚያደርግ ተወካዩ ለመራጩ ሕዝብ ያለውን ተጠሪነት ደካማ የሚያደርግ መሆኑ ነው:: ሌላው የዚህ ምርጫ ሥርዓት ድክመት የተወዳዳሪ ፓርቲዎች የምርጫ ትኩረት ለማሸነፍ የሚያስችል ልዩነት በሚፈጥረው ቁጥር መገኘትና አቋማቸውን በሚቀያይሩ መራጮች ላይ ብቻ እንዲሆን ስለሚያደፋፍር የውድድር አድማስን የሚያጠብ መሆኑ ነው:: ሌላው ድክመት የፓርላማው ጥንቅር መራጩ ሕዝብ ለተለያዩ ፓርቲዎች ከሰጠው ድምፅ ሥርጭት ጋር ሲመዘን በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ አመለካከት ሥርጭት በከፍተኛ ደረጃ የማይወክል መሆኑ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የሚጠቀሰው ድክመት የተበታተኑ ደጋፊዎች ያላቸውን አነስተኛ ፓርቲዎች ከፓርላማ ውክልና ውጭ ስለሚያደርጋቸው ውጤታማ ምርጫ ለማድረግ ያለውን ዕድል ማጥበቡ ነው:: በጣም ከፍተኛ ድክመት ሆኖ የሚጠቀሰው ደግሞ የዚህ ዓይነቱ የምርጫ ሥርዓት ሰፊ ማህበራዊ ውክልና ያለው ፓርላማ ለመፍጠር የሚያበረታታ አለመሆኑ ነው:: ምክንያቱም ትልቁ ትኩረት አብላጫ ድምፅ አግኝቶ የፓርላማ አሸናፊነትን ማረጋገጥ እንጅ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ውክልና እንዲኖር ማስቻል ቅድሚያ የሚሰጠው ባለመሆኑ ነው:: በብዙ አገሮች ሰፊ ክርክር ያስነሳው ዋነኛ ድክመት ደግሞ በዚህ የምርጫ ሥርዓት የሚመሠረት መንግሥት በአነስተኛ ድምፅ ብልጫ የተደገፈ ስለሚሆን የብዙሃን ድጋፍ የሌለው መሆኑ ነው::

የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ሥርዓት ሌላው ከባድ ድክመት በተለያዩ የምርጫ ክልሎች ለሚወዳደሩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች የሚሰጠው ድምፅ እኩል ዋጋ እንዳይኖረው የሚያደርግ መሆኑ ነው:: በአንድ የምርጫ ክልል አነስተኛ አብላጫ ድምፅ አግኝቶ ያለፈው ሰው ያገኘው ድምፅ 10 ሺህ ቢሆን በሌላ የምርጫ ክልል ደግሞ በአብላጫ ድምፅ ያለፈ ተወዳዳሪ ያገኘው ድምፅ 50 ሺህ ሊሆን ይችላል:: በዚህ መሠረት የአንድ ምርጫ ክልል 10 ሽህ መራጮች ድምፅ የሌለው ምርጫ ክልል 50 ሺህ መራጮች ድምፅ አንድ ተወካይ እንዲኖራቸው ያስገድዳል:: በሁለቱ መካከል ያለው የ40 ሺህ ድምፅ ልዩነት ዋጋ ቢስ ከመሆኑም ሌላ የመራጮች ድምፅ እኩል ዋጋ እንዳይኖረው ያደርጋል::

የዚህ ምርጫ ሥርዓት ሌላ ድክመት ለብዙዎቹ የፓርላማ መቀመጫዎች የተሰጠው ድምፅ ውጤት አስቀድሞ ከታወቀ ሌሎች መራጮች ድምፅ ለመስጠት የሚደፋፈሩበት ሁኔታ እንዳይኖር ማድረጉ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የሚጠቀስ ድክመት ቢኖር በበርካታ የምርጫ ክልሎች የሚገኙ መራጮች በሌላው የምርጫ ክልል ያሉ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበትን ሁኔታ እንዳያውቁ የሚያደርግና በጣም ቴክኒካዊ በሆነ አሠራር ለሁለተኛ ጊዜ ድምፅ እንዲሰጡ የሚያደፋፍር መሆኑ ነው:: በዚህ የምርጫ ሥርዓት አንፃር የሚነሱ ድክመቶች ብዙ ቢሆኑም ለመጥቀስ የተሞከረው ዋና ዋናዎቹን ብቻ ነው::

## 1.4.2 የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት

ከዚህ ቀጥሎ ለማየት የሚሞከረው ደግሞ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ያለውን ጥቅምና ጉዳት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህ ሥርዓት ብዙ ተመራጮች በአንድ የምርጫ ክልል የሚመረጡበት ሥርዓት ነው፡፡ መራጮች በሚቀርቡላቸው የፓርቲ ዕጩዎች ዝርዝር መሠረት ድምፅ የሚሰጡ ሲሆን ዕጩዎች ደግሞ የሚመረጡት በመቀመጫዎችና በሚሰጠው የድምፅ ካርድ መካከል ሰፊ መመጣጠን እንዲኖር በሚያስችል የኮታ ሥርዓት ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት የዚህ ምርጫ ሥርዓት ግልፅ ዓላማ ተመጣጣኝነትን ማረጋገጥ ስለሆነ ነው፡፡ የዕጩዎች ዝርዝር ከማይቀርብባቸው ሌሎች የምርጫ ሥርዓቶች የበለጠ ይኸኛው ሥርዓት ተመጣጣኝነትን በማስገኘት ረገድ በጣም የተሻለ ነው፡፡

በሌላ አገላለፅ ይኸኛው የምርጫ ሥርዓት የጥምር መንግሥት ለመመሥረት ከሚያስገኘው ጥቅም ጋር በዴሞክራሲያዊ አመለካከት ሁሉንም ዓይነት የተመጣጣኝነት መመዘኛዎች ከሌሎች የምርጫ ሥርዓቶች በተሻለ ደረጃ ሊያሟላ የሚችል ሥርዓት ነው፡፡ እነዚህ የተመጣጣኝነት መመዘኛዎች ቀደም ሲል የተገለፁት የጂኦግራፊያዊ መልክዓ-ምድራዊ ውክልና፣ የአመለካከት ውክልናና የማህበራዊ ጥንቅር ውክልና የሚባሉት ናቸው፡፡ በእርግጥ የተመጣጣኝነት ውክልና አንድ አማራጭ የሆነው የዝግ ዝርዝር ተመጣጣኝነት ውክልና ሥርዓት የዕጩ ተመራጮች ቅደም ተከተል ደረጃ በፓርቲዎቹ ዝርዝር ላይ አስቀድሞ ስለተወሰነ መራጮች በዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ምርጫ ለማድረግ ያላቸውን ዕድል በተወሰነ ደረጃ ይቀንሰዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዝግ ተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት መሠረት የፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝርና ቅደም ተከተል የሚዘጋጀው በአካባቢ፣ በክልልና በብሔራዊ ደረጃ በሚገኙት የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አካላት መሆኑ ራሱ የተወሰነ ጉዳት ይኖረዋል፡፡ ይኸውም ለዕጩ ተወዳዳሪነት የሚታሰቡ ሰዎች በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲው ከፍተኛ መሪዎች ከሚገባው በላይ ታዛዥ የሚሆኑበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጉድለቶች መፍትሔ የማይገኝላቸው አይደሉም፡፡

የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ካሉት በርካታ ጥቅሞች መካከል በጣም ጎላ ብለው ሊጠቀሱ የሚችሉትን ብቻ አንድ በአንድ እየጠቀሱ ማየትና በአንፃሩ አሉ ከሚባሉት ድክመቶች መካከል ደግሞ ከፍተኛ ትኩረት የሚጠይቁትን በማቅረብ በጥቅሙና ጉዳቱ ላይ ተመስርቶ የተወሰነ የማመዛዘን ሥራ መሥራት የዚህን ምርጫ ሥርዓት ባሕሪይ በተሻለ መንገድ ለመረዳት እንደሚያስችል ይታመናል፡፡

በዚህም መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርበው የዚህ ምርጫ ሥርዓት ጠቃሚ ጎን በመራጩ ሕዝብ ድምጽ መጨመርና መቀነስ ወይም በፓርላማ መቀመጫ መገኘትና መታጣት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖር ስለሚያደርግ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸው ተጠሪነት ከፍተኛ እንዲሆን ማስቻሉ ነው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ደጋፊዎች የምርጫ ድምፃቸውን የሚሰጡለት ፓርቲ በከፍተኛ ድምፅ የፓርላማ ውክልና ለማግኘት ዕድል ሲኖረው አነስተኛ ድምፅ የሚያገኘው ፓርቲ ደግሞ ዝቅተኛ የፓርላማ ውክልና ለማግኘት ስለሚገደድ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የፓርላማ መቀመጫ መጠን የሚወሰነው በሚገኘው የምርጫ ድምፅ መሠረት እንደመሆኑ ከፍተኛ ድምፅ ያገኘው ፓርቲ ብዙ የፓርላማ መቀመጫዎችን ሲቆጣጠር ዝቅተኛ ድምፅ ያገኘው ደግሞ አነስተኛ የፓርላማ መቀመጫ እንዲኖረው ይገደዳል፡፡

ስለዚህም በምርጫ ድምፅ መጨመርና መቀነስ ወይም በፓርላማ መቀመጫ መገኘትና መታጣት መካከል ባለው ቀጥተኛ ግንኙነት የተነሳ ብዙ የድምፅ ድጋፍ ማግኘት በርካታ የፓርላማ መቀመጫ ለመያዝ እንደሚያስችል ፓርቲዎች ስለሚገነዘቡ ሁልጊዜም ከመራጩ ሕዝብ ጋር ያለው ግንኙነት ያሳስባቸዋል፡፡ መራጩ ሕዝብም ድጋፉን የመስጠትና የመንፈግ ሥልጣን ስላለው በፓርቲዎቹ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳረፍና ቁጥጥር ማድረግ ይችላል፡፡ በመሆኑም ተመራጮች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸው ተጠሪነት ከፍተኛ መሆኑ የግድ ነው፡፡ ሌላው የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ጥቅም በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች በፓርላማ ውስጥ ውክልና እንዲያገኙና በሚገባም እንዲንፀባረቁ የሚያስችል መሆኑ ነው፡፡ በተመጣጣኝ ውክልና ምርጫ ሥርዓት አንድ ብቸኛ ፓርቲ የፓርላማ ስልጣን ጠቅልሎ የሚወስድበት ዕድል የተዘጋ ነው፡፡ ወይንም አንድ ገናና ፓርቲ ከመንግሥት ሥልጣን የአንበሣውን ድርሻ ለብቻው ወስዶ አድራጊና ፈጣሪ የሚሆንበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ ይኸ ከሌላ ደግሞ በፓርላማ ውስጥ አንድ ወጥ በሆነ ርዕዮተዓለም የተሸበበ የአንድ ቡድን አመለካከት

የሚነግሥበት ዕድል የለም:: የተመጣጣኝ ውክልና ምርጫ ሥርዓት አንዱ መመዘኛም የተለያዩ አመለካከቶች ውክልና በፓርላማ ውስጥ መኖር እንደመሆኑ የተለያየ አመለካከት የሚወክሉ ፓርቲዎች በፓርላማው መቀመጫ ማግኘታቸው ተፈላጊ ጉዳይ ነው:: የተለያዩ ፓርቲዎች በፓርላማው ውስጥ መኖር ማለት በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ አመለካቶች የፓርላማ ውክልና እንዲያገኙና በሚገባም እንዲንሸራሸሩ ማድረግ ማለት ነው:: የዴሞክራሲ ሥርዓት ዋነኛ ባህሪም የተለያዩ አመለካከቶች እንዲቻቻሉና አብረው እንዲኖሩ ማድረግ በመሆኑ የተመጣጣኝ ውክልና ምርጫ ሥርዓት ይኸንኑ መርህ ተግባራዊ በማድረግ የተሻለው አማራጭ ነው:: ሌላው መጠቀስ የሚገባው ጥቅም ፓርቲዎች የመራጩን ሕዝብ ማኅበራዊ ጥንቅር ሚዛን የሚጠብቅ የዕጩዎች ዝርዝር አዘጋጅተው ለምርጫ ውድድር እንዲያቀርቡ ስለሚያደፋፍር ፓርላማው የተሻለ ማህበራዊ ውክልና ያለው እንዲሆን ማስቻሉ ነው::

እያንዳንዱ ፓርቲ የዜጎችን የፆታ፣ የዕድሜ፣ የትምህርት፣ የጎሣ፣ የባህል፣ የሥራና የመሳሰሉትን ልዩነቶች የሚያቻችል የዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር አዘጋጅቶ ሲያቀርብ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅምና ፍላጎት የሚጠብቅ አጀንዳ እንደሚኖረው አንድ ጥሩ ምልክት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል:: በዚህ መንገድ የተሻለ ማህበራዊ ጥንቅር የሚያሟላ የእጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር የሚያቀርብ ፓርቲ ከመራጩ ሕዝብ የተለያዩ ክፍሎች የድጋፍ ድምፅ አግኝቶ ለመመረጥ እድል ያገኛል:: ከዚህ በተጨማሪ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት የተለያዩ ፓርቲዎች ወደ ፓርላማ እንዲገቡ መፍቀድ መሆኑ በራሱ ሰፊ ማህበራዊ ጥንቅር ያለው ውክልና እንዲኖር አስተዋፅኦ ይኖረዋል:: ምክንያቱም ሁሉም ፓርቲዎች አንድ ዓይነት ፆታ፣ አንድ አይነት የእድሜ፣ የትምህርትና የልምድ ደረጃ ያላቸውን ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሊያቀርቡ አይችሉም:: ወይንም ሁሉም ፓርቲዎች ከአንድ ዓይነት ባህል፣ ከአንድ ዓይነት ኃይማኖትና ጎሣ ብቻ የሚገኙ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ያቀርባሉ ተብሎ አይታሰብም:: በተለያየ የሥራ መስክ፣ በተለያየ የሙያና የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ እጩ ተወዳዳሪዎችን ማቅረባቸው የማይቀር ነው:: እንዲህ ዓይነት ማህበራዊ ጥንቅር ያለው ፓርላማ ሲመሠረት ደግሞ የፓርላማው ማህበራዊ ውክልና ሰፊ እንደሚሆን የሚያጠራጥር አይደለም::

የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ሌላ ጠቃሚ ጎን በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚገኝ ዜጋ ለማንኛውም ፓርቲ የሚሰጠው ድምፅ እኩል ዋጋ እንዲኖረው ማስቻሉ ነው:: ይህ አይነቱ ጠቃሚ ጎን በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት እንደሌለ ቀደም ሲል ለማሳየት ተሞክሯል:: በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት በአንደኛው የአገሪቱ ክፍል ውስጥ በሚገኝ አንድ የምርጫ ክልል የሚኖሩ 30 ሺህ መራጮች አንድ የፓርላማ ተወካይ ቢመርጡ በሌላው የአገሪቱ ክፍል በሚገኝ ሌላ የምርጫ ክልል ውስጥ የሚኖሩ 10 ሺህ መራጮችም አንድ የፓርላማ ተወካይ የሚመርጡበት ያልተመጣጠነ ሁኔታ ይኖራል:: ይኸም ማለት የመራጮች ድምፅ እኩል ዋጋ ስለማይኖረው በ30 እና 10 ሺህ መካከል የሚገኘው የ20 ሺህ መራጭ ድምፅ ዋጋ ቢስ ነው ማለት ነው::በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ግን በየትኛውም ክልል የሚኖር ዜጋ፣ ለማንኛውም ፓርቲ የሚሰጠው ድምፅ እኩል ዋጋ ይኖረዋል:: ከዚህ በተጨማሪ የሚጠቀስ ጠቃሚ ጎን ቢኖር በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት የሚመሰርቱ መንግሥታት የብዙሃን ድጋፍ ያላቸው እንዲሆኑ ማስቻሉ ነው::

ቀደም ሲል በተገለፀው የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ይኸ ጉድለት በሰፊው ይንፀባረቃል:: በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት የምርጫ አሸናፊ የሚሆነው ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች መካከል የድምፅ ብልጫ ያገኘው እንጂ የብዙሃን ድምፅ ድጋፍ ያገኘው አይደለም:: ለምሳሌ አንድ ሺህ መራጮች በሚገኙ ብት አንድ የምርጫ ክልል ሁሉም ድምፅ እንደሰጡ ተደርጎ ቢወሰድና ሦስት ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ቢያቀርቡ ከሦስቱ መካከል ደግሞ አንደኛው ብቻ 400 ድምፅ ቢያገኝ አሸናፊ የሚሆነው 400 ድምፅ ያገኘው ነው:: ማለፍ ያልቻሉት የሁለቱ ተወዳዳሪዎች ድምፅ አንድ ላይ ሲደመር ግን 600 ድምፅ ነው የሚሆነው:: በዚህ መሠረት አሸናፊነት ከብዙሃን ድምፅ መገኘት ጋር ምንም ተያያዥነት የለውም ማለት ነው:: ከዚህ አጭር ምሳሌ ተነስተን ስንገመግም በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት አሸናፊ የሚሆኑ ፓርቲዎች የሚመሠርቷቸው መንግሥታት የብዙሃን ድጋፍ የሌላቸው የሚሆኑበት ድክመት በግልፅ ይታያል:: በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ይህ ዓይነት ችግር ጎልቶ ሊከሰት አይችልም:: ምክንያቱም የተለያዩ ፓርቲዎች በአገኙት ድምፅ ልክ የሚመጣጠን የፓርላማ መቀመጫ የሚያገኙበት ዕድል ስላለ ለተለያዩ ፓርቲዎች ድምፅ የሰጠው መራጭ ተወካዮቹን በፓርላማ ለማስገባት የሚችልበት ሁኔታ ሰፊ በመሆኑ ነው:: እናም የብዙሃኑን ሕዝብ ድምፅ ዋጋ የሚያጣበት ዕድል የጠበበ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚቋቋሙት መንግሥታትም በአብዛኛው መራጭ ድምፅ የተደገፉ እንደሚሆኑ የታመነ ነው::

በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ጠቃሚ ጎን መነሣት የሚገባው ሌላ ጉዳይ ፓርቲዎች የሚያደርጉት የምርጫ ውድድር በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች በእኩል ደረጃ እንዲዳረስ የሚያስችል መሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ በግልፅ የተለየ የምርጫ ክልል ወሰን መኖር ያለው ፖለቲካዊ ጥቅም ዝቅተኛ ነው። እንዲያውም አንዳንድ አገሮች አገሩን በጠቅላላ እንደ አንድ የምርጫ ክልል የሚወስዱበት ሁኔታ አለ። ምክንያቱም መራጮች ድምፅ የሚሰጡት ፓርቲዎች በሚያቀርቡት የዕጩዎች ዝርዝር ላይ ተመስርተው ስለሆነና በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚገኝ መራጭ ዜጋ ለማንኛውም ፓርቲ የሚሰጠው ድምፅ እኩል ዋጋ ስለሚኖረው የተለያዩ የምርጫ ክልሎችን መወሰን በውድድሩ ውጤት ረገድ የሚያስገኘው ፖለቲካዊ ፋይዳ ትልቅ ግምት የማይሰጠው በመሆኑ ነው። ሌላው የተመጣጠኝ ውክልና ሥርዓት ጥቅም የሕዝብ ሥልጣን ውክልና የተሰጣቸው ፓርቲዎች የመራጩን ሕዝብ ድጋፍ ማግኘትና ማጣት የውክልና ሥልጣን ለማግኘት ያለውን ትርጉም በሚገባ ተገንዝበው ከመራጩ ሕዝብ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማስቻሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አነስተኛ ፓርቲዎች በፓርላማው ውስጥ በአቅማቸው ልክ ውክልና ለማግኘት የሚችሉበት ዕድል የተዘጋ እንዳልሆነ መራጮች ተገንዝበው ለሚፈልጉት ፓርቲ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ ስለሚያደፋፍር የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በተመጣጣኝ ምርጫ ሥርዓት ለአናሳ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚሰጥ ድምፅ አይባክንም። ለምሳሌ እንደ ኢጣሊያ ባሉ አገሮች በምርጫ ጊዜ በተሰጠው ድምፅ መጠን ፓርቲዎች ተመሳሳይ ውክልና ያገኛሉ። አንድ ፓርቲ ከተሰጠው ድምፅ ውስጥ ያገኘው 10 ከመቶ ብቻ ቢሆን በሕግ አውጪው ውስጥ 10 በመቶ መቀመጫዎችን ያገኛል እንጂ መራጮች የሰጡት ድምጽ ውድቅ የሚሆንበትና የሚባክንበት ሁኔታ የለም።

የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት አሁን ከተጠቀሱት ጥቂት ጠንካራ ጎኖች በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት ቢታወቅም ምንም ዓይነት እንከን የማይወጣለትና አንድም ድክመት የሌለው አድርጎ መረዳት ግን ትክክል አይሆንም። በመሆኑም ይኸንን የምርጫ ሥርዓት በሚመለከት ከሚነሱት ደካማ ጎኖች መካከል በጣም አከራካሪ የሆነውን እዚህ ላይ ማንሳት አስፈላጊው ነው። ብዙ ጊዜ እየተደጋገመ እንደድክመት የሚነሳው ነጥብ በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት የሚመሠረት መንግሥት በርካታ አናሣ ፓርቲዎች የፓርላማ መቀመጫ እንዲያገኙ የሚያግዝ በመሆኑ ጠንካራ የጥምር መንግሥት ለማቋቋም እንቅፋት ይፈጥራል የሚል ነው።

የሚመሠረተው ጥምር መንግስት ጠንካራ ካልሆነ ደግሞ በጥቃቅን የአስተሳሰብ ልዩነቶች ሳይቀር ቶሎ ቶሎ የሚፈርስ ፓርላማ ይሆንና የተረጋጋ መንግስት በማቋቋም አገርን ለመምራት ዕድል አይሰጥም። ይኸ ስጋት በተለያዩ ጊዜያት በታዩ ተጨባጭ ክስተቶች የታየና እውነተኛ ስጋት መሆኑ አይካድም።

ይሁን እንጂ ይህ ችግር መፍትሔ የሌለውና የተመጣጣኝ ውክልና ስርዓትን መልካም ውጤቶች ጨርሶ የሚያጠፋ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። የዚህ ዓይነቱ ድክመት የሚወገድበትን መፍትሔ በማስቀመጥ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ጠንካራ ጥምር መንግስት ለማቋቋም የሚያስችል ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ ይቻላል። ጀርመን በዚህ ረገድ በመልካም ምሳሌነት የምትጠቀስ አገር ነች። ከዚህ ሌላ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ድክመት ተደርጎ የሚጠቀሰው ነጥብ በምርጫው ውጤትና በሚቋቋመው መንግስት መካከል ያለው ግንኙነት ቀጥተኛ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገለፅ በመሆኑ የተጠሪነት ሁኔታን ይቀንሳል የሚል ነው። ይኸም ማለት በዚህ የምርጫ ሥርዓት አንድና ገናና ፓርቲ በብቸኝነት አሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት ሁኔታ ስለሌለና የተለያዩ ፓርቲዎች በሚያገኙት ድምፅ መጠን ውክልና የሚያገኙበት ዕድል ክፍት በመሆኑ የትኛው ፓርቲ ከየትኛው ጋር ቅንጅት እንደሚመሰርት፣ ማን ከማን ጋር ስምምነት ፈጥሮ መንግስት እንደሚያቋቁም አስቀድሞ ለማወቅ እንደማይቻል የሚያመለክት ነው። ስለዚህም የሚመሰረተው መንግስት የመራጩን ድምፅ አግኝተው የፓርላማ መቀመጫ ማሸነፍ በሚችሉ የተለያዩ ፓርቲዎች መካከል ጥምረት ለመፍጠር በሚካሄድ ድርድርና በሚደረስበት ስምምነት የሚወሰን እንጂ በቀጥታ በተገኘው ድምፅ ስለማይሆን መንግስት ለመራጩ ሕዝብ ያለው ተጠሪነት ጠንካራ አይሆንም ከሚል ሥጋት የሚመነጭ ነው።

ይሁን እንጂ የተለያዩ ፓርቲዎች በመንግስት ምስረታ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችለውን ፈቃድ ያገኙት መራጩ ሕዝብ በሰጣቸው የምርጫ ድምፅ መሆኑን ስለሚገነዘቡ የሚቋቋመው

መንግስት ጠንካራ ተጠሪነት እንዲኖረው ጥንቃቄ ማድረጋቸው የማይቀር ነው። መንግሥት ከመሠረቱ በኋላ ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን ተጠሪነት በቸልታ ይመለከቱታል የሚለውም ስጋት ትልቅ ክብደት የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም በዴሞክራሲ ስርዓት መራጩ ሕዝብ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግባቸውና ከፓርላማ ውጭ የሆኑ የተለያዩ ሰፊ አማራጮች ስለሚኖሩት አንድ ፓርላማ መንግስትን ከመሰረትኩኝ በኋላ ከመራጩ ሕዝብ የሚመጣ ምንም ነገር የለም ብሎ ሊቀመጥና መራጩን እስከመርሣት ይደርሳል ለማለት አይቻልም። ከዚህም ሌላ በድክመት መልክ የሚነሳው አንድ ነጥብ በጥምር መንግስት አደረጃጀት የግልፅነት ጉድለት ከተፈጠረ ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ተጠሪነት በግልፅ ላይታይ ይችላል ወይም ድብቅ ይሆናል የሚለው ነው። ይኸ አባባል የሚቋቋመው መንግስት በተለያዩ ፓርቲዎች ጥምረት የሚመሠረት ስለሚሆን አንዱ በሌላው እየተሸፈነ ለልማቱ የሚመሰገነውን፣ ለጥፋቱ ደግሞ የሚወቀሰውን ፓርቲ መለየት አይቻልም የሚል መልዕክት ያዘለ ነው። ይሁን እንጂ የዴሞክራሲ ሕብረተሰብ አንዱ ባህርይ ግልጽነት እንደመሆኑ ተመስጋኝና ተወቃሹን ለመለየት ከባድ ፈተና ያጋጥማል ለማለት አያስደፍርም። ሌላው አንደድክመት የሚነሳው የዕጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር በፓርቲዎች ተዘጋጅቶ ስለሚቀርብ እያንዳንዱ ተወካይ በግሉ ለመራጩ ሕዝብ ያለው ተጠሪነት ደካማ እንዲሆን ያደርጋል የሚለው ነው።

ይኸም ቢሆን ከፍተኛ ችግር ተደርጎ የሚታይ አይደለም። ምክንያቱም አንድ የፓርቲ ተወካይ የሚመርጠኝም የሚሸረኝም ለውድድር ያቀረበኝ ፓርቲ እንጂ ድምፁን የሰጠኝ መራጭ አይደለም በሚል መራጩን ረስቶ በፓርላማ ውስጥ ተደላድሎ ሊቀመጥ አይችልም። በተወከለበት የፓርላማ መድረክ የመራጩን ሕዝብ ጥያቄዎች ትኩረት እንዲያገኙና መፍትሔም እንዲፈለግላቸው ከመስራት አይቦዝንም። እያንዳንዱ የፓርቲ ተወካይ ለዜጎች መሠረታዊ ጉዳዮች በሚኖረው ተቆርቋሪነትና ለመራጩ ሕዝብ ባለው ተጠሪነት የፓርቲው ተቀባይነት እንደሚጨምር ታሳቢ አድርጎ ስለሚሰራ የተባለው ድክመት ጎልቶ ሊንፀባረቅ አይችልም።

በመሠረታዊው የፓርቲው መርሆዎች ላይ ከባድ ቅራኔ የሚፈጥር እስካልሆነ ድረስ ለመራጩ ሕዝብ ጥቅም ታማኝ መሆን ለፓርቲው የሚኖረውን ታማኝነት ሊቀንስበት አይችልም። እንደውም በዴሞክራሲ ሥርዓቶች በተግባር እንደሚታየው የፓርላማ መቀመጫ ያገኘ አንድ የፓርቲ ተወካይ በፓርቲው መሠረታዊ መርሆዎችና በዜጎች መሠረታዊ ጥቅሞች መካከል ቅራኔ መኖሩን ተገንዝቦ የመራጮችን ጥቅም ማስቀደም ይገባኛል ብሎ ከወሰነ ለፓርቲው ያለውን ታማኝነት በመተው ከመራጮች ጥቅም ጎን ሊቆም ይችላል። በዚህ አቋሙ ምን አልባት ከፓርቲው እንደሚባረር ቢያውቅም እንኳ ለሕሊናውና ለመራጩ ሕዝብ ታማኝ መሆንን የሚመርጥበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። በአሜሪካ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የዴሞክራቲክና የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላት በማንኛውም ጉዳይ ሁልጊዜም ከየፓርቲዎቻቸው አጀንዳዎች ጎን ይቆማሉ ማለት አይቻልም። አንዳንድ ጊዜ በሪፐብሊካኖቹ የሚቀርበው አጀንዳ ለዜጎች ጥያቄ የበለጠ መፍትሔ የሚሰጥ መስሎ ሲታያቸው የዴሞክራሲ ፓርቲ ተወካዮች የፓርቲያቸው ፍላጎት ባይሆንም እንኳ ድጋፋቸውን ይሰጣሉ። ወይንም በሪፐብሊካኑ ፓርቲ የሚደገፍ አንድ ጉዳይ የዜጎችን ጥያቄ የማይመልስ መስሎ ቢሰማው ሊቃወም ይችላል። ስለዚህ በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ያለው ነፃነት የፓርቲ እስረኛ አድርጎ ማስቀመጥን ስለማይፈቅድ ተወካዮች በግል ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን ተጠሪነት አያዳክመውም።

ከዚህ በተጨማሪ የተመጣጣኝ ውክልና ደካማ ጎን ተደርጎ የሚጠቀሰው ነጥብ የምርጫ ክልሎች ስፋት ስለሚኖራቸው ተመራጮች ለምርጫ ክልላቸው ያላቸውን ተጠሪነት ያጠፋዋል የሚለው ነው። እንደሚታወቀው የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ዋነኛ ዓላማ በሁሉም ረገድ ተመጣጣኝነትን ማስገኘት እንደመሆኑ ይኸንን ተመጣጣኝነት ለማሟላት የፓርቲዎች ውድድር ሁሉንም የአገሪቱ ክፍሎች በእኩል ደረጃ የሚያዳርስ መሆኑ የማይቀር ነው። ይህ አይነቱ የምርጫ ሥርዓት የጂኦግራፊ፣ የአመለካከትና የማህበራዊ ጥንቅር ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖር የሚጠይቅ በመሆኑ ለአንዱ አካባቢ ቅድሚያ ሰጥቶ ለሌለው አካባቢ ግድየለሽነት ማሳየት አያስችልም። ስለዚህ ለሁሉም አካባቢዎች እኩል ትኩረት በመስጠት ከሌሎቹ የምርጫ ሥርዓቶች ሁሉ የተሻለው የተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት በመሆኑ ለምርጫ ክልል ያለውን ተጠ ሪነት ያጠፋዋል የሚለው ስጋት የተጋነነ ነው።

በአብላጫ ድምፅ ሥርዓትና በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ዙሪያ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ከሞላ ጎደል ተነስተዋል። በመርህ ደረጃ የምርጫ ሥርዓትን የሚመለከቱ መሠረታዊ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው እንደየአገሩ ሁኔታ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ አማራጮችና ከተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚታዩ ልምዶች በመጠኑም ቢሆን ተፈትሸዋል። የምርጫ ሥርዓት መሠረታዊ ሀሣቦችንና ተጨባጭ ልምዶችን ለመዳሰስ ከተደረገው የእስካሁኑ ሙከራ መማር የሚቻለው አንድ ቁምነገር ቢኖር ሁሉም የምርጫ ስርዓቶች በሁሉም አገሮች በተመሣሣይ መንገድ ስራ ላይ ሊውሉ አለመቻላቸውን ነው።

አገሮች አንድ ላይ የሚጋሯቸው አጠቃላይ መርሆዎች ቢኖሩም እነዚህ ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ  የእያንዳንዱን አገር ልዩ ሁኔታ ታሣቢ የማድረግና ከዚሁ ጋር መርሆዎችን የማጣጣም ሥራ መከናወኑ የማይቀር ነው። ዴሞክራሲን በሚያራምዱ አገሮች የሚካሄድ የምርጫ ሥርዓት የሚመሰረትባቸው መርሆዎች ቀጥተኛ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ነፃ፣ እኩል፣ ትክክለኛና ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ምርጫን ማካሄድ የሚሉት መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የትኛውን የድምፅ አሠጣጥ (የአመራረጥ) ሥርዓት መከተል ያስፈልጋል የሚለው ለእያንዳንዱ አገር ምርጫ የሚተው ነው። የአንዳንዱ አገር ፖለቲካዊ አመለካከት፣ ማህበራዊ ጥንቅር፣ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ኤኮኖሚያዊና ባህላዊ ገፅታ ለተመጣጣኝ ውክልና ስርዓት የሚያመች ሲሆን የሌላው ደግሞ ለአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የሚያመች ሊሆን ይችላል። አንዳንዱ አገር ከአንድ በላይ የሆኑ የምርጫ ሥርዓቶችን እያቀናጀ ለመጠቀም የሚገደድበት ሁኔታ ሲኖር ሌላው መሠረታዊውን መርህ በማያናጋ መንገድ የተወሰነ ማስተካከያ እያደረገ በአንድ ዓይነት ሥርዓት ብቻ ለመጠቀም የሚገደድበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ እንደየአገሩ ሁኔታ የጂኦግራፊ፣ የማህበራዊ ጥንቅርና ፖለቲካዊ አመለካከት ውክልናን የሚያረጋግጡ፣ ብቁና ውጤታማ ለሆነ የሪሶርስ አጠቃቀም አመቺ የሆኑ፣ አጠቃላይ መርሆዎችን ከተጨባጩ ሁኔታ ጋር ለማስማማት የማያስቸግሩ፣ ጉድለቶችን ለማረምና ለመቀነስ ዕድል የሚሰጡ የድምፅ አሰጣጥ (የምርጫ) ሥርዓቶችን መርጦ መጠቀም የእያንዳንዱ አገር ፋንታ ነው። በየአገሩ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የዜጎችን መብት በማረጋገጥ ረገድ የትኛው የምርጫ ሥርዓት እንደሚሻል የመለየትና ጥቅምና ጉዳቱን አመዛዝኖ የመወሰን ጉዳይ የእያንዳንዱ አገር ድርሻ ነው።

## 1.5 ምርጫና ለመራጩ ሥልጣን መስጠት

የምርጫ ሥርዓቶች ጉዳይ ሲነሣ አብሮ መታየት ያለበት ከፍተኛ ነጥብ በምርጫ ተግባር የመራጮች መብትና ሥልጣን ምንድን ነው? የሚለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የትኛው የምርጫ ሥርዓት ተገቢ ውክልና እንደሚያስገኝለት፣ ፍላጎቱንና ጥቅሙን እንደሚያስከብርለት መምረጥ የራሱ የመራጩ መብት ነው። በሁለተኛ ደረጃ ብቃት ያለው ምርጫ ለማድረግ የሚያስችለው መንገድ በግለሰብ ተወዳዳሪዎች መካከል ማማረጥ ነው ወይንስ በፓርቲ ተወዳዳሪዎች መካከል ማማረጥ የሚለውን መወሰን ያለበት ራሱ መራጩ ነው። በእርግጥ ቀደም ባሉት ገለፃዎች እንደተብራራው በአሁኑ ጊዜ ባለው አገራዊ ፖለቲካ በጣም ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው በፓርቲ ተወዳዳሪዎች መካከል ምርጫ ማድረግ ነው። ነገር ግን በግለሰብ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚካሄደውንም ምርጫ ጨርሶ መዘንጋት አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ከሁሉም በላይ በዴሞክራሲያዊ አመለካከት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ነገር በመጀመሪያ ደረጃ ምርጫ ለማካሄድ ብቁ አማራጮች መቅረብ ያለባቸው መሆኑ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ከተወዳዳሪ ፓርቲዎችም ይሁን በተወዳዳሪ ግለሰቦች መካከል የሚደረገው ምርጫ ራሱ ብቃት ያለው እንዲሆን ማድረግ ነው። መራጮች በተወዳዳሪ ፓርቲዎች መካከል የሚያደርጉት ብቃት ያለው ምርጫ ጠቃሚ የሚሆነው ለዜጎች ፖለቲካዊ ትኩረት ቅድሚያ ሰጥቶ በአገር ደረጃ በስፋት የሚንቀሳቀስና በፓርላማ መድረክም ድምፁ ሊሠማ በሚችል ደረጃ ውክልና የሚኖረው የተደራጀ አካል ስለሚያስገኝላቸው ነው።

በተመሣሣይ ሁኔታ መራጮች በግለሰብ ተወዳዳሪዎች መካከል የሚያደርጉት ብቃት ያለው ምርጫ ጠቃሚ የሚሆነው ዜጎች በጎሣ፣ በፆታና በመሣሰሉት ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያሏቸውን ማንነትና ባህርይ የሚወክል ሰው ሊያስገኝላቸው ስለሚችል ነው። ዞሮ ዞሮ ምርጫው በፓርቲ ተወዳዳሪዎች መካከል ይሁን በግለሰብ ተወዳዳሪዎች ተፈላጊው ነጥብ የመራጩን ጥቅምና

ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ የመወከል ብቃት ያለው እንዲሆን ማድረጉ ላይ ነው:: ብቃት ያለው ምርጫ ለማካሄድ ደግሞ ብቁ አማራጭ ተወዳዳሪዎችን ብቻ ሳይሆን ተስማሚ የምርጫ ስርዓትንም መምረጥ የማይታለፍ ጥያቄ ነው:: ቀደም ሲል ስለምርጫ ስርዓቶች በሚገለጽበት ጊዜ እንደታየው የአብላጫ ድምፅ ስርዓት በሁሉም ረገድ ብቃት ያለው ምርጫ ለማድረግ ከባድ ችግር ያለበት ነው:: የተለያዩ አገሮች እንደየሁኔታው ማስተካከያ እያደረጉና የተለያዩ የአፈፃፀም አማራጮችን እየተጠቀሙ በስራ ላይ እንደሚያውሉት ቢታመንም ያሉትን ድክመቶች ለመቀነስ አሁንም ከባድ ፈተናዎች አሉባቸው:: የአብላጫ ድምጽም ሆነ የዚሁ ምርጫ ሥርዓት ሁሉም በአንድ የምርጫ ክልል አንድ አሸናፊ የሚወክልበትን አቅጣጫ ስለሚከተሉ እንዲሁም በምርጫ ክልሉ ከተሰጠው ድምጽ የብዙሃኑን ድጋፍ ከማግኘት ይልቅ ከተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ማግኘትን ብቻ እንደመሠረታዊ መመዘኛ ስለሚቀበሉ መራጩ ብቃት ያለው ምርጫ እንዲያደርግ የሚያደፋፍሩ አልሆኑም:: እነዚህ የምርጫ ሥርዓቶች አነስተኛ ፓርቲዎች በፓርላማ ውስጥ ምንም አይነት ውክልና እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ በመሆኑ የብዙ መራጮችን ድምፅ ዋጋ አሳጥተውታል:: የመራጮች ድምጽ እኩል ዋጋ እንዳያገኝ የሚደርጉ ከመሆናቸውም በላይ የአመለካከትና የማህበራዊ ጥንቅር ውክልናን በማሟላት ረገድ ከባድ ድክመት አለባቸው:: ምንም እንኳ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ዓይነት የምርጫ ሥርዓቶች የሚጋሩት ችግር ቢሆንም የፓርቲ ተወዳዳሪ ዕጩዎች ለመራጩ የሚቀርቡት በፓርቲዎቹ ተመርጠውና በዕጩ ማቅረቢያ ዝርዝር ተመዝግበው ስለሚሆን መራጮች በአንድ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ለማማረጥ ዕድል የላቸውም:: መራጮች ፓርቲዎቹ ባቀረቡት የዕጩዎች ዝርዝር ላይ መቀነስም መጨመርም አይችሉም:: የቀረበውን ተቀብለው ከመምረጥ በስተቀር ሌላ ዕድል የላቸውም::

በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተጠቀሱት የአብላጫ ድምፅ ሥርዓቶች ብቁ ምርጫ ለማካሄድ ከባድ ድክመት ስላለባቸው መራጮች በምርጫ ወቅት ያላቸው ተሳትፎ እየቀነሰ እንዲመጣ ካደረጉ በርካታ ምክንያቶች መካከል ክብደት የሚሰጣቸው ሆነዋል:: ሌሎቹ የምርጫ ሥርዓቶች ደግሞ ተመጣጣኝነትን ማስገኘት ቀዳሚ አላማቸው አድርገው ስለሚሠሩ መራጮች በተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦች መካከል ብቁ ምርጫ ለማድረግ እንዲችሉ የተሻለ ዕድል ፈጥረዋል:: ተመጣጣኝነትን ማሟላት ብቃትንም የሚያጠቃልል ሰፊ ማዕቀፍ ስለሚሆን ከሌሎቹ የምርጫ ሥርዓቶች ይልቅ የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓቶች በስራ ላይ በሚውሉበት አገር የመራጮች ተሣትፎ ከፍተኛ ሆኖ ነው የሚታየው:: የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓቶች ልዩ ልዩ አማራጮች ያሏቸው መሆኑ ቀደም ሲል የተገለፀ ሲሆን ሁሉም ዓይነት የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓቶች መራጮች በተለያዩ ተወዳዳሪዎች መካከል ብቁ ምርጫ እንዲያደርጉ በሚፈጥሩት ሰፊ ዕድል ከሌሎቹ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል:: ሁሉም የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓቶች በአንድ የምርጫ ክልል ብዙ አባላት የሚመረጡባቸው ስለሆኑ መራጮች በተወዳዳሪ ፓርቲ ዕጩዎችና በተወዳዳሪ ግለሰቦች መካከል የተወሰነ ማመዛዘን አድርገው እንዲመርጡ ያስችሏቸዋል:: በአንድ የምርጫ ክልል ብዙ አባላት የሚመረጡባቸው ሥርዓቶች ስለሆኑ ብዙ ቁጥር ያሏቸውን ተወካዮች ከአንድ የምርጫ ክልል ያስገኛሉ:: ከአብላጫ ድምፅ ሥርዓቶች ጋር ሲወዳደሩ የተመጣጣኝ ውክልና ስርዓቶች ሰፊ በሆኑ የምርጫ ክልሎች የሚካሄዱ ስለሆነ ቢያንስ ሁለት የተሻለ ጥቅም ለመራጮች ያስገኛሉ:: እነዚህም አንደኛ ከሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች መካከል ለመራጮች ጥቅምና ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ተቆርቋሪ የሆነና ማንነቱን በሚገባ ለይተው የሚያውቁት ተወካይ ሊያገኙ ይችላሉ::

ሁለተኛ ደግሞ መራጮች በምርጫው ዕለት በአንድ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከል ለማማረጥ ዕድል ይኖራቸዋል:: እናም ሁሉም ተወዳዳሪዎች በተቻለ መጠን በምርጫ ክልል ደረጃ የሚገኙበት ሁኔታ ይኖራል:: በእነዚህ መሠረታዊ ምክንያቶች የተነሳ መራጮች በተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት ጎልቶ የሚነሳው ችግር ጠንካራ የጥምር መንግስት ለመፍጠር አያስችልም የሚለው ቢሆንም ብዙ አገሮች መፍትሔ እንዳገኙለትና ውጤታማም እንደሆኑበት በተግባር የታየ ነው::

ስለዚህ የምርጫ ሥርዓቶችን የመምረጥ ጉዳይ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የመንግሥታት ኃላፊዎች ብቻ ተደርጎ መታየት የሚገባው አይደለም:: መራጮች የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን አመዛዝነው ጥቅምና ፋላጎታቸውን በተሻለ ደረጃ ያውላል የሚሉትን የምርጫ ሥርዓት የመምረጥ ሥልጣን እንዲኖራቸው ማስቻል የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚያቅደው አሠራር ነው::

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለራሱ አሸናፊነት ይጠቅመኛል የሚለውን አማራጭ እንደፈለገው እየወሰነ ስራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ የመራጩ መብትና ሥልጣን ሊጠበቅ አይችልም፡፡ ምርጫን የተወሰነ ጊዜ እየጠበቁ ማካሄድና በምርጫ ስም ስልጣን መያዝ ብቻውን የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ አይሆንም፡፡ የመራጩን ሙሉ ፈቃድና ስምምነት ያገኘ የምርጫ ሥርዓት መከተል፣ መራጩ ከቀረቡለት አማራጮች መካከል ያለአንዳች አስገዳጅ ኃይልና በራሱ ፈቃድ የፈለገውን እንዲመርጥ ማስቻልና ምርጫዎች የብዙሃኑ ሕዝብ ተሣትፎ በሚገባ የሚያረጋገጥባቸው እንዲሆኑ ማድረግ የዴሞክራሲ ስርዓት የሚጠይቀው ግዴታ ነው፡፡ ሕጋዊ ሥልጣን የሚለው እነዚህን ሁኔታዎች በሚያሟላ መንገድ በተካሄደ ምርጫ የተያዘ ሥልጣን ነው፡፡

የዘመናዊ ፖለቲካ ሥርዓቶች የተመሰረቱት ሕዝቡ በተወሰነ ጊዜ በሚካሄድ ምርጫ በሚደርገው ተሳትፎ ላይ መሆኑ ባይካድም ተሳትፎው በምን ያክል ስፋትና ደረጃ እንደሚገለጽ ማወቅና የምርጫው ጥራት ምን ያክል አስተማማኝ እንደሆነ መረዳት ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ እስካሁን የታዩ ልምዶች እንደሚያረጋግጡት በምዕራብ አውሮፓ አገሮች ከ85% በላይ የሚሆኑ መራጮች በምርጫ መደበኛ ጊዜ እየተገኙ ተሣትፎ ሲያደርጉ በሌሎቹ አካባቢዎች ደግሞ የመራጮች ተሳትፎ መቀነስ ይታያል፡፡ ዜጎች ድምጽ ለመስጠትና በፖለቲካ ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት የሚሳዩት ከሁሉም በላይ ጥያቄያቸውና ፍላጎታቸው ትኩረት አግኝቷል ብለው ሲያምኑ ነው፡፡ ወጣቶች የሥራ ዋስትና እንደሚያገኙ ተስፋ ሲያደርጉ ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸው ይጨምራል፡፡ ተስፋ ከቆረጡ ደግሞ ተሳትፎአቸው ይቀንሣል፡፡ ሴቶች የፆታ አድሎ እንደሚወገድና በሁሉም መስክ እኩል ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችል ዕድል እንደሚፈጠር ሲያምኑ ተሳትፎአቸው ይጨምራል፡፡ ምሑራን ለአካዳሚክ ነፃነት መከበርና ለጥናትና ምርምር መስፋፋት ዋስትና እንደሚኖር ሲያውቁ፣ ገበሬዎች በእርሻ መሬታቸውና ምርታቸው ላይ ባለሙሉ መብት እንደሚሆኑ ሲገነዘቡ፣ ሠራተኞች የተሻለ የሥራ አካባቢ እንደሚፈጠርላቸው ሲያምኑ፣ ባለሀብቶች ለምርት ለአገልገሎትና ለኢንቨስትመንት (ለልማት) ማደግ የተሻለ ነገር እንደሚመጣ ተስፋ ሲያደርጉ ፖለቲካዊ ተሳትፎአቸው ይጨምራል፡፡ በምርጫ ንቁ ተሳትፎ ከማድረግ በተጨማሪ በፖለቲካ ፓርቲዎችና በግፊት ማድረጊያ ቡድኖች (pressure groups) ውስጥ የመሳተፍ ፍላጎት ያሳያሉ፡፡ አንዳንዴ መራጮች ድጋፋቸውን ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ቅሬታቸውን፣ ስጋታቸውንና ተቃውሟቸውንም ለማሳየት ከፍተኛ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በምርጫ ጊዜ የመራጮች ተሳትፎ እንዲጨምርና እንዲቀንስ የሚያደርግ ሌላ ነጥብ የምርጫ ሥርዓት ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው የተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ስርዓት ለመራጮች ተሳትፎ መጨመር ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚደርግ ሥርዓት ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ዓይነቱ የምርጫ ሥርዓት በተጨባጭ የብዙሃን ፓርቲ ተሳትፎ መኖር ብቻ ሳይሆን ሁሉም ባገኘው ድምፅ ልክ የሚመጣጠን ውክልና ስለሚገኝና የሚባክን የመራጭ ድምፅ ስለማይኖር ነው፡፡

በብዙዎቹ የምዕራብ አውሮፓ አገሮች የመራጮች ተሳትፎ ከፍተኛ የመሆኑ ምስጢር በአብዛኛው ከዚሁ የምርጫ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት በሕግ አውጭው ውስጥ በሚደረጉ ክርክሮች በቀላሉ ስምምነት ላይ የሚደረስበትን ሁኔታ በመፍጠር የተረጋጋ መንግስት እንዲኖር ያደርጋል ከሚለው ነጥብ ባሻገር የመራጮችን ሰፊ ተሳትፎ በማረጋገጥም ሆነ የብዙሃን ፓርቲ ተሳትፎን በማስገኘት ረገድ የሚመሰገን ነው ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም የአናሣ ፓርቲዎችን ውክልና በመገደብ ለእነዚህ ፓርቲዎች መራጮች የሚሰጡት ድምፅ እንዲባክን ስለሚያደርግ ነው፡፡ የአናሣ ፓርቲዎች ውክልና የተገደበ መሆኑንና ለእነዚህ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድምፅ እንደሚባክን መራጮች አስቀድመው በሚገነዘቡበት ጊዜ ተሳትፎ ከማድረግ ይቆጠባሉ፡፡ ስለዚህ የመራጮች ተሳትፎ እንዲጨምር ብቃቱና ጥራቱም አስተማማኝ የሆነ ምርጫ እንዲኖር ከተፈለገ መራጮች የሚስማማቸው የምርጫ ሥርዓት የትኛው ዓይነት መሆን እንዳለበት ራሳቸው እንዲወስኑ ሥልጣን መስጠት ያስፈልጋል፡፡

## 1.6 **በድምጽ አሠጣጥ ሥርዓት አብዛኛ ድምፅ (Majority vote)**

በምርጫ ሥርዓት አብዛኛ ድምፅ (Majority vote) ሲባል ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ የንድፈ ሀሳብ ክርክሮችን ሲያስነሳ የቆየ ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ ፅንሰ ሃሳብ ዙሪያ ብዙ ጊዜ ከሚነሱት ክርክሮች መካከል አብዛኛ ድምፅ ሲባል መምረጥ ከሚገባቸው መካከል አብዛኛውን ማለት ነውን? ወይንስ ደግሞ የምርጫ ድምፅ ከሰጡት መካከል አብዛኛውን ማለት ነው?

የሚለው አንደኛው ነው:: በዚህ ፅንሰ ሃሳብ ላይ የሚነሳው ሌላ ክርክር የአብዛኛ ድምፅ መኖር ትክክለኛ ምርጫን ይወክላልን? ወይንስ አይወክልም? የሚለው ነው:: ከዚህም ያለፈ ክርክር በአብዛኛ ድምፅ ምንነት ላይ ይነሳል:: አንዳንድ ጊዜ አብዛኛ ድምፅ ማግኘት ሲባል ተቀባይነት ካጡ ሌሎች በርካታ አመራጮች መካከል አንደኛው ያገኘውን አንፃራዊ ተመራጭነት ብቻ የሚያሳይ ነው የሚሉም አሉ::

ይኸኛው አስተሳሰብ አብዛኛ ድምፅ ማግኘት ትክክለኛ ምርጫን ይወክላል ብሎ ሙሉ በሙሉ መደምደም እንደማይገባ ለማሳየት የሚቀርብ አመለካከት ነው:: ወይንም ደግሞ ውሣኔ ሕዝብን እንደትክክለኛ የውሣኔ አሰጣጥ ዘይቤ አድርጎ መጠቀም ለውሣኔው ትክክለኛነት አስተማማኝ ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም ከሚለው የቆየ ክርክር ጋር የተያያዘ ነው:: ይኸኛውን ክርክር የሚያራምዱ ክፍሎች የሚያነሱት ነጥብ በተለይም ለኃላፊነት ቦታ የሚወክልን ሰው ከሌሎች ሁሉ የተሻለ ሆኖ መገኘቱንና በትክክል መመረጡን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዝርዝር ሕጎችና የአሰራር ስርዓቶች በሌሉበት ሁኔታ ውሣኔ ሕዝብን መጠቀምና የአብዛኛ መራጭ ድምፅን መመዘኛ ማድረግ አስቸጋሪ ነው የሚለውን ቴክኒካል አሰራር ነው::

እነዚህንና የመሳሰሉ ሌሎች ክርክሮች ቢኖርም በምርጫ ሥርዓት የአብዛኛ ድምፅ አሰራር ከሞላ ጎደል አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውና በተግባርም እየዋለ የሚገኝ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ነው:: በእርግጥ የአብዛኛ ድምፅ ሥርዓት በሁሉም ጉዳዮች ላይ ይሰራበታል ማለት ሳይሆን በተመረጡና ስምምነት በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ነው:: በተለይ ደግሞ በቂ ክርክርና ውይይት በተደረገባቸው ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ አሣሪ ውሣኔ መስጠት በሚያስፈልግበት ጊዜ ነው:: በሕዝብ ተወካዮች ምርጫም በ50%+1 (Simple Majority) መሠረት የአብዛኛ ድምፅ ይሰራበታል:: በፖለቲካዊ ሥርዓትም ሆነ በሌላ ጉዳይ የሚነሳ ሕገመንግስታዊ ማሻሻያ ተቀባይነት የሚያገኘው በአብዛኛው ጊዜ በ2/3ኛ ድምፅ እንዲሆን በብዙ አገሮች ሕገመንግስቶች ውስጥ ተደንግጓል::

የአብዛኛ ድምፅ ሥርዓትን በ50%+1 ድምፅን ለመግለፅ አነስተኛ የአብዛኛ ድምፅ ሥርዓት (simple majority) ወይም ከተሰጠው ድምፅ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሆነውን በአጠቃላይ ለመግለፅ ፍፁም አብዛኛ (Absolute majority)፣ የሁሉም ተወዳዳሪዎች ድምፅ አንድ ላይ ተደምሮ ከሚሰጠው ቁጥር በላይ ብልጫ ያለውን ለመግለጽ ጠቅላላ አብዛኛ (overall majority)፣ አንድ ጉዳይ ወይም ተመራጭ አላፊ የሚያደርገውን የድምፅ ዋጋ እንዲያስመዘግብ የተወሰነ የመራጭ ድምፅ መጠን እንደአስፈላጊ ሁኔታ በሚጠየቅበት ጊዜ ብቁ አብዛኛ (Qualified majority) እያሉ መጥራት የተለመደ ነው::

እነዚህ የተለያዩ የአብዛኛ ድምፅ አይነቶች በተለያዩ አገሮች እንደአስፈላጊነቱ ስራ ላይ የሚውሉ ሲሆን ለሕዝብ ተወካዮች ምርጫ፣ ለፓርላማ ውሣኔዎች፣ ለሕገ መንግስት ማሻሻያና ሌሎች ውሣኔ ሕዝብ ለሚሰጥባቸው ጉዳዮች፣ ለተለያዩ የኮሚቴ ውሣኔዎች በጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው:: በመንግስታት ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በአለም አቀፍ ተቋሞች፣ በሞያ ማህበራት፣ በተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ተቋሞች ሁሉ አገልግሎት ይሰጣሉ::

ከላይ ከተዘረዘሩት በርካታ የአብዛኛ ድምፅ አይነቶች የትኛው ለየትኛው ጉዳይ ቢያገለግል ይሻላል የሚለውን መርጦ የሚወስነው ራሱ አገልግሎቱን የሚፈልገው አገር፣ መንግሥት፣ ሕዝብ፣ ማህበር፣ ድርጅት፣ ኮሚቴ ወዘተ. ነው:: ከዚህ ውጭ ለዚህኛው ጉዳይ ይኸኛው አይነት አብዛኛ ድምፅ ሥርዓት የግድ አስፈላጊ ነው በሚል የተቀመጠ ወጥ የሆነ አሰራር የለም:: ይህ ማለት ግን አንዱ ከሌላው ጠቃሚ ልምድ አይማርም ማለት አይደለም:: በማንኛውም መስክ እንደሚደረገው በዚህም ረገድ በተደጋጋሚ ጊዜ በስራ ላይ ውሎ ውጤታማ ሆኖ የተገኘውን የሌላ ተሞክሮ መቅሰምና ለራስ እንደሚስማማ አድርጎ መጠቀም የሚከለክል ነገር አይደለም::

ነገር ግን በምርጫ አሰጣጥ ሥርዓት አነስተኛ የአብዛኛ ድምፅ (Simple Majority rule) ሕግ በብዙዎቹ ዴሞክራሲ አገሮች ተቀባይነት ያገኘና በሕግም እንደግዴታ ሆኖ የተቀመጠ ሥርዓት ነው:: አነስተኛ የአብዛኛ ድምፅ መገኘት የሚለው በቁጥር ሲገለጽ በ50%+1 ሲሆን አንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም አንድ ለውሣኔ የቀረበ ሃሳብ አላፊ መሆኑ ተቀባይነት የሚኖረው ድምፅ ከሰጠ

-ት መካከል ይኸንኑ አነስተኛ የአብዛኛ ድምጽ መጠን ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው። በዴሞክራሲ አመለካከት ለምርጫ የቀረበ ዕጩ ተወዳዳሪም ሆነ ለውሣኔ የቀረበ ሀሳብ ይኸንን አነስተኛ የአብዛኛ ድምፅ አግኝቶ አላፊ ከሆነ ተቀባይነቱ አስተማማኝ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። አፈፃፀሙ የዴሞራሲን ሥርዓት ተከትሎ እስከሆነ ድረስ በተገኘው ውጤት ሕጋዊነት ላይ ጠንካራ ክርክር ሊነሳ አይችልም። ከዚህ በተለየ መንገድ አነስተኛ የአብዛኛ ድምጽ በ50%+1 ወይም በአጠቃላይ ከግማሽ በላይ የሆነ አብዛኛ ድምጽ (ፍፁም አብዛኛ) ሳያስፈልግ ከተሰጠው ድምፅ መካከል በድጋፍ የተመዘገበው በተቃውሞ ከተመዘገበው የበለጠ ሆኖ ከተገኘ ብቻ በፖለቲካ ረገድ ሕጋዊ ነው የሚል አካሄድ እንዳለ ቀደም ሲል ተገልጿል።

ይኸኛው አሰራር የአብላጫ ድምጽ (Plurality rule) የምርጫ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች የሚታይ ሲሆን ከ50% አብዛኛ ድምጽ ባነሰ መጠን ከተወዳዳሪዎች መካከል የበለጠ ድምፅ የሚመሰረቱ መንግስታት ብዙ ጊዜ የብዙሃኑ መራጭ ድጋፍ የሌላቸው እየተባሉ የሚቀሰቀሱት በዚህ የተነሳ ነው። በዚህ ዓይነት ሥርዓት የሚተላለፉ ውሣኔዎችም የአነስተኛው ክፍል ድጋፍ ብቻ ያላቸው ናቸው በሚል ብዙ ጊዜ ቅሬታ የሚቀርብባቸው ናቸው።

ስለዚህ አንድ ሕግ ከመውጣቱ በፊት፣ አንድ ውሣኔ ከመተላለፉ በፊት፣ አንድ ሀሳብ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊትና አንድ ተመራጭ አሸናፊ ከመሆኑ በፊት ከተሰጠው ድምፅ ውስጥ ቢያንስ አነስተኛ የአብዛኛ ድምፅ (50%+1) ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ የብዙሃኑን መራጭ ፈቃድና ስምምነት እንደማግኘት የሚቆጠር ነው።

ከሁሉም በላይ ደግሞ አፈፃፀሙ የዴሞክራሲን አግባብ ተከትሎ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በውጤቱ ላይ ጠንካራ ክስና ወቀሳ እያነሱ ለመከራከር ያለው ዕድል አነስተኛ ነው። በእርግጥ ዴሞክራሲ በሌለባቸው አገሮች በምርጫም ሆነ በሌላ ሁኔታ የአብዛኛ ድምፅ ድጋፍ ማግኘት የሚቻልበት አሰራር የዴሞክራሲ ስርዓት በሚከተሉ አገሮች ካለው የተለየ ነው። ዴሞክራሲ በሌለባቸው አገሮች ዴሞክራሲ እንዳለ ለማስመሰል መራጩን እያስገደዱ፣ የማይፈልገውን እንዳይቃወም እያስፈራሩና እነርሱ የሚፈልጉትን እንዲደግፍ በልዩ ልዩ የተቀዕኖ መንገዶች እያስጨነቁ የአብዛኛ ድጋፍ አግኝተናል ይላሉ። ብዙ ጊዜ በእነዚህ አገሮች የሚመዘገበው ውጤት ከ98% በታች ዝቅ አይልም። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከ100% በላይ እየሄደ አለምን የሚያስገርምበት አጋጣሚ አለ። በአጠቃላይ ከዴክሞራሲያዊ የምርጫ ድምጽና ውሣኔ አሰጣጥ ሥርዓት ውጪ የሚመዘገብ የአብዛኛ ድምፅ ውጤት ሕጋዊነትም ተቀባይነትም የሌለው ነው።

## 1.7 በድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት የአናሣ ድምጽ (Minority vote)

አናሣዎች (Minorities) ሲባል በአንድ በኩል በተወሰነ አመለካከት በአንድ የተለየ የፖለቲካ ሥርዓት ክልል ውስጥ በግልጽ ብዙሃን ሆነው የማይገኙትን የሚመለከት ጽንሰ ሀሣብ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በቁጥር አነስተኛ ሆነው የሚገኙትን የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚመለከት ነው። በአመለካከትና በቁጥር ብዙሃን ሆነው የማይገኙትን ለመግለፅ ሲባል አናሣ ፓርቲዎች፣ አናሣ ጎሣዎች፣ አናሣ መራጮች ወዘተ. እያሉ መጥራት የተለመደ ነው።

በፖለቲካዊ መንገድ አናሣዎችን በሚመለከት ጠቃሚ የሆነ ትርጉም በሕብረተሰቡ ውስጥ በብዙ ጉዳዮች ላይ የጋራ ፍላጎትና እምነት ያላቸውን፣ በአብዛኛው ሕዝብ ተገቢ አያያዝ የማይደረግላቸውንና ነገር ግን ብዙ አስፈላጊ ነገሮች ሊሟሉላቸው የሚገቡትን ይልቁንም ልዩ እንክብካቤ ሊደረጉላቸው የሚገቡትን ቡድኖች የሚመለከት መሆኑ ነው። በሌላ አባባል በሕብረተሰቡ ውስጥ በጣም የተበደሉ፣ የተለየ ሕጋዊ ጥበቃና ገንቢ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድላቸው የሚገቡትን የጎሣ፣ የኃይማኖት፣ የብሔረሰብ ቡድኖችን የሚመለከት ነው። ከዚህም በላይ አናሣዎች ቋሚነት ያላቸው ቢያንስ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩና ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ተቋማዊና መዋቅራዊ መሠረቶች እንዲፈጠሩላቸው የሚያስፈልጓቸው ናቸው። በብዙ ሕብረተሰብ ውስጥ በተለይ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የፆታ አናሳዎችን በሚመለከት የሚሰማው ድምጽ ከፍተኛ ነው። አናሣ ጎሣዎችንና አናሣ የፖለቲካ ፓርቲዎችንም በሚመለከት ተመሳሳይ አቤቱታ ይሰማል።

አናሣዎችን በሚመለከት በከፍተኛ ደረጃ አሳሳቢ ሆኖ የሚታየው ስጋት በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸው ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ አሳሳቢው ጉዳይ በገዥዎች የሚደርስባቸው መገለልና የበታች ሆነው የሚታዩበትን አመለካከትና አሰራር ለመለወጥ የሚያስችል ተገቢ ጥበቃ የማይደረግላቸው መሆኑ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሴቶች በቁጥር ደረጃ በሕዝቡ ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር ይዘው ነገር ግን በአጠቃላይ አገላለፅ ፖለቲካዊ በሆነ መንገድ አናሣ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም በታሪክ የወንዶች የበታች ሆነው ሲታዩ በመቆየታቸውና የተሟላ መብት ስለሌላቸው ነው፡፡ በእርግጥ በሕዝቡ ውስጥ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሳይሆኑ ወይም በሕዝቡ ውስጥ ቁጥራቸው ብዙ ሆኖ ሳለ አናሳ እንደሆኑ አድርጎ መግለጽ በከፊል ትርጉም አልባ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በአመለካከት ረገድ የበታች ተደርገው የሚታዩበትና በአሰራርም በደል የሚደርስባቸው መሆኑ እስካልተወገደ ድረስ የቁጥራቸው ብዛት ብቻውን አናሣ አንዳይሆኑ አያደርጋቸውም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አናሣዎች የሚለው አገላለጽ በጠቅላላው የልዩነቱ መሠረት በቁጥር ማነስና በፖሊሲ አለመጣጣም ብቻ ሳይሆን በርዕዮተ ዓለማዊ ፉክክር ላይ ሲሆን አናሣ ፓርቲዎችን ወይንም አናሳ የሕዝብ አስተያየትን ለማመልከት ያገለግላል፡፡ በምርጫ ስርዓቶችም ስለአናሳዎች የሚነሳው ጥያቄ ሁለት ገጽታዎች ያሉት ነው፡፡ ይኸውም አንደኛ አናሣ ቁጥር ያላቸውን መራጮችና ሁለተኛ አናሣ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን የሚመለከት ነው፡፡ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መራጮች በምርጫ ወቅት የሰጡት ድምጽ ከሌሎች በማነሱ የፓላርማ መድረክ የሚወክልና ለጥቅማቸው የሚከራከር ያጣሉ፡፡ የዚህ አይነቱ መገለል የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ሲባል የአናሣ መራጮች አመለካከት በፓርላማ የሚወከልበትን ሁኔታ በተለየ መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲኖር በእነዚህ አናሣዎች ውክልና መረጋገጥ የሚያስችል ድርድርና ስምምነት በማድረግ ችግሩን መፍታት ይቻላል፡፡

አናሣ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችንም የሚመለከተው ችግር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለአናሣ ፓርቲዎች ድምፃቸውን የሚሰጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ፓርቲዎቹ በምርጫ ውድድር አሸናፊው የፓርላማ መቀመጫ ካልያዙ አመለካከታቸው በፓርላማ ውስጥ ውክልና ያጣል፡፡ እንዲህ አይነቱ የውክልና ማጣት ችግር የሚያስከትለውን መገለል ለመከላከል እንደየአገሩ ሁኔታ ልዩ ልዩ ገንቢ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ ለምሳሌ በጀርመን የዳሽ አናሣዎችን የሚወክለው የደቡብ ስከልስዊግ መራጮች ማህበር የአገሪቱ ሕገ መንግስት የሚጠይቀውን የ5ኸ ድምጽ ቅድመ ሁኔታ ሳያሟላ በፓርላማ ውስጥ ውክልና እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ የቀድሞው ምስራቅ ጀርመን ሶሻሊስት አንድነት ፓርቲ የነበረውና አሁን የዴሞክራቲክ ሲሻሊዝም ፓርቲ የሚባለው የፖለቲካ ድርጅት ለምስራቁ የሀገሪቱ ክፍል መራጮች ውክልና መኖር ሲባል የ5ኸ መሰናክል ሕግ በተለየ መንገድ ስራ ላይ እንዲውል በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኙት በመስማማታቸው በቡንደስታግ (በሀገሪቱ ፓርላማ) ውስጥ ውክልና እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

በሌሎችም አገሮች እንደዚሁ በተለያየ ምክንያት በፖለቲካ አናሣ ተደርገው ለሚታዩ ክፍሎች አስተሳሰባቸው በፓርላማ ውስጥ እንዲወከል የሚያስችል ሕጋዊ ጥበቃ እንዲኖር ልዩ ልዩ ገንቢ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ ዋናው ነገር በቁጥርም ይሁን በተወሰነ አመለካከት ምክንያት ብዙሃን ሆነው የማይገኙትን የሕብረተሰብ ክፍሎችና ፓርቲዎች የሚያገል ፖሊሲ መከተል ለአንድ አገር ዴሞክራሲ፣ ሠላምና ልማት አደጋ የሚፈጥር መሆኑን በመረዳት የአናሣዎችንም ውክልና የሚያሟላ ሰፊና አሰባሳቢ የፖለቲካ ማዕቀፍ መፍጠር ይገባል የሚለውን ዴሞክራሲያዊ አሠራር መከተል ነው፡፡

## 1.8 **የባለአደራነት ሥልጣን** (Mandate)

ብዙ ጊዜ መንግሥታት ለሚወስዱት ማንኛውም እርምጃ በምርጫ ጊዜ አገኘን የሚሉትን የባለአደራነት ሥልጣን እንደምክንያት ሲያቀርቡ መስማት የተለመደ ነው፡፡ ይኸንን ባለአደራነት አገኘን የሚሉት ፓርቲያቸው ለውድድር መልምሎ ያቀረበውን ዕጩ መራጩ ሕዝብ የድምፅ ድጋፍ በመስጠት አሸናፊ እንዲሆን ማድረጉን በመጥቀስ ነው፡፡ በእርግጥም ፓርቲዎች ለውድድር የሚያቀርቧቸው በሚወዳደሩበት ጊዜ ፓርቲያቸው ወደፊት ሥልጣን ቢያገኝ የሚመራበትን አቅጣጫ በፓርቲያቸው መርሆዎችና ፖሊሲዎች ላይ ተመስርተው ለሕዝብ

የሚያቀርቡበት ሁኔታ መኖሩ የማይቀር ነው:: በዚህ መንገድ የፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚቀርቡት የፓርቲዎች መወዳደሪያ ሰነድ በእንግሊዞች አጠራር የምርጫ ማኒፌስቶ ሲባል በአሜሪካኖች ደግሞ ፕላት ፎርም እየተባለ የሚጠራው ነው:: በሌሎችም ዴሞክራቲክ አገሮች እንደየቋንቋቸው የሚጠራ የፓርቲዎች መወዳደሪያ ሰነድ አዘጋጅቶ የማቅረብ አሰራር መኖሩ የሚታወቅ ነው:: እዚህ ላይ ለሁሉም የጋራ የሆነው ነጥብ አንድ ፓርቲ ለምርጫ ውድድር ያቀረባቸው ዕጩዎች አሸናፊ ሆነው የመንግስት ሥልጣን በሚይዝበት ጊዜ በውድድር ወቅት በቀረበው ማኒፌስቶ መሠረት እንዲአስተዳድር የሕዝብ ፈቃድና የባለአደራነት ሥልጣን አግኝቻለሁ ብሎ የሚከራከርበት ሁኔታ መኖሩ ነው:: ይኸንን አቋም ለመያዝ የሚያስችል መብትና ሕጋዊነት ተገኘ የሚባለው ደግሞ በምርጫ ሂደት መራጩ ከሰጠው ውሳኔ ነው::

ነገር ግን ከሥልጣን ባለአደራነት ጋር የተያያዙ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው:: በዴሞክራሲ አመለካከት በምርጫ ጊዜ ፓርቲዎች ፖሊሲዎቻቸውን ለመራጩ ሕዝብ ይፋ ማድረጋቸው ጠቃሚ መሆኑ ይታመንበታል:: ነገር ግን ይህ ሁኔታ በጥንቃቄ መታየት የሚገባው ነው:: ምክንያቱም በአንድ በኩል በምርጫ ማኒፌስቶ ወይም ፕላት ፎርም የሚቀርቡ ሃሳቦች አንድ ፓርቲ የመንግስት ሥልጣን ሲይዝ ሊመራባቸው የሚገቡትን ጉዳዮች በጥንቃቄና በተሟላ ሁኔታ ይይዛሉ የሚል ግምት ወደሚያሳድር የተሳሳተ መደምደሚያ ሊያደርስ ስለሚችል፣ በሌላ በኩል ደግሞ አሸናፊው ፓርቲ በማኒፌስቶው ውስጥ ላቀረባቸው ነጥቦች በሙሉ የመራጩን ድጋፍ ለማግኘቱ እርግጠኛ የሚያደርግ በቂ ማረጋገጫ ስለማይገኝ ነው::

ለአንድ የተወሰነ ምርጫ ውድድር በሚዘጋጅ አንድ ማኒፌስቶ ወይም ፕላት ፎርም አንድ ፓርቲ ለበርካታ ዓመታት ሊያከናውናቸው የሚፈልጋቸውን ሁሉንም የፖሊሲ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ አካቶ ሊያቀርብ ይችላል ብሎ መጠበቅ ትክክል አይደለም:: ምንአልባት ዋና ዋና የሚሉትን ለይቶ ማቅረብ ይቻል ይሆናል:: በዚህም የተነሳ አንድ ፓርቲ በምርጫ ወቅት የገባውን ቃልና ሕዝቡም የሰጠውን ድጋፍ መሠረት በማድረግ ሁሉንም የፓርቲ ፖሊሲ ነጥቦች ሙሉ በሙሉ የመፈፀም መብት አለው ማለት እንደዚሁ ደካማ መከራከሪያ ነው:: ምክንያቱም መራጮች በፓርቲ መወዳደሪያ ማኒፌስቶ ወይም ፕላት ፎርም ከቀረቡት ሀሳቦች መካከል የሚፈልጓቸውንና የሚቃወሟቸውን እየለዩ  ተወዳዳሪዎችን ለመምረጥ የሚችሉበት ሁኔታ የለም:: መራጮች ድምፅ በሚሰጡበት ጊዜ ማድረግ የሚችሉት አንድም ሙሉ በሙሉ ድጋፍ መስጠት አሊያም ሙሉ በሙሉ ድጋፋቸውን መንሳት ነው:: ከሚሰጡት ድምፅ ውስጥ ግማሹን ለሚደግፉት ሃሳብ በማድረግ ግማሹን ደግሞ ለሚቃወሙት የሚያደርጉበት ዕድል የለም::

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መራጮች ድምጻቸውን የሚሰጡት ፓርቲው ለሚያራምዳቸው ፖሊሲዎች ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ለራሱ ለፓርቲው የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል:: የመራጮችን ፖለቲካዊ ድጋፍ የሚወስኑ እንደማህበራዊ ስፍራ፣ ፖለቲካዊ አመለካከትና የመሳሰሉ መሰረታዊ ጉዳዮች ቢኖሩም ባልተለመዱ ሁኔታዎች ምክንያት ፓርቲዎች በሚያቀርቡት የፖሊሲ ሀሳብ ፋንታ ፓርቲዎቹ ራሳቸው የመራጮችን ድጋፍ የሚያገኙበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል:: ከዚህ በተጨማሪ ፓርቲዎች የመወዳደሪያ ማኒፌስቶ ወይም ፕላት ፎረም በሚያዘጋጁበት ጊዜ ያልታዩና መራጩም አስተያየቱን ያልሰጠባቸው ነገር ግን መልስ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ከምርጫ በኋላ ሊፈጠሩ ይችላል:: ስለዚህ በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ አንድ ፓርቲ አንዴ የመንግስት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ በሚሰጥበት ጊዜ በተወሰነ ደረጃ ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባው መቀበል ያስፈልጋል:: እናም የባለአደራነት ሥልጣን ሲባል ዳር ድንበሩ ተለይቶ የማይታወቅና በምርጫ አሸናፊነት እያሳበቡ ፈላጭ ቆራጭ የሚኮንንበት ሳይሆን ሁልጊዜም የመራጩን ፈቃድና ፍላጎት እየጠበቁ ሊገለገሉበት የሚገባ ኃላፊነት ነው::

## 1.9 በምርጫ ጊዜ የሚታዩ ችግሮችና የመከላከያ መፍትሔዎች

የምርጫ ተግባር በጣም ከባድና የተወሳሰበ እንደመሆኑ ብዙ ዓይነት ችግሮች ያለበት ነው:: እንደየሁኔታው የችግሩ ማነስና መብዛት ወይንም መቅለልና መክበድ ይለያይ እንጂ አንዳችም ጉድለት የሌለበት ምርጫ ለማካሄድ አይቻልም:: በዴሞክራሲ ስርዓት የሚካሄዱ ምርጫዎች ልዩ ባህርይ እንከን አልባ መሆናቸው ሳይሆን ለሚያጋጥሙ ጉድለቶች መከላከያና ማረሚያ ሆነው

የሚያገለግሉ ሕጋዊ ስርዓቶች በግልጽነትና ተጠያቂነት መርህ የተቋቋሙና በዚሁ መርህ መሠረት የሚሰሩ ተቋሞች መኖራቸው ነው፡፡ በዴሞክራሲ ስርዓቶች የሚካሄዱ ምርጫዎች ዋና ዓላማ የዜጎችን የሥልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት ማረጋገጥ እንጂ ለጭቆና አገዛዝ ሽፋን በመሆን የተሳሳተ ስዕል እንዲፈጠር ማድረግ አይደለም፡፡ ስለሆነም በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚካሄዱ ምርጫዎች ተቀባይነት ባገኙ የፖለቲካ ጨዋታ ሕጎች በጥብቅ በሚከበሩ የሥነ ምግባር ደንቦች የሚመሩ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት በብዙዎቹ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቶች ከምርጫ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚከሰቱ ችግሮች በተቻለ መጠን እንዲቀንሱ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ችግሮቹ ከተፈጠሩ ደግሞ መፍትሔ የሚያገኙበት የተደላደለ ሕጋዊ አማራጭ ተዘጋጅቶ በቦታው ላይ ይገኛል፡፡

ከምርጫ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚታዩ ጉድለቶችን ሙሉ በሙሉ መዘርዘር ባይቻልም ዋና ዋና ከሚባሉት መካከል ጥቂቶቹን መገምገም የችግሩን ባህርይ ለመረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ እስካሁን ካለው ልምድ በመነሳት የምርጫ ችግሮች በሶስት መሠረታዊ ነጥቦች ተጠቃለው ሊቀርቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት የመጀመሪያው ችግር የምርጫ ክልል በሚወሰንበት ጊዜ ለራስ ፓርቲ በሚጠቅምና ሌሎች ፓርቲዎችን በሚጎዳ መልኩ የሚፈፀመው ጉድለት (Gerry mandering) ነው፡፡ ይህ ጉድለት ለአካባቢ፣ ለክልልና ለብሔራዊ ምርጫ መወዳደሪያ የሚሆኑ የምርጫ ክልሎች ወይም ወረዳዎች በሚከለሉበት ጊዜ የራስን ፓርቲ አሸናፊነት በሚያስገኝ መንገድ እንዲከለሉ ማድረግንና የምርጫውን ውጤት ወደራስ ፓርቲ ጥቅም እንዲያዘነብል በሚያደርግ አኳኋን አስቀድሞ የተዛባ ስዕል መፍጠርን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ አይነቱ ጉድለት ጀሪ ማንደሪንግ የሚል ስያሜ የተሰጠው ለራሱ ፓርቲ ጥቅም ሲል እ.ኤ.አ በ1811 የማሳቹሴት አገረ ገዢ የነበረውና ኤልብሪጅ ጀሪ ተብሎ የሚታወቀው ሰው ፈጥሮት ከነበረው ሾጣጣ ቅርጽ ያለው የምርጫ ክልል በመነሳት ነው፡፡

በዴሞክራሲ ሥርዓቶች ውስጥ ሳይቀር የምርጫ ክልልን በመወሰን ረገድ ለራስ ፓርቲ አሸናፊነት የሚጠቅም እንዲሆን የማድረግ ዝንባሌ እንደሚታይ ባይካድም ይኸንን ዝንባሌ ለመቆጣጠርና ችግሩን ለመቀነስ የሚረዱ ግልፅ ዘዴዎች ተቀይሰው በስራ ላይ ውለዋል፡፡ በጥቅም ላይ ከዋሉት መከላከያ ዘዴዎች መካከል አንዱ የምርጫ ክልል በገለልተኛ አካል እንዲወሰን ማድረግ ነው፡፡ ዘዴዎቹ ከአገር አገር ቢለያዩም በሁሉም የዴሞክራሲ ሥርዓቶች የተጠቀሰውን የምርጫ ክልል አወሳሰን ችግር መከላከያ መንገዶች ተመቻችተዋል፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝ፣ የምርጫ ክልልን እንደገና የመወሰን ሥራ የሚካሄደው በነፃነትና በገለልተኝነት በሚሰሩ የወሰን (የድንበር) ኮሚሽነሮች ነው፡፡ በእርግጥ ኮሚሽነሮች ከወሰን አከላለል ጋር በተያያዘ የሚቀርቡትን የአፈፃፀም ሪፖርት ሥልጣን ላይ ያለው የመንግስት አስፈፃሚ አካል ለራሱ የሚስማማውን ጊዜ እየመረጠ ተግባራዊ እንዲሆን የማያደርግበት ሁኔታ ጨርሶ አልተወገደም፡፡ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው እ.ኤ.አ በ1970 ስለምርጫ ክልል አከፋፈል የቀረበውን የኮሚሽነሮች አስተያየት ለኮንሰርቫቲቭ ፓርቲ ሊጠቅምና የሌበሩን ፓርቲ ሊጎዳው ይችላል በሚል ስጋት ስልጣን ላይ የነበረው የሌበር ፓርቲ አገር ወስጥ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ጀምስ ቻላግሀን የአፈፃፀሙ ጊዜ እንዲዘገይ ያደረጉበት ሁኔታ ነው፡፡ የምርጫ ክልሎችን በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቶችም የሚጫወቱት በጣም ጠቃሚ ሚና አለ፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ እ.ኤ.አ ከ1962 ጀምሮ የምርጫ ክልሎችን በመወሰን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የእኩልነት ማረጋገጫ መመዘኛዎች የተለያዩ ቢሆኑም የኮንግረስ፣ የግዛቶችና የወረዳ ምርጫ ክልሎች እኩል መጠን እንዲኖራቸው የሚያስችል ውሣኔ በፍርድ ቤቶች ይሰጣል፡፡ የአሜሪካ ሕገመንግስት የሚጠይቀውን አንድ ሰው አንድ ድምፅ መርህ በጥብቅ በመተርጎም፣ ከ1962 በፊት ከገጠር ጋር ሲወዳደር ተገቢ ያልነበረውን አነስተኛ የከተሞች ውክልና በማስተካከል በተለይ ጥቁሮችንና ስፓኒሽ ተናጋሪ የሆኑ የከተማ ውስጥ አናሳዎችን በሚመለከት በሕግ አውጪው የነበረውን ተገቢ ያልሆነ አያያዝ በማስተካከል ፍ/ቤቶች የተጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የምርጫን ክልል ለራስ ፓርቲ እንደሚጠቅም አድርጎ የማደራጀት ችግር አሁንም ጨርሶ ተወግዷል የሚባል ባለመሆኑ የፍርድ ቤቶችን ትኩረት እንዳሳሰበ ነው፡፡ በተለይም ከቴክኒዎሎጂ ዕድገት ጋር ተያይዞ እየተስፋፋ የመጣውና በተራቀቀ ኮምፒዩተር የሚደገፈው የተዛባ የምርጫ ክልሎች አወሳሰን በተወዳዳሪዎች መካከል የሚፈጥረውን ተገቢ ያልሆነ የቁጥር መበላለጥ ለመከላከል የተራቀቀ ክትትልና ቁጥጥርን፣ እንዲሁም የፍርድ ቤቶችን ቀልጣፋ

ውሳኔ የሚጠይቅ ሆኗል፡፡ የዚህ አይነቱ ጉድለት ብዙውን ጊዜ ጎልቶ የሚከሰተው የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮች ነው፡፡ ምክንያቱም የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ዋነኛ ትኩረት ተመጣጣኝ ውክልና መፍጠር ሳይሆን በሆነ መንገድ የፓርላማ መቀመጫ አሸንፎ መያዝ እንደመሆኑ ለዚህ ዓላማ መሳካት የምርጫ ክልሎችን ለራስ ፓርቲ አሸናፊነት በሚያመች መንገድ መወሰን እንደአንድ ታክቲክ ስለሚቆጠር ነው፡፡

ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚታየው ሁለተኛው ችግር የምርጫን ውጤት በተለያዩ የማታለያ (Fraudulent) ዘዴዎችና ሕገወጥ (illicit) መንገዶች በማዛባት ወይንም በምርጫ ሂደት በስውርና ቅንነት በሌለው መንገድ ጣልቃ በመግባት (Under hand interference) የድምጽን ውጤት የመቆጣጠር (Ballot-rigging ) ችግር ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ጉድለት የሚመነጨው የተሳሳተ ውጤት ለራስ ፓርቲ በማስገኘት የምርጫ አሸናፊነትን በቅድሚያ ለማረጋገጥ በመፈለግ ከሚፈፀም ማጭበርበር ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተብራራው የድምፅ መስጫ ወረቀት (Ballot ) ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች ወይም ፓርቲዎች በሚያካሂዱት የምርጫ ውድድር መራጮች ለሚደግፉት ግለሰብ ወይም ፓርቲ ድምፅ የሚሰጡበት ነው፡፡ የድምፅ መስጫ ሣጥን (Ballot-Box) የሚባለው ደግሞ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበትን ወረቀት የሚያስገቡበት (የሚያስቀምጡበት) ነው፡፡ እንደሚታወቀው ብዙ አይነት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቶች ያለ ሲሆን በዘመናዊው ዴሞክራሲ ድምፅ አሰጣጥ በምስጢር መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ ከድምፅ ጋር የተያያዙ ማንኛቸውንም አይነት ሕገወጥ ጣልቃገብነቶች ለመከላከል የሚያስችል ውጤታማና ለአንድ ፓርቲ ወገንተኛ ያልሆነ አስፈፃሚ ተቋም መገንባት እንዳለበትም ተቀባይነት ያለው ነው፡፡

የዴሞክራሲ ስርዓቶች ድምፅን በልዩ ልዩ ሕገወጥ መንገድ በመቆጣጠር አሸናፊነትን በቅድሚያ ለማረጋገጥ የሚደረግን እንቅስቃሴ የሚከላከሉበት ዘዴ የምስጢር ድምፅ አሰጣጥን በስራ ላይ ማዋልና ለአንድ ፓርቲ ወገንተኛ ያልሆነ አስፈፃሚ አካል በማቋቋም ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ እንዲህ አይነቱን ሙስና ለማስወገድ ባደረጉት ብዙ አይነት የተቀነባበረ ጥረት በአብዛኛው ውጤታማ ሆነዋል፡፡ ከዚህ ጋር የተያያዙ ጉድለቶችን የሚጽያጋልጡ የነፃ ፕሬስ ተቋሞች፣ ገለልተኛ ታዛቢዎች ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የበጎ ፈቃድ ቡድኖች በሰፊው ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ጉድለቶች እንዲታረሙ ውጤታማ ተፅዕኖ መፍጠርም ይችላል፡፡ ከሁሉም በላይ ፍርድ ቤቶች የተዛባ ውጤትን በመሰረዝ፣ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ሙስና ውስጥ የገቡ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችንና ግለሰቦችን በሕጉ መሰረት በመቅጣት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

አየር ላንዶች «ብዙውን ጊዜ በትክክል የመረጠ ቀድሞ የመረጠ ነው» የሚሉት አባባል አላቸው፡፡ ይህ አባባል የድምጽን ውጤት ለራስ ፓርቲ እንደሚጠቅም ለማድረግ ሲባል በመራጮች መዝገብ ላይ ከተመዘገቡ በኋላ በሞቱና አካባቢያቸውን በለቀቁ ሰዎች ስም ሳይቀር ሕገወጥ ድምፅ መስጠትን የመሳሰሉ ሙስናዎች የሚፈፀሙት የድምፅ አሰጣጡ በሚጠናቀቅበት የመጨረሻዎቹ ሰዓታት ወስጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ከምርጫ ሂደት ጋር የተያያዘው ሶስተኛ ችግር የመራጮች ተሳትፎ መቀነስ እንደ ብቸኛ ምክንያት ማቅረብ አይቻልም፡፡ እንደገና ደግሞ የብዙ ሰው በምርጫ መሳተፍ በራሱ ጠንካራና ጤነኛ ዴሞክራሲ ለመኖሩ ማሳያ ምልክት ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው፡፡ ሕገመንግስታዊ አምባገነንነት በነገሰባቸው አገሮች ከ100% በላይ የሕዝብ ተሳትፎ መኖሩን በተለያየ ጊዜ የአለም ሕብረተሰብ መታዘብ ችሏል፡፡ የቀድሞዎቹ ምስራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገሮች ከ99% ያነሰ ተሳትፎ መኖርን እንደማይፈቅዱ በተደጋጋሚ ጊዜ በተግባር ማሳየታቸው የሚታወስ ነው፡፡ በምርጫ ተሳትፎ ማድረግ ብቻ የሕዝቡን ፖለቲካዊ ዓላማ የሚገልጽ እንዳልሆነ ሁሉ የብዙ ሕዝብ በምርጫ መሳተፍም ብቻውን የዴሞክራሲ መለኪያ ሊሆን አይችልም፡፡ የመራጩ ሕዝብ ተሳትፎ ትርጉም ያለውና የዴሞክራሲ ማሳያም ሊሆን የሚችለው በንቃትና በሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምርጫ ተሳትፎ መደረግ የቻለ እንደሆነ ነው፡፡ በእርግጥም በንቃትና በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚገኝ ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ ሲኖር ጠንካራና ጤነኛ ዴሞክራሲ ለመኖሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ በምዕራብ አውሮፓ አብዛኛዎቹ አገሮች ያለው የሕዝብ ተሳትፎ ለዚህ አባባል ጥሩ ማስረጃ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች እንዳመለከቱት በዚህ የአለማችን ክፍል የሚገኘው ሕዝብ ተሳትፎ ከፍተኛ ሲሆን ከ80 እስከ 90% የሚደርስ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ጠንካራ የሕዝብ ተሳትፎ በማስገደድ፣ በማዋከብና በተፅዕኖ የሚገኝ»ሳይሆን በመራጩ ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

በአንዳንድ የዴሞክራሲ ሥርዓቶች ደግሞ የሕዝብ ተሳትፎ በተለያዩ ምክንያቶች የመቀነስ አዝማሚያዎች አሳይቷል፡፡ በእነዚህ ሥርዓቶች የመምረጥ መብታቸውን በመጠቀም ረገድ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙት በትምህርት ያልገፉት፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸውና ስራ አጦች ናቸው፡፡ አብዛኞቹ መራጮች የሚሰጡት ድምጽ በምርጫና ውጤት ላይ ልዩነት አያመጣም ብለው ያስባሉ፡፡ ድምፅ ሰጡ አልሰጡ ነገሮች በነበሩበት መንገድ መቀጠላቸው አይቀርም የሚል ስሜት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ የትኛው ተወዳዳሪና ከየትኛው ፓርቲ ጋር ትስስር ያለው ዕጩ ተመረጠ የሚለው ጉዳይ የሚያሳስባቸውም አሉ፡፡ ነገር ግን ድምፃቸውን ለሚፈልጉት ተወዳዳሪ በመስጠት ልዩነት መፍጠር እንደሚችሉ ያለመገንዘብ ከባድ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ራሳቸውን ከፖለቲካ ተሳትፎ በማግለል ከዳር ቆመው መመልከትን ይመርጣሉ፡፡ ድምፅ አለመስጠትና በፖለቲካ አለመሳተፍ ውሳኔዎች በጥቂት ሰዎች አማካይነት እንዲወሰኑና ለውጦችም እጅግ የተጓተቱ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡ በምርጫና በፖለቲካ ተሳትፎ የሚታየው የፍላጎት ማጣት፣ ለመብት ያለመቆርቆርና አለማስተዋል የሚፈጥረው ውስብስብ ሁኔታ መኖሩ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ መሪዎች ካለሕዝብ ቁጥጥር እንዲገዙ በር መክፈቱ የማይቀር ነው፡፡ አንዳንዴ ከዚህም በከፋ ሁኔታ አምባገነን መሪዎች እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ለመራጩ ሕዝብ ተሳትፎ መቀነስ እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል የሚነሳው ሌላ ነጥብ የምርጫው ሥርዓት ዓይነትና የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀት ሥርዓት ነው፡፡ የምርጫ ሥርዓቱ የአብላጫ ድምፅ በሆነባቸው አገሮች የሚገኙ መራጮች የሚደግፏቸው አናሳ ፓርቲዎች ለማሸነፍ ያላቸው ዕድል አነስተኛ ስለሚሆን የሚሰጡት ድምፅ ዋጋ አልባ ሆኖ ይቀራል ከሚል ስጋት ተሳትፎ ከማድረግ ይቆጠባሉ፡፡ ምክንያቱም የዚህ አይነቱ ምርጫ ስርዓት የአብዛኛ ድምጽ ሳይሆን የአብላጫ ድምፅ በማግኘት የፓርላማ መቀመጫ የሚይዝበት በመሆኑና ለውክልና መመጣጠን ትኩረት የማይሰጥ በመሆኑ ነው፡፡ የፓርቲው ስርዓት የአንድ ወይም የነጠላ ፓርቲ ስርዓት ከሆነ ደግሞ ውድድሩ በተለያዩ ፓርቲዎች መካከል ሳይሆን በአንድ ፓርቲ ዕጩዎች መካከል የሚደረግ የእርስ በርስ ውድድር ስለሚሆን የተለያየ አመለካከት ያላቸው መራጮች አመለካከታቸውን የሚወክል ፓርቲ ባለመወዳደሩ ተስፋ ይቆርጡና ተሳትፎ ማድረጉን ይተዉታል፡፡ ባለሁለት ፓርቲ ሥርዓትም እንደዚሁ በሁለት ፓርቲዎች መካከል ብቻ የሚደረግና የሶስተኛ ፓርቲዎችን መኖር የሚገድብ ሥርዓት ስለሆነ፣ የዚህ ዓይነት የፓርቲ ስርዓት ያላቸው አገሮች የሚጠቀሙበት የምርጫ ሥርዓት ደግሞ የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ስለሆነ መራጮችን ለተሳትፎ የሚያደፋፍር አይደለም፡፡

የመራጮችን ተሳትፎ የሚቀንስ ሌላ ነጥብ ዜጎች በመንግስት አደረጃጀትና አሰራር ደስተኞች የማይሆኑበት ሁኔታ ሲፈጠርና ፓርቲዎች በቀየሷቸው ፕሮግራሞች ላይ ተቃራኒ ዝንባሌ ሲኖራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ውስጥ ለሚታየው የመራጮች ተሳትፎ መቀነስ ይኸ ምክንያት አንደኛው እንደሆነ በጥናት ተደርሶበታል፡፡ የአሜሪካ ዜጎች በፌዴራል መንግስቱና በማህበራዊ ፕሮግራሞቹ ላይ ተቃራኒ ዝንባሌዎች አሏቸው፡፡ ከፊሎቹ አሜሪካዊያን ለሰው ልጅ ማህበራዊ አገልግሎት የሚመደበው ከቀረጥ የሚገኝ ገንዘብ አጠቃቀም ደካማ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የኢኮኖሚ አቅማቸው ለማይፈቅድላቸው ሰዎች የሕክምና፣ የሕግና የመሳሰሉት የድጋፍ አገልግሎቶች በፌዴራሉ መንግስት በበቂ ሁኔታ እንዲሟላ ማድረግ ተገቢ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ የተወሰኑት እንዲሁ የዜጎችን ኤኮኖሚያዊ ሕይወትዎም በመወሰን ረገድ መንግስት ከሚገባ በላይ እየሄደ ነው ብለው ሲያማርሩ ሌሎች ከዚህ በተለየ መንገድ መንግስት ሁሉም ዜጎች ጥሩ የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅበታል ይላሉ፡፡ አብዛኞቹ በትምህርት፣ በገቢ መጠንና በሥራ ኃላፊነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ጨምሮ ፌዴራል መንግስቱ የተቸገሩትን በመርዳት ብዙ አልተራመደም የሚል ቅሬታ አላቸው፡፡ በመንግስትና ፓርቲዎች ላይ ያለው እንዲህ ዓይነት ተጻራሪ ዝንባሌ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተቀናጀና የተጠና ርዕዮተዓለማዊ አቋም በማዳበር ፈንታ አንዴ በዚህኛው ሌላ ጊዜ ደግሞ በዚያኛው ዝንባሌ እየተሳቡ የሚዋልሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ መራጩም የትኛውን ፓርቲ ደግፎ የትኛውን መተው እንደሚገባው ለመምረጥ የሚቸገርበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ከተሳትፎ ይቆጠባል፡፡

ሌላው የምርጫ ተሳትፎን የሚቀንስ ምክንያት ከመራጩ ሕዝብ ውስጥ ራሳቸውን ከማንኛውም ፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ አድርገው የሚመለከቱ ዜጎች መጠን እያደገ መምጣቱ ነው፡፡ ከማንኛውም ፓርቲ ወገንተኛ ላለመሆን የሚፈልጉበት ሁኔታ መኖሩ ራሱ አከራካሪ ቢሆንም

ከፖለቲካ ተሳትፎ ገለልተኛ ለመሆን መፈለግ ጤናማ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ከፓርቲ ጋር ያለ ትስስር መላላት በምርጫ ሂደት የተረጋጋ ሁኔታ እንዳይፈጠር ማድረጉ የማይቀር ነው፡፡ ምክንያቱም ከፓርቲ ጋር ትስስር የሌላቸው ሰዎች ዕለታዊና አላፊ በሆኑ ጊዜያዊ ክስተቶች በቀላሉ ለመሳብ ከማንም በላይ የተመቻቹ ስለሚሆኑ ነው፡፡ ለፓርቲዎች ያለ ታማኝነት ሲሸረሸር የምርጫ ሂደት አለመረጋጋትን ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው የፓርቲ ሥርዓት እየወደቀ መምጣቱን የሚያበስር ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ውጤት ደግሞ ከራሱ ከዴሞክራሲ ውድቀት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡ ፓርቲዎች ከሌሉ በፈቃደኛ ቡድኖችና (Interest groups) በመራጩ ሕዝብ በተመረጡ ባለሥልጣኖች መካከል ነፃ የወሰነ ክልል አይኖርም፡፡ በዚህም የተነሳ ጥቂቱን የሕብረተሰብ ክፍል ብቻ የሚወክሉ የፈቃደኛ ቡድኖች የመንግሥትን ፖሊሲ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ዕድል ያገኛሉ፡፡ በእርግጥ ብዙዎቹ ከወገንተኝነት ነፃ ነን ባዮች ሙሉ በሙሉ ነፃ ለመሆናቸው መተማመኛ ሊኖር አይችልም፡፡ ዋናው ነገር ገለልተኛ ከመሆን ይልቅ የሚመርጡትን ፓርቲ ለይቶ መደገፍ፣ በምርጫና በአጠቃላይ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ማድረግ ለዴሞክራሲ ስርዓት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡

ከዚህ ሌላ ለመራጮች ተሳትፎ መቀነሰ እንደምክንያት የሚጠቀሰው በአንዳንድ አገሮች የሚያጋጥመው የመረጃ ፍሰት ችግር፣ የምርጫ ስራ ካለው ውስብስብነትና አሻሚነት የሚከሰት ጥላቻ፣ የተወሳሰቡ አሰራሮችን ለመረዳትና ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም እጥረት የመሳሰሉት ቴክኒካዊ ችግሮች መኖራቸው ነው፡፡ ይኸንንና ቀደም ሲል የተነሱትን ችግሮች ለመከላከልና ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት የመገናኛ ብዙሃን የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ነው፡ በዴሞክራሲ ስርዓቶች የእነዚህ ተቋሞች ኃላፊነት እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እንደውም ቀደም ሲል የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥራ ተደርጎ ይቆጠር የነበረውን የምርጫ ተግባር አሁን እነርሱ ተክተው የሚሠሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ምርጫው በምን አይነት መንገድ ሊካሄድ እንደሚችል ቅድሚያ ትንበያ ያደርጋሉ፡፡ የምርጫውን ሂደትና አጠቃላይ ሥርዓት የሚመለከቱ መረጃዎችን በተቀናጀና ተከታታይ በሆነ መንገድ ለሕዝቡ ያሰራጫሉ፡፡ ስለተወዳዳሪ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ምንነትና ማንነት የተሟላ መረጃ ለሕዝብ ያቀርባሉ፡፡ ለውድድር የቀረቡትን ፓርቲዎችና ግለሰቦች የኋላ ታሪክ፣ ድክመትና ጥንካሬ፣ ለረጅም ጊዜ ተደብቀው የቆዩና በምስጢር የተያዙ መረጃዎችን ሳይቀር ለሕዝብ ይፋ ያደርጋሉ፡፡ ዜጎች ቅሬታቸውን ለሚያሰሙባቸው ጉዳዮች ተጠያቂና ኃላፊው ማን እንደሆነ፣ በልዩ ልዩ መስክ ከሚንፀባረቁ ችግሮች መውጫው መንገድ ምን ሊሆን እንደሚችል በበቂ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ትንተናዎችንና ዜናዎችን ያቀርባሉ፡፡ በዚህ ላይ ተመስርተው መራጮች ጠንካራ ተሳትፎ ለማድረግ ይደፋፈራሉ፡፡ መጥፎውን ከጥሩው ለይቶ ለመምረጥ የሚረዳ መነሻ ያገኛሉ፡፡

ከምርጫ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቀነስ በዴሞክራሲ ስርዓት ከሚሰራባቸው የመፍትሔ አማራጮች መካከል የዜግነት ትምህርት አንዱ ነው፡፡ ዜጎች በምርጫና በአጠቃላይ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ተሳትፎ የማያደርጉት የአዕምሮ ጉድለትና የፍላጎት ማጣት ስላላቸው ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የምርጫ ተግባር በጣም ጥልቅና ስውር እየሆነ በመምጣቱ እንዲሁም ስራ ላይ የሚውልበት ዘዴ የተወሳሰበም በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በዜጎች የሚታየው ዝንባሌ እንደፈለጉ ያድርጉት በሚል ጉዳዩን ለተወሰኑ ክፍሎች በመተውና በእነዚህ ጥቂት ሰዎች የሚወሰደውን እርምጃ እየተቀበሉ በማጽደቅ ለመገዛት የመስማማት ወይም የመፍቀድ ዝንባሌ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ራስን ለተገዥነት የማመቻቸትና የሚገባውን ተሳትፎ ያለማድረግ ስር የሰደደ ዝንባሌ በአጭር ጊዜና በቀላሉ የሚወገድ ባለመሆኑ በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ተካቶ በተከታታይ መንገድ የሚሰጥ የዜግነት ትምህርት አስፈላጊ መሆኑ በብዙ አገሮች በሚገባ ስለታመነበት በሰፊው ይሰራበታል፡፡ በምርጫ መሳተፍ በቸልታ ሊታለፍ የማይገባ ጠቃሚና መሰረታዊ መብት መሆኑን ዜጎች እንዲማሩ ይደረጋል፡፡

ይኸንን ርዕስ ለማጠቃለል ጥቂት ሃሳቦችን እንደገና በአጭሩ መድገም ያስፈልጋል፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚካሄዱ ምርጫዎች ፈጽሞ እንከን የማይገኝባቸው እንዳልሆኑ መረዳት ጠ ቃሚ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዴሞክራሲ ስርዓት የሚካሄዱ ምርጫዎች ያሉባቸውን ችግሮች ለመከላከልም ሆነ ለመቀነስ የሚያስችሉ ግልጽ የመፍትሔ አማራጮችና ዘዴዎች በተፈለገው ጊዜና በተፈለገው ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆናቸው መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ የመፍትሔ አማራጮችና ዘዴዎች እንደችግሩ ባህርይ፣ እንደየአገሩ አደረጃጀትና አቅም የሚለያዩበት ሁኔታ ቢኖርም በመርህ ደረጃ ተቋማዊ መፍትሔ (Institutttional solution) በማስገኘት፣

የተደራጀ ሥርዓት (Organized system) በመዘርጋት ግልጽነትና ተጠያቂነትን (Transparency and accountability) በማስፈንና የሕግ የበላይነትን (Rule of law) በማክበር ላይ ተመስርተው የሚፈፀሙ ናቸው። በመሆኑም ከምርጫ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቀነስ ለአንድ ፓርቲ የማይወግን የምርጫ አፈፃፀም ተቋም፣ የምርጫ ክልል ወሰኝ ኮሚሽን፣ ፍርድ ቤት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የዜግነት ትምህርትና ነፃ ታዛቢዎች በሚገባ ጥቅም ላይ ይውላሉ። እነዚህ ተቋሞች አሰራራቸውን የሚገዙበትና ተወዳዳሪ ፓርቲዎችም ሆኑ ግለሰቦች የሚመሩበት የሥነ ምግባር ደንብ (code of conduct) ወጥቶ ተግባራዊ ይሆናል። በዴሞክራሲ ሥርዓቶች የሚካሄድ ምርጫ እነዚን መርሆዎችና የዴሞራሲያዊ ፖለቲካ ጨዋታ ሕጎች ተከትሎ የሚከናወን በመሆኑ የእውነተኛ ዴሞክራሲ መኖር መገለጫና የዜጎች መብት ማረጋገጫ ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል።

# 1.10 ከምርጫ ሌላ የዜጎች ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚገለጥባቸው ዘዴዎች

በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚካሄድ ምርጫ ሕዝቡ የመንግሥትን ሥልጣን ውክልና የሚረከቡ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲመርጥ ማስቻሉና በራሱ ውሳኔ ኃላፊነት መስጠቱ ብቻ ሕዝቡ በፖለቲካ ጉዳይ ጠቃሚ ሚና እንዲኖረው አያስችልም። ወይም በተከታታይ ምርጫዎች ተወካዮችን መምረጥና ሥልጣን ላይ ስለተቀመጡት ተወካዮቹ ተግባር አስተያየት ማቅረብ ብቻ አጠቃላይ ሕዝቡ በፖለቲካ ጉዳይ ጠቃሚ ሚና እንዲጫወት አያስችሉትም። ስለዚህም በብዙዎቹ የዴሞክራሲ ሥርዓቶች ውስጥ ዜጎች በፖሊሲ ማውጣት ሥራ ቋሚ ሚና እንዲጫወቱ የሚያግዙ ሌሎች በርካታ ዘዴዎች በሥራ ላይ ውለዋል። ከእነዚህም መካከል ግፊት-አድራጊ[4] ቡድኖችን ማቋቋም፣ ከፓርላማ በተጨማሪ በሚከናወን ፖለቲካዊ ሥራ መሳተፍ፣ የምክክርና ተሳትፎ መድረኮችን ማስፋት፣ በውሳኔ ሕዝብ ወይም ቀጥተኛ ዴሞክራሲ መጠቀም፣ ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ውሣኔ ላይ መሳተፍ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የግፊት መስጫ ቡድኖች መራጩ ሕዝብ በፖሊሲ አወጣጥ ሂደት ተፅዕኖ የማሳረፍ ዕድል እንዲያገኝ ያስችሉታል። የግፊት መስጫ ቡድኖች በተለያዩ ቡድኖች መካከል ጠቃሚ ውይይትና ድርድር እንዲኖር ያደርጋሉ። በእንዲህ አይነቱ ውይይትና ድርድር ላይ የተመመረተ ፖሊሲ መቅረፅ ሕብረ ብሔራዊ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሁነኛ ገፅታዎች ናቸው።

በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ ሕግ አውጪ አካል በመደበኛ ተግባሩ ከሚያሳልፈው የፖለቲካ ውሣኔ በተጨማሪ በመራጩ ሕዝብ በቀጥታ የሚከናወን አማራጭ ተግባርም አለ። ይህ ከፓርላማ በተጨማሪ የሚከናወን ሥራ በተለያየ ዘዴ በመንግሥት ውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ተፅዕኖ ለማድረግ የሚፈልጉ ዜጎች በቡድን እየሆኑ የሚያካሂዱትን ጥረት የሚያጠቃልል ነው። ለምሳሌ ሠላማዊ ሠልፍ ማካሄድ፣ የሥራ ማቆም አድማ፣ የሲቪል እምቢተኝነትን ማሳየትና የመሳሰሉት ዘዴዎች ከፓርላማ በተጨማሪ ከሚከናወኑ ሥራዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ከግፊት መስጫ ቡድኖችና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ ዘዴዎች በተለመደው መስመር ከሚደረገው የፓርላማ ፖለቲካዊ ተግባር የተለየ አማራጭ የሚያስገኙ ናቸው። ዜጎች በእነዚህ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች መሣተፍ መቻላቸው የዴሞክራሲ ሥርዓት ጠቃሚ ባህርያት ሲሆኑ በተወሰነ ወቅት በሚከናወን ምርጫ ድምጽ በመስጠት ከሚደረግ ተሳትፎ ባሻገር በአገራቸው መንግሥት ተግባር ውስጥ ራሣቸው እንዲሳተፉና የራሳቸውን ጥቅም የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ሲኖሩ ተፅዕኖ ለማሳረፍ ያስችላቸዋል። ከፓርላማ ፖለቲካ በተጨማሪ የሚካሄዱ ጥረቶች የአናሳዎችን ፍላጎቶች በማንፀባረቅ ለምሳሌ የሴቶችን፣ የአካባቢ ጥበቃንና የመሳሳሉትን ጉዳዮች የፖለቲካ አጀንዳ እንዲሆኑ አጉልቶ ለማንፀባረቅ የሚረዱ ናቸው።

የሕብረተሰቡ አባላት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አስተያየት ለፖሊሲ አውጭዎች የሚገልጹበትና በፖሊሲ ቀረፃ ወቅት ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያደርጉበት መንገድ አላቸው። ከእነዚህ የተለያዩ ዘዴዎች መካከል ምክክርና ተሳትፎ ማድረግ ይገኙበታል። ምክክር የሚለው ቁምነገር የመደመጥን መብት የሚመለከት ነው። ዜጎች በተወሰነ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን

[4] *ግፊት-አድራጊ ቡድኖች* = Pressure Groups

እንዲገልፁ በፖሊሲ አውጭዎች ይጋበዛሉ። ፖሊሲ አውጭዎችም ከዜጎች የሚቀርቡ ሃሳቦችን ያዳምጣሉ። ጠቃሚ ሆኖ የተገኘውን የፖሊሲ አካል ያደርጉታል። ተሳትፎ የሚለው ነገር ደግሞ በሕዝብና በፖሊሲ አውጭዎች መካከል ያለውን የኃይል ግንኙነት የሚቀይር እንቅስቃሴ ነው። ይኸውም ፖሊሲ ማውጣት የመንግሥት ሥራ ብቻ ሳይሆን የመንግሥትና የሕዝብ የጋራ ተግባር እንዲሆን የሚያደርግ ነው።

ምክክርና ተሣትፎ የሕዝቡ የፖሊሲ አማራጮች ትኩረት እንዲሰጣቸው ወይም ተቀባይነት እንዲያገኙ የሚረዱ በመሆናቸው በዴሞክራሲ ሥርዓቶች ውስጥ እንደትልቅ ነገር የሚታዩ ናቸው። በእርግጥ ሕዝቡ በሚያጋጥመው የመረጃ እጥረት ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማድረግ ስለሚቸገር ፖሊሲ አውጭዎች የሚያቀርቧቸውን አወዛጋቢ የፖሊሲ ሃሳቦች እንዲደግፍ ግፊት የሚደረግበት አሠራር ጨርሶ አንዳልተወገደ መካድ አይቻልም።

ከምክክርና ተሳትፎ ተለይቶ የማይታየውና በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የዜጎች አስተዋፅኦ የሚገኝበት ሌላው መንገድ ሕዝበ-ውሣኔ ነው። የውሣኔ ሕዝብ ዋነኛው ጥቅም ወሣኝ በሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጠቅላላው ሕዝብ ውሣኔ በመስጠት በቀጥታ እንዲሳተፍ ማስቻል ነው። ውሣኔ ሕዝብ በፖሊሲ አወጣጥ የብዙሃኑ ሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖር የሚያስችል በመሆኑ በባሕሪው ቀጥተኛ ዴሞክራሲ ነው። የተለያዩ የውሣኔ-ሕዝብ መልኮች ያሉ ሲሆን፣ ለምሳሌ ቀደም ሲል በመንግሥት የተወሰዱ እርምጃዎችና የቀረቡ የጉዞ አቅጣጫዎች ድጋፍ የሚያገኙ ብትን ዕድል ለመፍጠር ውሣኔ ሕዝብ ሊካሄድ ይችላል። ወይም ደግሞ ዜጎች የዕለት ከዕለት ሕይወታቸውን በሚወስኑ ጉዳዮች ላይ መስማማት አለመስማማታቸውን ራሳቸው እንዲወስኑ ስለሚያስችል መንግሥታት የሕዝቡን አስተያየት በትክክል ለማንፀባረቅ ያላቸውን ችግርና በዚህም ሳቢያ የሚፈጠረውን አደጋ ለማስቀረት ውሣኔ ሕዝብ ሊካሄድ ይችላል። ፖሊሲ አውጭዎች ሕዝቡን የሚመለከቱ የፖሊሲ ይዘቶችን ለመወሰን ያላቸው ኃይል እንዲቀንስና የሕዝቡን አስተያየት በትክክል የሚያንፀባርቁ የተግባር አቅጣጫዎችን እንዲከተሉ ለማድረግ ውሣኔ ሕዝብ ትልቅ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል። ውሣኔ ሕዝብ አንድም እንደምክር ማግኛ አሊያም እንደሕጋዊ የሕዝብ ድጋፍ ማግኛ በመሆን መንግሥታትን ያገለግላል።

ውሳኔ ሕዝብ ለማድረግ የሚያስችል ሃሳብ ማመንጨት የመንግሥት ሥልጣን የያዙ ሰዎች ብቻ ኃላፊነት አድርጎ የመመልከት ችግር ብዙ ጊዜ ይከሰታል። ውሣኔ ሕዝብ ዜጎች በፖሊሲ አወጣጥ ያላቸውን ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚረጋግጡበት መንገድ የሚሆነው ሕዝቡ ራሱ የውሣኔ ሀሣብ ሲያፈልቅና በይዘቱም ላይ ቁጥጥር ሊኖረው ከቻለ ብቻ ነው። ፓርላማዎችና የሕገ መንግሥት ም/ቤቶች ብቻ ሳይሆኑ ዜጎችም የውሳኔ ሕዝብ ሃሳብ የማመንጨት መብት ሲኖራቸው የውሳኔ ሕዝብን አምባገነኖች ሥልጣናቸውን ለማጠናከር ዓላማ እንደፈለጉ እንዳይጠቀሙበት ለመቆጣጠር ያስችላል። ሒትለር ወደሥልጣን ከመጣ በኋላ ሕጋዊነትና ተቀባይነት እንዳለው ለማሳየት ውሳኔ ሕዝብን እንደተጠቀመበት ይታወሳል።

# 2. ምርጫ በኢትዮጵያ

## 2.1 መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለዴሞክራሲ ምርጫ እየሰበኩ በዴሞክራሲ ላይ ደባ መሥራት የተጀመረው ከአሁኑ አገዛዝ በፊት በነበሩት መንግሥታት ነው። ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ በደርግና በአሁኑ አገዛዝ ዘመን የተካሄዱ ምርጫዎች ሁሉም የጋራ ባሕሪይ አላቸው። በሦስቱም መንግሥታት የተካሄዱ ምርጫዎች በየትኛውም ዴሞክራሲ በሌለበት አገር እንደሚደረገው ሁሉ የጭቆና አገዛዝን ትክክለኛ ገጽታ ለመደበቅና በሕዝብ ድጋፍ የቆመ ለማስመሰል ሲባል የተደረጉ ናቸው። በሦስቱም መንግሥታት የተካሄዱ ምርጫዎች የዜጎችን ነጻ ተሳትፎ መሠረት ያደረጉ ሳይሆኑ በተለያዩ ተፅዕኖዎች ታጅበው በኃይልና በግዴታ ጭምር የተካሄዱ ናቸው። በዜጎች የምርጫ ውሣኔ ለመገዛትና የዜጎችን ፍላጎት ጠብቆ ለመሥራት ታስበው የተካሄዱ ሳይሆኑ ከሕዝብ ፈቃድ ውጭ የያዙትን ሥልጣን ጠብቆ ለማቆየት የሚያገለግል እርዳታና ብድር የሚሰጧቸውን የውጭ ኃይሎች ድጋፍ ላለማጣትና በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ መገለል እንዳይደርስባቸው ለመከላከል የተደረጉ የምርጫ ቲያትሮች ነበሩ።

ባለፉት ሁለት አገዛዞች የተካሄዱትን ምርጫዎች ትተን በአሁኑ አገዛዝ ሥር የተካሄዱ ምርጫዎችን በተሻለ ጥልቀት ለመረዳት ብንሞክር አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል ድባብ እንዳልተፈጠረ በሚገባ መገንዘብ ይቻላል:: የአሁኑ አገዛዝ ከመነሻው ወደሥልጣን መንበር የተንጠላጠለው በሕዝብ ፈቃድ ሳይሆን በጠመንጃ እንደመሆኑ በመራጩ ሕዝብ የነቃ ተሳትፎ ላይ ተመሥርቶ ለሚከናወን ነፃ ምርጫም ሆነ በዚህ ዓይነቱ ዴሞክራሲያዊ አግባብ በውክልና ለሚይያዝ የመንግሥት ሥልጣን ከፍ ያለ ግምት የሚሰጥና አክብሮት ያለው አይደለም:: ለነፃ ምርጫ ከፍተኛ ዋጋ እንዲሰጥም ሆነ አክብሮት እንዲያሳይ ተፈጥሯዊ ባሕሪይውና ታሪካዊ አመጣጡ አይፈቅዱለትም:: ሥልጣንን በጠመንጃ ኃይል ማግኘ ት የቻለ እንደመሆኑ አመጣጡና የኋላ ታሪኩ የሥልጣን ምንጭ ሕዝብ ነው በሚለው የዴሞክራሲ መርህ ለመዳኘት እንዳይችል ከፍተኛ የአስተሳሰብ ጫና አሳድረውበታል:: በዚህም ምክንያት ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በማድረግ ፋንታ ሸፍጥና የፖለቲካ ሴራ በማካሄድ በሥልጣን ላይ መቆየትን ቀዳሚ ምርጫው አድርጓል::

የሕወሓት አገዛዝ በአገሪቱ ከተተከለ በኋላ በሕዝብ ምርጫ ስም የሚካሄደው ትዕይንት የመጀመሪያ ምዕራፍ የተከፈተው በየካቲት ወር 1984 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 1992 ዓ.ም) ከተካሄደው የቀበሌና የክልል ምርጫ ጋር ተያይዞ ነው:: የሕወሓትና እጩዎች የሕወሓት ተወዳድረው የሕወሓት ያሸነፈበት የመጀመሪያው አስቂኝ የምርጫ ተውኔት ሆኖ ተዘጋ::

ከዚህ በኋላ 1986 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1994 ዓ.ም) የሕገ-መንግስት ጉባዔ አባላት ለመምረጥ በሚል የተካሄደው የማስመሰል ተግባር ሌላው በምርጫ ስም የተሠራ አሳፋሪ ትዕይንት ነበር:: ይኸም ትዕይንት በ1992 እንደተደረገው ሁሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ካድሬ እርስ በርሱ እየተመራረጠ የሕዝብ ውክልና አገኘሁ በሚል ከየቦታው ተጠራርቶ አዲስ አበባ ላይ «የሕገ-መንግሥት ጉባዔ» ስብሰባ እንዲከፍት መነሻ ሆነ:: ከጥቅምት 17 ቀን እስከ ሕዳር 29 ቀን 1987 ከአንድ ወር በላይ አዲስ አበባ ውስጥ ሲመክር የሰነበተው የሕወሓት ሕገ-መንግሥት ጉባዔ ይኸው የፖለቲካ ቡድን የድርጅቱ ፕሮግራም ዓላማዎች አድርጎ የሚያራምዳቸውን መርሆዎች ሕገ-መንግሥታዊ ቅርፅ በመስጠት የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ-መንግሥት ዋነኛ ይዘት እንዲሆኑ አድርጎ አፀደቃቸው::

ሕገ-መንግሥቱን አፀደቀ የሚባለውን ጉባዔ አባላት መልምሎ ያቀረበ፣ እነዚህን አባላት ለማስመረጥ የሚያስችለውን የምርጫ ሕግ አውጥቶ ያወጀና ሥራውን በኃላፊነት የሚያካሂድ የምርጫ አስፈፃሚ ያቋቋመ፣ ይኸው ሕዝባዊ ውክልናና ሕጋዊ መሠረት የሌለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ነበር:: የሕገ-መንግሥት ጉባዔውን አባላት ለማስመረጥ በተቋቋመው የምርጫ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ውስጥ ከላይ እስከታች የተመደቡትን አስፈፃሚዎች መልምሎ ያሠማራና ይቆጣጠር የነበረው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለዚህ ተግባር ከተሠማሩት መካል በዝቅተኛ የስሌት መጠን ከ99 ከመቶ በላይ የሆኑት የሕወሓት/ኢሕአዴግ የፖለቲካ ካድሬዎችና አባላት ነበሩ::

ከሕገ-መንግሥቱ መፅደቅ በኋላ በ1987 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ1995) የተካሄደውን የፌዴራልና የክልል ምርጫ እንዲያስፈጽም የሽግግር መንግሥቱ በሕገ-መንግሥት ጉባዔው ሥልጣን ተሰጥቶታል ስለተባለ ቀደም ሲል ለሕገ-መንግሥት ጉባዔ ምርጫ አቋቁሞት የነበረውን የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም በአዲስ አዋጅ አጠናክሮ በማቋቋም ለዚህ ምርጫ አስፈፃሚ አካል አደረገው::

የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት ጋር ለማጣጣም የወጣው አዋጅ ቁጥር 111/1987 ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለተተኪው አካል (የተተካው አካል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞራሲያዊ ሪፑብሊክ ነው) የሆነ ብሔራዊ ምርጫ ተብዬዎችን እያስፈፀመ የሚገኘ ው ምንም ዓይነት የሕዝብ ውክልናና የሕዝባዊነት መሠረት የሌለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት በተጠቀሰው አዋጅ ያቋቋመው የምርጫ ቦርድ ነው:: እ.ኤ.አ በ2000 የተካሄደውን የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫና በ2001 የተካሄደውን የወረዳ ምርጫ ያስፈፀመውም በተጠቀሰው መንገድ የተቋቋመው የምርጫ ቦርድ ነው::

እስካሁን በሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ዘመን የተካሄዱትን ምርጫዎች ለመታዘብ የቻሉ የውስጥና የውጭ ታዛቢዎች የሰጡት ምስክርነት ቢኖር ከተከናወኑት ምርጫዎች መካከል

አንዳቸውም የነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መርሆዎችን ተከትለው ያልተፈፀሙ መሆናቸውን ነው። በሌላ አገላለጽ ሁሉም ምርጫዎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫዎች አልነበሩም የሚል ነው። ተጨባጩ ዕውነታ ይህ ከሆነ መመለስ የሚገባው ጥያቄ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ ምርጫዎች ዋና ዋና ችግሮች ምንድን ናቸው? መፍትሔዎቹስ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆን ሃሳብ ለማቅረብ የኢትዮጵያን የምርጫ ችግሮች በሦስት መሠረታዊ ክፍሎች በመክፈል ለማየት ይቻላል። እነዚህም አንደኛ ከአደረጃጀት ጋር የተያያዙ ወይም መዋቅራዊ ችግሮች፣ ሁለተኛ የምርጫ ሥርዓት ችግሮች፣ ሦስተኛ የአሠራርና አፈፃፀም ችግሮች ናቸው።

## 2.2 የአደረጃጀት ወይም መዋቅራዊ ችግሮች

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱ ምርጫዎች ያሉባቸው ችግሮች በመጀመሪያ ደረጃ የሚመነጩት በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኘው ፖለቲካዊ አደረጃጀት ነው። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፖለቲካዊ አደረጃጀት በተግባር የብዙሃን ፓርቲ መኖርን የሚገድብ፣ ለአንድ የፖለቲካ ቡድን ገናና (ዶሚናንት) ሆኖ መውጣት የሚያግዝ፣ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መፈጠር አስፈላጊ የሆነው ንቁና የተሟላ የሕዝብ ተሳትፎ እንዳይኖር በሚያደርጉ አያሌ መሰናክሎች የታጠረ ነው። ሕገ-መንግሥቱ ራሱ የፖለቲካ ሥልጣን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የአስፈጻሚው አካል በተለይም የጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን አድርጎ በመደንገጉ በምርጫ አሸንፎ የመንግሥት ሥልጣን የሚይዝ አንደ ፓርቲ የሚያቋቁመው መንግሥት እስከፈለገው ድረስ በሥልጣን እንዲባልግ እድሉን ክፍት አድርጎ የሚሰጥ ነው።

በመንግሥት ልዩ ልዩ የሥልጣን አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ ሕግ-አስፈፃሚውና ሕግ-ተርጓሚው መካከል ትርጉም ያለው የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር ባለማድረጉ፣ በተለይም አስፈፃሚው አካል በሕግ-አውጭውና በሕግ-ተርጓሚው ላይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከፍተኛ ተፅዕኖ ለማሳረፍ የሚያስችለው ሙሉ ሥልጣን እንዲኖረው ሆኖ በመደንገጉ፤ አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበት አደረጃጀት አልተፈጠረም። ሕግ-አውጭውና ሕግ-ተርጓሚው ነፃ አካላት ሳይሆኑ የሕግ-አስፈፃሚውን ውሳኔዎች ሕጋዊ ቅርጽ ለማስያዝ በሚያስችል መሣሪያነት እንዲያገለግሉትና እንዲታዘዙት ብቻ የሚያደርግ ደካማ ሥልጣን ነው ያላቸው። ይህ አባባል ግልጽ ሊሆን የሚችለው ስለተወካዮች ምክር ቤት አባላት አመራረጥ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት ባሕሪይ መረዳት ከተቻለ ነው። በዚህ የምርጫ ሥርዓት መሠረት የብዙሃን ፓርቲ ፖለቲካ አሠራር የሚኖርበት ዕድል የመነመነ በመሆኑና በድምጽ ብልጫ የሚያሸንፍ አንድ ገናና ፓርቲ በምክር ቤቱ ውስጥ አብዛኛውን መቀመጫ መያዙ ስለማይቀር ጉዳዩ ሁሉ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ውስጥ ይገባል። በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 56 ስለፖለቲካ ሥልጣን በተደነገገው መሠረት በምክር ቤቱ መቀመጫ ያገኙ ጣምራ ድርጅቶች የፌደራሉን መንግሥት ሕግ-አስፈጻሚ እንደሚያደራጁና እንደሚመሩ ቢደነገግም የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት ደግሞ በባሕሪይው የጣምራ መንግሥት እንዳይኖር የሚገድብ በመሆኑ ዞሮ ዞሮ ሕግ-አስፈፃሚውን የማደራጀቱና የመምራቱ ኃላፊነት በአንድ ፓርቲ ላይ ይወድቃል።

በተመሳሳይ መንገድ የሕግ-አስፈጻሚውን አካል ስለሚመራው ጠቅላይ ሚኒስትር አሰያየም በሚመለከት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ቢኖሩም የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ሥልጣን በአንድ የፖለቲካ ድርጅት እንዲሰባሰብ የሚፈቅድ በመሆኑ የመንግሥት ሥልጣንን ትርጉም ባለው መንገድ የሚጋሩ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊኖሩ አይችሉም። ስለሆነም አብላጫ ድምፅ ያገኘ አንድ ፓርቲ የመንግሥት ሥልጣንን ይረከባል። ሥልጣን የሚረከብ የፖለቲካ ድርጅት ደግሞ የሕግ-አስፈፃሚውን አካል የሚያቋቁምና የሚመራ እንደመሆኑ ዞሮ ዞሮ ሥልጣን በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ቁጥጥር ሥር ይወድቃል ማለት ነው። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የምክር ቤቱን አብላጫ መቀመጫ በያዘበት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ከዚሁ አብላጫ መቀመጫ ከያዘ ፓርቲ በሚሰየምበት፣ ይኸው ፓርቲ የመንግሥትን ሕግ-አስፈጻሚ አካል በሚያቋቁምበትና በሚመራበት ሁኔታ ጉዳዩ ሁሉ የሕገ-መንግሥት ሳይሆን የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ መሆኑ የግድ ነው።

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 2 ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪዎች መሆናቸው የተደነገገ ቢሆንም እንደገና በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 2 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ

ነው በሚል ስለተደነገገ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥር መሆኑ ግልፅ ነው:: በዚህም ምክንያት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሕግ-አስፈጻሚውን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በብቸኝነት ይዟል ማለት ነው:: በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 17 በተደነገገው መሠረት የተወካዮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ሌሎች የፌዴራል መንግሥት ባለሥልጣናትን ለጥያቄ መጥራት እንደሚችል፣ የሕግ-አስፈፃሚውን አካል አሠራር የመመርመር ሥልጣን እንዳለው የሠፈረ ቢሆንም በዚሁ ሕገ-መንግሥት የተደነገገው የአብላጫ ምርጫ ሥርዓት ሕግ-አውጭውም፣ ሕግ-አስፈጻሚውም የአንድ ፓርቲ ሰዎች እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው የሕጉ ተግባራዊነት አጠራጣሪ መሆኑ አይቀርም:: በዚሁ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 18 እንደተደነገገው ለሕግ-አስፈጻሚው አካል በተሰጠ ማንኛውም ሥልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሦስተኛ ድምፅ ሲጠይቁ ምክር ቤቱ ይወያያል:: ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመመካከርና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው ቢባልም በአብላጫ ድምጽ የምርጫ ሥርዓት አንድ ፓርቲ የምክር ቤቱን አብላጫ መቀመጫ የሚይዝበት ሁኔታ መኖሩ ስለማይቀር የዚህም ድንጋጌ ተግባራዊነት ደካማ መሆኑ የግድ ነው:: ስለዚህ የሕግ አስፈፃሚነት ሥልጣን የያዘው ጠቅላይ ሚኒስትር ለመረጠው ፓርቲ በሚጠቅምና ሌሎችን በሚጎዳ መልኩ ሥልጣኑን እንደፈለገው ለመጠቀም የሚያስችለው አደረጃጀት መሠረት የተጣለው በራሱ በሕገ-መንግሥቱ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል::

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል በሚል ተደንግጓል:: በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል በሚል ተደንግጓል:: ይኸንኑ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት ጋር ለማጣጣም አዋጅ ቁጥር 111/1987 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል:: በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው የምርጫ ቦርዱን ዋና ኃላፊና ምክትል ዋና ኃላፊ መርጠው በተወካዮች ምክር ቤት የሚያሾሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ናቸው::

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ 5 የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ ይካሄዳል:: በውጤቱም መሠረት የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ይወስናል በሚል ተደንግጓል:: በእነዚህ አንቀጾች ከተቀመጡት ድንጋጌዎች በሚገባ መገንዘብ እንደሚቻለው የምርጫ ክልሎችን አከላለል አጥንቶና ረቂቅ አዘጋጅቶ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለውሣኔ የሚያቀርበው ይኸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተፅዕኖ ሥር የሚገኘው የምርጫ ቦርድ ነው:: በዚህ መሠረት የምርጫ ክልሎችን የመወሰንም ሥልጣን በተዘዋዋሪ መንገድ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ነው ያለው ማለት ይቻላል:: ይኸንን ሥልጣን በእጅ ያስገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ደግሞ ለራሱ ፓርቲ አሸናፊነት የሚጠቅመውን የምርጫ ክልል እንደሚያዘጋጅ የሚያጠራጥር አይደለም::

የዴሞክራሲ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች እንደሚደረገው ከማንኛውም የመንግሥት አካል ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋምም ሆነ የምርጫ ክልል ኮሚሽን በአገራችን የለም:: ምርጫን የሚመለከቱ ቁልፍ ኃላፊዎች ለምርጫ ቦርዱ የተሰጡ ሲሆን ምርጫ ቦርዱ ደግሞ በሕግ-አስፈፃሚው በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተፅዕኖ ስር የወደቀ ነው:: በተግባርም የሚታየው ይኸው በተፅዕኖ ሥር የመውደቅና ነፃነት የሌለበት አሠራር መኖሩ ነው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የሚሰራው ቦርድ በጽሕፈት ቤቱ ውስጥ የሚመደቡት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የአንድ ፖለቲካ ድርጅት አባላት ብቻ እንዲሆኑ የሚደረግበትን አሠራር ለመቆጣጠርና ለመከላከል የሚያስችል ነፃነት የለውም::

በመሆኑም የኢትዮጵያ ምርጫ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤቶችን የሚመሩ ኃላፊዎች ከብሔራዊ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት ጀምሮ እስከ ምርጫ ጣቢያ ድረስ ያሉት ሙሉ በሙሉ አሁን ሥልጣን ላይ ባለው ፓርቲ እየተመለመሉ የሚመደቡ ናቸው:: 99.9 ከመቶ የሚሆኑት የዚሁ ፓርቲ አባላት እንደሆኑም ይታወቃል:: እነዚህ በየደረጃው የሚገኙትን የምርጫ አስፈፃሚ ጽሕፈት ቤቶች የሚመሩ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት አባላት በምርጫ አስፈፃሚነት የሚመድቧቸውና የሚያሰማሯቸው ሠራተኞች የዚህኑ ፓርቲ የኮር አባላት መሆኑም ያደባባይ ምስጢር ነው:: የምርጫ ወረቀትና ልዩ ልዩ ቁሳቁስ የሚገዙ፣ የሚያከማቹ፣ የሚያሳትሙ፣ የሚያሰራጩና የሚቆጣጠሩ እነዚህ በምርጫ አስፈጻሚነት ስም ተመልምለውና ሠልጥነው የተመደቡ የአንድ

ፓርቲ አባላት ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት በተካሄዱ ምርጫዎች በድምጽ አሰጣጥ ላይ የተፈጸሙትን ልዩ ልዩ የማጭበርበር ሥራዎች ሲሰሩ የነበሩት እነዚህ የአንድ ፓርቲ አባላት ናቸው። ለፓርቲያቸው አሸናፊነት በሚጠቅም መንገድ ለተቃዋሚዎች የተሰጡትን የድምጽ ወረቀቶች ሲደብቁ፣ ዋጋ አልባ ሲያደርጉ፣ የምርጫ ሳጥን ሲሰውሩ፣ ሌላ የድምጽ ወረቀት በሌላ ሣጥን ውስጥ በምስጢር እየሞሉ ተቃዋሚዎች ተሸንፈው ገዢው ፓርቲ አሸነፈ ሲባል የከረመው በእነዚህ አስፈፃሚ በሚባሉ የኮር አባላት አማካይነት ነው። ድምፅ የሚቆጥሩና የምርጫ ውጤት ሪፖርት የሚያዘጋጁ እነዚህ የኮር አባላት በመሆናቸው የፈለጉትን አላፊ፣ ያለፈለጉትን ወዳቂ እያደረጉ ለበላዮቻቸው ያቀርባሉ። የበላዮቹም ይኸንኑ ተቀብለው ያፀድቁና የገዥውን ፓርቲ አሸናፊነት ለህዝብ ያውጃሉ። በዚህ ሁኔታ በሚካሄድ ምርጫ የመራጩ ሕዝብ ወደ ምርጫ ጣቢያ እንዲወጣ የሚፈለግበት ዋናው ምክንያት ምርጫ ተካሂዷል እንዲባል ብቻ ነው። አሸናፊውና ተሸናፊውን የሚወስኑት ገዥው ፓርቲ በምርጫ አስፈፃሚነት መድቦ ያሰማራቸው የኮር አባላት ናቸው። አብዛኛው መራጭ በዝቅተኛ የኑሮና የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች በምርጫ ሰሞን የሚያካሂዱትን ዛቻና ማስፈራሪያ ተቋቁሞ የፈለገውን ለመምረጥ እንደሚቸገር የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ በሕይወቱና በኑሮው ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ እጋፈጣለሁ ብሎ ነጻ ውሳኔ ለማድረግ የሚሄድ መራጭ ከተገኘ ደግሞ ምርጫ ጣቢያ አሰፍስፈው የሚጠባበቁና ምስጢር ድምጽ መስጫ ቦታው ድረስ ዘልቀው በመግባት እጅ እየጠመዘዙ ያልፈለገውን እንዲመርጥ የሚያስገድዱ የምርጫ አስፈጻሚዎች ያጋጥሙታል። የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ የሚንቀሳቀሱ ነፃ ታዛቢዎች እውነቱን አይተው መታዘብ እንዳይችሉና የታዘቡትን ሪፖርት እንዳያደርጉ ገዥው ፓርቲ ባቋቋማቸው የመስተዳድር አካላትና በምርጫ አስፈጻሚነት ባሰማራቸው የኮር አባላት ልዩ ልዩ መሰናክሎች ይፈጥሩባቸዋል። የተቃዋሚ ድርጅቶች የምርጫውን ሂደት እንዲከታተሉ በድምፅ መስጫ ጣቢያ የሚመድቧቸውን ተወካዮች የምርጫ አስፈጻሚ የሚባሉት የኮር አባላት ሲፈልጉ ያስሯቸዋል፣ ሲፈልጉ ያባርሯቸዋል። ካልሆነም ከእነዚህ የተቀዋሚ ድርጅቶች ተወካዮች ተደብቀው ድምፅ ከቆጠሩ በኋላ በማያውቁት ጉዳይ ላይ «ድምጽ ቆጠራው እኛ በተገኘንበት በትክክል መቆጠሩን አይተናል» እያሉ እንዲፈርሙ ያስገድዷቸዋል።

በምርጫው ሂደት በመራጮች፣ በተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ በነፃ ታዛቢዎችና በነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ ወንጀል ሲሠራ፣ ምርጫው ግልጽ በሆነ ተፅዕኖና ማጭበርበር ነፃ ምርጫ መሆኑ ሲቀር አቤቱታ የሚቀርብበት ነፃ የዳኝነት አካል የለም። ምርጫ ቦርዱና አስፈፃሚዎቹ ቀደም ሲል በተጠቀሰው ሁኔታ ነፃነት እንዳይኖራቸው ሆነው የተቋቋሙ በመሆናቸው ገዥውን ፓርቲ ከሶ እነርሱ ፊት መቆም ማለት ትርጉም የለውም። በተግባርም የታየው የአገሪቱን ምርጫ ውጤት ጠቅላላ ሊያሰርዝ የሚችል ወንጀል እየተፈፀመ በጥቂት ወረዳዎች፣ በጥቂት ጣቢያዎች ብቻ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲደረግ ነው። ጉዳዩ ህወሓት/ኢሕአዴግ ጥፋት ሠርቷልና ይጠየቅልኝ ይቀጣልኝ ብሎ ለራሱ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ አቤቱታ እንደማቅረብ የሚቆጠር በመሆኑ የሚገኘው መልስ አሳዛኝ ነው። ፍርድ ቤት እንዳይኬድ ነፃ የፍርድ ሥርዓት በአገሪቱ ውስጥ አልተመሠረተም።

በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 78 ንዑስ አንቀፅ 1 ነፃ የዳኝነት አካል መቋቋሙና በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የዳኝነት አካል የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደሚሆን ተደንግጓል። ይሁን እንጂ በዚሁ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የዳኝነት አካል የሆነውን የፌዴራሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት መርጦ ሹመታቸውን በተወካዮች ምክር ቤት የሚያጸድቀው ጠቅላይ ሚኒስትሩ መሆኑ ስለተደነገገ የጠቅላይ ሚኒሰትሩን ፓርቲ የምርጫ አሸናፊነት የሚጎዳ ውሳኔ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ መቸገሩ የማይቀር ነው። በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተደነገገው በየትኛውም ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ እንዲሆን በመደረጉ እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም  የመንግሥት አካል፣ ባለሥልጣን ሆነ ሌላ ተፅዕኖ ነፃ ነው ተብሎ በመደንገጉና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ደግሞ ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት እንደሚያከናውኑና ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ እንደማይመሩ በመደንገጉ የፍርድ ቤቱን ነፃነት መጠራጠር አይገባም የሚል መከራከሪያ ብዙ ጊዜ ይቀርባል። ይኸ መከራከሪያ ግን ዕውነቱን ሊደብቅ ያልቻለና ተጨባጭነት የሌለው መከራከሪያ ነው። ምክንያቱም በፌዴራል ደረጃ ከፍተኛ የዳኝነት አካል የሆነውን የፌዴራሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት መርጦ ሹመታቸውን በተወካዮች ምክር ቤት የሚያፀድቀውን ጠቅላይ ሚኒስትርና በአንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የክልሎች ከፍተኛ የዳኝነት አካል የሆኑትን የክልሎች

ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች መርጠው በክልል ምክር ቤቶች የሚያሾሙትን የየክልሉ ርዕሰ መስተዳድሮች ፓርቲ አሸናፊነት የሚጎዳ ውሳኔ ሰጥቶ የዳኝነት ሥልጣን እንደያዘ ለመቀመጥ የሚችል ዳኛ በኢትዮጵያ የዳኝነት ተቋሞች እንዳልተሾመ በደንብ የሚታወቅ ነው:: ገዥው ፓርቲ በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ የሕግ ሞያና የዳኝነት የሥራ ልምድ ያላቸውን ሞያተኞች አባሮ ለራሱ ፖለቲካ የሚስማሙትን እየመረጠ የዳኝነት ሥልጣን የሰጠው እንዲህ ዓይነት ሥጋት እንዳይፈጠርበት አስቦ ነው:: አሁን በዳኝነት ሥራ ላይ ካሉት ሰዎች መካከል ችሎታ ያላቸው ለሕጉና ለሕሊናቸው ታማኝ የሆኑ ፈጽሞ አይገኙም ማለት አይደለም:: ነገር ግን ነፃ ሆነው በሕጉ መሠረት ለመዳኘት የሚያስችል ምቹ የአደረጃጀትና የአሠራር ሁኔታ በሌለበት ከእነዚህ ችሎታና የሞያ ዲስፕሊን ካላቸው ግለሰቦች አንዳች ተዓምር መጠበቅ ተገቢ ሊሆን አይችልም::

በምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/1987 ከአንቀጽ 69 እስከ አንቀጽ 73 በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎችና ክርክሮች የሠፈሩት ድንጋጌዎች በተጠቀሰው የዳኝነት አካላት አደረጃጀት ነፃነት አለመኖር የተነሳ ትርጉም የሌላቸው ሆነው ቀርተዋል::

ሌላው በአደረጃጀት ችግር ተጠልፎ የወደቀ የሕዝብ ተቋም የመገናኛ ብዙሃን ነው:: ይህ ተቋም ሚዛናዊ የሆነ መረጃ እየሰበሰበ በማሰራጨትና በማሳወቅ መራጩን ሕዝብና በምርጫ የሚወዳደሩትን የተለያዩ ፓርቲዎችና ግለሰቦች በእኩልነት እንዳያገለግል በሚያሳዝን መንገድ የአንድ ቡድን ፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ሆኖ ተደራጀ:: የመንግሥት ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ፕሬስ ድርጅቶች በየሕወሓት/ኢሕአዴግ ከፍተኛ ካድሬዎች አመራር ሥር ወደቁ:: ነፃ አደረጃጀትና አሠራር እንዲኖራቸው በቦርድ የሚተዳደሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ ተስፋ ሲደረግ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪ ካድሬዎቹን በእነዚህ ተቋሞች የቦርድ ኃላፊነትና አባልነት በመመደብ የታሰበውን ነፃ አደረጃጀትና አሠራር የማይቻል አደረገው:: ይባስ ብሎ የፓርቲውን ካድሬዎችና አባላት ካለሞያቸው የጋዜጠኝነት ሥራ እንዲሠሩ እየመደበ የተከበረውን ሞያ አረከሰው:: በዚህ መንገድ የመገናኛ ብዙሃን የሕወሓት/ኢሕአዴግ አወዳሽ ሆነው እንዲሠሩ ተገደዱ:: በምርጫ ጊዜ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን አቋም በማንቋሸሽ ከሚሠሩት አስነዋሪ ተግባር በተጨማሪ መግለጫዎቻቸውንና ማስታወቂያዎቻቸውን እየቆራረጡና እያዛቡ ማሠራጨት መደበኛ ሥራቸው ሆነ:: ከዚህም በከፋ ደረጃ በተቃዋሚ ፓርቲዎች በቂና ተስማሚ የአየር ጊዜ፣ የጽሑፍና ማስታወቂያ ማውጫ ገጽ በነፃ መስጠት ይቅርና በክፍያም እንኳ ለመፈፀም ውጣ ውረዱ የሚቻል አይደለም:: የእነዚህን የሕዝብ ተቋማት ተልዕኮ የጠለፈውና ለራሱ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ አድርጎ መጠቀምን የመረጠው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ይኸንን ሲያደርግ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና ፕሬስ እጥረት ስላጋጠመው አይደለም:: ሌላ ተሻሚ የማይቀርባቸውና የግሉ ንብረት እንደሆኑ የሚታወቁ ነገር ግን ሕግ ከሚፈቅደው ሥርዓት ውጭ ያቋቋማቸው የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች አሉት:: ዜና በማሰባሰብና በማሰራጨት ተግባር ተሠማርተው እንደፈለጋቸው የሚሠሩ እንደ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልና እንደፋና ሬዲዮ ያሉ ተቋሞች አሉት:: ሥርጭታቸው በአንዳንድ ክልሎች የተወሰኑ የድርጅቱ ሬዲዮ አገልግሎት መስጫ ተቋሞችም አሉት:: እነዚህ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ሌላ ለማንም አገልግሎት እንዲሰጡ ጥያቄ የሚቀርብላቸው አይደሉም:: የተቋቋሙበት አግባብ ሕገወጥ ቢሆንም ባለንብረቱ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ራሱ መንግሥት እንደመሆኑ ለመጠየቅና ለመክሰስ የሚችል አንድም ኃይል ስለሌላ የፕሮፓጋንዳና የሚዲያ ንግድ ሞኖፖል ፈጥረው እንዳሻቸው ይሠራሉ:: በምርጫ ጊዜ ሙሉ ኃይላቸውን እየተጠቀሙ በሕወሓት/ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎች ላይ ያነጣጠረ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ይከፍታሉ:: ድርጅቶችን የሚያጥላላ ብቻ ሳይሆን በድርጅቶቹ ውስጥ የገቡትን ግለሰቦች ስብዕና የሚነካ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያካሂዳሉ::

ከዚህ ሌላ የመራጩን ሕዝብ መብትና ግዴታ በማሳወቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉት የትምህርትና የምርምር ተቋሞች የአደረጃጀት ነፃነት ስለሌላቸው ዴሞራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ የሚያግዝ ሚና አይጫወቱም:: የሥርዓተ ትምህርቱንና የምርምሩን ዓላማና ይዘት ለአንድ ቡድን ጥቅም በሚያመች አቅጣጫ እንዲቀረጽ የሚወስኑትና አመራር የሚሰጡት ሕወሓት/ኢሕአዴግ ያስቀመጣቸው የፖለቲካ ካድሬዎች በመሆናቸው በአገሪቱ ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲበቅል የሚረዳ አስተዋፅኦ ማድረግ አልቻሉም:: እነዚህና የመሳሰሉት መዋቅራዊ ችግሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዳይኖር ያደረጉ ሲሆን በአገሪቱ ውስጥ ላለው የምርጫ ችግር በተመሳሳይ ሁኔታ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሌሎች ነጥቦች እንዳሉም መረዳት ያስፈልጋል::

## 2.3 የምርጫ ሥርዓት ችግሮች

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ አገዛዝ እየተካሄዱ ያሉትን ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ እንዳይሆኑ ካደረጓቸው መዋቅራዊ ችግሮች ጎን መታየት ያለበት ነጥብ የምርጫ ሥርዓቱ ነው:: አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተደነገገው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት እንደሚመረጡና የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው አናሣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል እንደሚሆኑ ተገልጿል:: ይኽ ድንጋጌ የሚያሳየው በተወካዮች ምክር ቤት ደረጃ ለሚደረገው ምርጫ ሥራ ላይ የሚውለው አብላጫ ድምጽ ሥርዓት መሆኑን ነው:: ይህ የምርጫ ሥርዓት ደግሞ የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለበትም አገር ቢሆን እስካሁን በሥራ ላይ ካሉት የምርጫ ሥርዓቶች ሁሉ የተሻለው ሆኖ እንዳልተገኘ የሚታወቅ ነው:: በዚህም የተነሣ ይኽንን የምርጫ ሥርዓት ሥራ ላይ በሚያውሉ አገሮች ከተለያየ አቅጣጫ ቅሬታ የሚቀርብበትና አከራካሪነቱ እየጨመረ የመጣ የምርጫ ሥርዓት ዓይነት ነው፡ በዚህ የምርጫ ሥርዓት ላይ የሚቀርበው ቅሬታና የሚነሳው ክርክር አንደኛ በፓርላማ ውስጥ የተለያዩ አመለካከቶች፣ የሕዝቡ ማኅበራዊ ጥንቅርና መልክዓ ምድራዊ ውክልና በሚገባ እንዲንፀባረቅ አያስችልም የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አሸናፊው የሚለየው የአብዛኛ ድምጽ ማግኘቱ ሳይረጋገጥ በድምጽ ብልጫ ብቻ በመሆኑ የሚመሠረተው መንግሥት ሠፊ የሕዝብ ድጋፍ የሌለው መንግሥት ይሆናል የሚል ነው::

ይህ ነጥብ ዕውነትነት እንዳለው ለመረዳት በቅርቡ በ1992 ዓ.ም በአገራችን የተካሄደውን የክልልና የፌዴራል ምክር ቤቶች ምርጫ[5] ለአብነት መጥቀስ ይቻላል:: በዚህ ምርጫ በርከት ያሉ ተቃዋሚዎች ከገኙት ፓርቲ ጋር የተወዳደሩበትን የአዲስ አበባ ከተማ ውጤት ማየት እንደተቻለው በአብዛኛው የገዥው ፓርቲ ተወካዮች አሸናፊ በሆኑባቸው የምርጫ ክልሎች ድምፅ ከሰጠው መራጭ ውስጥ «50 በመቶና + 1» ውጤት አላገኙም:: አሸናፊ መሆን የቻሉት መራጩ ከሰጠው ድምፅ ከ50 በመቶ በታች የሆነውን ድጋፍ «አግኝተው» ነገር ግን ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች መካከል የተሻለ ድምፅ ያለው አላፊ እንዲሆን በሚፈቅደው የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ተጠቅመው ነው:: ለምሳሌ ከ100 መራጮች መካከል 30 የሚሆኑት የገዥውን ፓርቲ ዕጩ ደግፈው ድምፅ ቢሰጡና 70 ከመቶ የሚሆኑት መራጮች ደግሞ ለ3 የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች እኩል በሆነ መጠን የድጋፍ ድምፅ እንደሰጡ ተደርጎ ቢወሰድ አሸናፊ የሚሆነው የገዥው ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ ነው:: ምክንያቱም የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች እያንዳንዳቸው በተናጠል የሚያገኙት የድጋፍ ድምፅ ከ25 በታች ስለሚሆንና የ30 መራጮችን የድጋፍ ድምፅ ለብቻው ያገኘው የገዥው ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ አብላጫ ድምፅ ስለሚሆን ነው:: ከዚህ ቀላል ምሳሌ ስሌት ማየት እንደሚቻለው ጠቅላላ ድምፅ ከሰጡ መራጮች መካከል 30 ከመቶ የሚሆኑት የፓርላማ ተወካይ ሲያገኙ 70 ከመቶ የመራጮች ድምፅ ግን ዋጋ ያጣል ማለት ነው:: ለዚህም ነው በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት የሚመሠረት መንግሥት ሠፊ የሕዝብ ድጋፍ የሌለው ነው የሚለው ቅሬታና ክርክር በየአቅጣጫው የሚሰማው::

ከዚህ ሌላ በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ላይ የሚቀርብ ጠንካራ ድክመት አለ:: ይኸውም በተወሰነ የሀገሪቱ ክፍል ብቻ አሸናፊ በመሆን የፓርላማውን አብዛኛ መቀመጫ አንድ ፓርቲ እንዲቆጣጠ ር የሚያስችል መሆኑ ነው:: ይኽንን ድክመት በሀገራችን ከተደረገው ምርጫ ለማየት እንዲቻል አንድ አብነት በማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል:: ኤች ጀምስ ቶልሔሙስ (H.Jems Tolheemus) የተባለ አማካሪ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2002 አዲስ አበባ ለሚገኘው የኔዘርላንድስ ኤምባሲ ካቀረበው አንድ ጥናት ለዚህ አስተያየት ትክክለኛነት ደጋፊ ማስረጃ ሊሆን የሚችለውን አንድ ነጥብ ብቻ ማንሳት በቂ ነው:: ይኸ ጥናት «እ.ኤ.አ በ2005 ኢትዮጵያ በምታካሂደው ብሔራዊ ምርጫ የእርዳታ ሰጪዎች ጠቃሚ ተሳትፎ የድርጊት መርሃ ግብር» በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1995 ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደውን የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የሚገመግም መረጃም በጥናቱ ውስጥ ተካቶ ቀርቧል:: በዚህም መረጃ መሠረት በተጠቀሰው አመት የተካሄደው ምርጫ የሚያጠቃልላቸውን ክልሎች በእያንዳንዱ ክልል የተመዘገበውን

---

*[5] ኤች ጀምስ ቶልሔሙስ የተባሉ አማካሪ ሐምሌ 1994 ዓ.ም. (እ.አ.አ 2002) አዲስ አበባ ለሚገኘው የሆላንድ (ኔዘርላንድስ) ኤምባሲ አንድ ጥናት አቅርበዋል:: ይኽ ጥናት «በ1997 ዓ.ም (እ.ኤ.አ በ2005) ኢትዮጵያ በምታካሂደው ብሔራዊ ምርጫ የእርዳታ ሰጪዎች ጠቃሚ ተሳትፎ የድርጊት መርሃ ግብር» በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሲሆን በ1987 ዓ.ም ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደውን የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የሚገመግም መረጃም በጥናቱ ውስጥ ተካቶ ቀርቧል::*

መራጭ፣ የእያንዳንዱ ክልል መራጭ ለተወካዮች ምክር ቤትና ለክልል ምክር ቤት መርጦ የላከውን የተወካዮች ብዛት ከዚህ ቀጥሎ በማቅረብ የአብላጫ ድምጽ ሥርዓትን ጉልህ ችግሮች ግልጽ አድርጎ ለማሳየት ይሞከራል፡፡

## እ.ኤ.አ በ1995 ኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው ሀገራዊ ምርጫ የተመዘገቡ መራጮችና የተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች ተወካዮች

| ተ.ቁ | ክልል | የተመዘገቡ መራጮች | ለተወካዮች ምክር ቤት የተመረጡ ተወካዮች | ለክልል ም/ቤት የተመረጡ ተወካዮች | አንድ የተወካዮች ም/ቤት አባል ለመወከል የሚያስችለው መራጭ ቁጥር | አንድ የክልል ምክር ቤት አባል ለመወከል የሚያስችለው መራጭ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ትግራይ | 1364087 | 38 | 152 | 35897 | 8974 |
| 2 | አፋር | 574616 | 8 | 48 | 71827 | 11971 |
| 3 | አማራ | 5447236 | 138 | 274 | 39473 | 19880 |
| 4 | ኦሮሚያ | 6191826 | 177 | 354 | 34982 | 17491 |
| 5 | ሶማሌ | 2294497 | 23 | 139 | 99761 | 116507 |
| 6 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 213665 | 9 | 57 | 23741 | 3749 |
| 7 | ደቡብ | 4473693 | 123 | 240 | 36371 | 18640 |
| 8 | ጋምቤላ | 52487 | 3 | 40 | 17496 | 1312 |
| 9 | ሀረር | 60357 | 2 | 36 | 30179 | 1677 |
| 10 | ድሬዳዋ | 100151 | 2 | 0 | 50076 | 0 |
| 11 | አዲስ አበባ | 564378 | 23 | 92 | 24538 | 6135 |
| | **ድምር/አማካይ** | **21336993** | 546 | 1432 | 464341 | 206336 |

ከዚህ አሃዛዊ መረጃ ማየት እንደሚቻለው እ.ኤ.አ . በ1995 ኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደው ምርጫ አዲስ አበባና ድሬዳዋን ጨምሮ 11 ክልሎች በምርጫው ተካፍለዋል፡፡ በሁሉም ክልሎች (በመላው ኢትዮጵያ ማለት ነው) የተመዘገቡ መራጮች ብዛት 21,336,993 (ሃያ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰላሳ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሶስት) ነው ለተወካዮች ም/ቤት የተመረጡት 546 ሲሆኑ ለክልል ምክር ቤቶች ደግሞ 1432 (አንድ ሺህ አራት መቶ ሰላሳ ሁለት) ተወካዮች ተመርጠዋል፡፡ በሀገሪቱ የተመዘገቡ መራጮች በተወካዮች ምክር ቤት ለተወከሉት ተወካዮች ሲካፈል የሚገኘው ቁጥር 39,079 (ሰላሳ ዘጠኝ ሺህ ሰባ ዘጠኝ) ነው፡፡ ወይም 21,336,993÷546= 39079 ነው፡፡ ይኸም ማለት በአማካይ እያንዳንዱ 39,079 መራጭ አንድ የተወካዮች ምክር ቤት ወክሏል ማለት ነው፡፡

**እንደሚታወቀው ገዥው ፓርቲ ትግራይን፣ አማራን፣ ኦሮሚያንና የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝቦች የሚሉትን አራት ክልሎች በብቸኝነት የራሱ ነፃ ክልል አድርጎ ስለሚቆጣጠራቸውና ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወደነዚህ ክልሎች ገብተው መወዳደር እንዳይችሉ ከባድ ተፅዕኖ ስለሚያደርግባቸው ከእነዚህ ክልሎች የሚገኘውን የመራጭ ድምፅ ሙሉ በሙሉ ይወስዳል፡፡ በገዥው ፓርቲ ሙሉ ተፅዕኖ ሥር የወደቁት ክልሎች መራጭ ቁጥር በጠቅላላው በአገሪቱ ከተመዘገቡ መራጮች ያለው ድርሻ 82 በመቶ ነው፡፡ አራቱ ክልሎች በተወካዮች ምክር ቤት ያላቸው የውክልና ድርሻ ትግራይ 6 በመቶ፣ አማራ 26 በመቶ፣ ኦሮሚያ 29 በመቶ፣ ደቡብ 21 በመቶ፣ በጠቅላላው 82 በመቶ ነው፡፡ የአዲስ አበባ መራጮች ድምፅ በአራቱ ክልሎች ላይ ከተጨመረ ድርሻው ወደ 85 በመቶ ከፍ ይላል፡፡ በዚህም መሠረት 82 ወይም 85 የፓርላማ መቀመጫ ያገኘ ፓርቲ አገሪቱን ለመግዛት የሚያስችለውን ድምፅ ስለያዘ ቀሪው 15 በመቶ በሚወከልባቸው ክልሎች የመራጭ ድምፅ ለማግኘት የሚጨነቅበት ሁኔታ የለም፡፡ ለዚህም ነው ገዥው ፓርቲ አራቱን የአገሪቱን ክልሎች እንደግል ንብረቱ ይዞ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን አላስደርስም እያለ ጥብቅ ክልከላ የሚያደርገው፡፡ የሚመጣውን ዕዳ እንሸከማለን ብለው በመወሰን ተሳትፎ ለማድረግ የሚሞክሩ ተቃዋሚዎች ብቅ ካሉ ደግሞ መከላከያ ሠራዊት አሠማርቶ ከባድ ጭፍጨፋ የሚያካሂደውና ለገላጋይ እስስኪያስቸግር ድረስ ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለው ይኸንን 82**

በመቶ የፓርላማ መቀመጫ አጋርቶ በፓርላማ ውስጥ የያዘውን የበላይነት ላለማጣት ነው:: እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ አበባንም ጨምሮ ነፃ ክልል ለማድረግና የፓርላማ ድርሻውን ወደ 85 ከፍ ለማድረግ በሌሎች ክልሎች የሚጠቀምበትን ኃይልና አፈና ለመጠቀም እየሞከረ ነው::

ይህ የፓርላማ መቀመጫ ድርሻ እስካልተቀየረ ድረስ ተቃዋሚዎች እስከ ዓለም ፍፃሜ ቢቃወሙ ወይንም ግፋ ቢል ገዢው ፓርቲ የኢሕአዴግ ያልሆኑ ክልሎች በሚላቸውና የሞግዚት አስተዳደር ኃላፊነት እንደወሰደ አድርጎ በሚመለከታቸው ሌሎች ክልሎች ያለውን 15 ከመቶ የመራጮች ውክልና ቢያሸንፉ እንኳ ገዥ ፓርቲ ሆኖ መቀጠሉን የሚያስቀር ተዓምር እንደማይፈጠር ስለሚያውቅ የፖለቲካ ጨዋታውን በዚህ ስሌት እየመራው ነው:: የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የሕገ-መንግሥቱ አካል እንዲሆን የተደረገበት ዋና ምክንያትም ለዚህ ዓላማ ተፈጻሚነት የተሻለው ሥርዓት ሆኖ በመገኘቱ ነው:: በተለይ ደግሞ ተቃዋሚዎች አሁን በሚገኙበት የተበታተነ ሁኔታ እስከቀጠሉና የተሳትፎ ክልላቸውም አሁን ባለበት አነስተኛ የሽፋን ደረጃ ተወስኖ እስከቆየ ድረስ የመራጩን ድምፅ እንዲከፋፈል ስለሚያደርጉትና ብዙ መራጭ የሚገኙባቸውን ክልሎች ድምፅ መጋራት ስለማይችሉ በአብላጫ የድምፅ ሥርዓት ዝንተ-ዓለም አሸናፊ የሚሆነው አሁን ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ነው::

የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት በሥራ ላይ መዋሉ እስከቀጠለ ድረስ ፓርላማው በአገሪቱ ውስጥ ያሉት የተለያዩ አመለካከቶች ማህበራዊ ጥንቅርና ጂኦግራፊያዊ ክልሎች በሚገባ የማይወከሉበት፣ የብዙሃኑ መራጭ ሕዝብ ድጋፍ የሌለው፣ ቢሮክራሲውንና መከላከያን እንዲሁም የፖሊስና የደህንነት ተቋሙን አንዷ በእጁ ያገባ ቡድን እንደፈለገው ሲያሽከረክረው የሚኖር ፋይዳ የሌለው ተቋም ሆኖ ይቀራል:: በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በተለያዩ አንቀጾች የተደነገጉትና ተፈፃሚነት እንዲያገኙ ከፓርላማው አባላት የተወሰነ ድምጽ እንዲኖር የሚጠይቁት ጉዳዮች ሥልጣን የያዘው ፓርቲ ካልፈለገ በስተቀር ምንጊዜም ተፈጻሚነት አያገኙም:: ለምሳሌ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 18 የተደነገገውና ለሕግ-አስፈጻሚው አካል በተሰጠ ማንኛውም ሥልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ-ሦስተኛ ድምፅ ሲጠይቁ ምክር ቤቱ ይወያያል የሚለው ሕግ ሥልጣን ከያዘው ፓርቲ ፍላጎት ውጭ ተፈፃሚ እንዲሆን ምክር ቤቱ በ1987 ዓ.ም ከነበሩት 546 ተወካዮች መካከል ቢያንስ ከ182 በላይ የሚሆኑ አባላት የመንግሥት ሥልጣን ከተረከበው ፓርቲ ተወካዮች የተለየ አመለካከት የሚወክሉ መሆን አለባቸው::

ከሁሉም በላይ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 56 በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የፌዴራሉን መንግሥት የሕግ-አስፈፃሚ አካል ያደራጃል/ያደራጃሉ፣ ይመራል/ይመራሉ በሚል የተደነገገውና በዚህ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ 2 በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ያገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች የመንግሥት ሥልጣን ይረከባል/ይረከባሉ በሚል የተደነገገው አንቀጽ ከአንድ ብቸኛ ፓርቲ የበላይነት ነፃ በሆነ መንገድ ተፈፃሚነት እንዲያገኝ ከ546 የተወካዮች ምክር ቤት አባላት መካከል የአንድ ብቸኛ ፓርቲ ተወካዮች ከ273 በላይ እስከሆኑ ድረስ በሕገ-መንግሥቱ የተደነገገው የጣምራ መንግሥት የመመሥረት ድንጋጌ ትርጉም የሌለው የወረቀት ላይ ጌጥ ሆኖ ይቀራል:: ፓርላማውም የአንድ ፓርቲ አጀንዳ ማስፈጸሚያ ጠባብ መድረክ እንደሆነ ይቀጥላል:: የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ ሆኖ እስከተቀመጠ ድረስ ከዚህ ሁኔታ በመውጣት ሠፊ የሕዝብ መሠረት ያለውና ሁሉንም ዓይነት የውክልና ገፅታዎች በሚገባ የሚያንፀባርቅ ፓርላማ በአገሪቱ ለመመሥረት ያለው ዕድል ለሁልጊዜም እንደተዘጋ የሚቆጠር ነው::

ከላይ በአሃዝ ከተቀመጠው መረጃ በመነሳት የተወሰኑ ክልሎችን ብቻ እንደምሳሌ ወስዶ በተወካዮች ምክር ቤት ያገኙትን የውክልና ድርሻ ማነፃፀርና የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት ያለበትን ሌሎች ችግሮች ማየት ይቻላል:: ከእነዚህ ችግሮች መካከል አንደኛው በተለያዩ ምርጫ ክልሎች የሚገኙ መራጮች ድምፅ እኩል ዋጋ እንዳይኖረው ማድረጉ ሲሆን ሌላው ደግሞ መራጮች የሰጡትን ድምፅ ዋጋ የሚያሳጣ መሆኑ ነው:: በዚህም መሠረት ለምሳሌ ጠቅላላ ከተመዘገቡት የሀገሪቱ መራጮች ውስጥ 6,191,826 (ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ስድስት) የሚሆኑት በኦሮሚያ ክልል የተመዘገቡ መራጮች ናቸው:: ለእያንዳንዱ 39,079 መራጭ አንድ ተወካይ ለተወካዮች ም/ቤት መላክ ስላለበት ኦሮሚያ ሊወክል

የሚችለው 6,191,826÷39,079=158 (አንድ መቶ ሃምሳ ስምንት) ተወካዮችን ነው። ይሁን እንጂ በዚህ መረጃ ላይ እንደተመለከተው በተወካዮች ም/ቤት የኦሮሚያ ተወካዮች ቁጥር 177 (አንድ መቶ ሰባ ሰባት) ነበር። በትግራይ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 1,364,087÷39079=35 (ሰላሳ አምስት) ነው። ይሁን እንጂ በተጨባጭ ትግራይ መወከል የቻለው 38 (ሰላሳ ስምንት) ተወካዮችን እንደነበር መረጃው ያመለክታል። በአማራ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 5,447,236 (አምስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ስድስት) ሲሆኑ፤ በተወካዮች ም/ቤት ሊወክሉት የሚችሉት ቁጥር 5,447,234÷39,079=139 (አንድ መቶ ሰላሳ ዘጠኝ) ነው። ይሁን እንጂ በተጨባጭ አማራ መወከል የቻለው 138 (አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት) ተወካዮችን እንደነበር መረጃው ያመለክታል። በአፋር የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 574,616 (አምስት መቶ ሰባ አራት ሺህ ስድስት መቶ አስራ ስድስት) ሲሆኑ በተወካዮች ምክር ቤት ሊወክሉት የሚችሉት ቁጥር 574,616÷39,079=15 (አስራ አምስት) ነው። ይሁን እንጂ በተጨባጭ አፋር መወከል የቻለው ስምንት ተወካዮችን እንደነበር መረጃው ይጠቁማል። በሶማሌ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 2,294,497 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ሰባት) ሲሆኑ በተወካዮች ምክር ቤት ሊወክሉት የሚችሉት ቁጥር 2,294,497÷39,079=58 (ሃምሳ ስምንት) ነው። ይሁን እንጂ በተጨባጭ ሶማሌ ክልል መወከል የቻለው ሃያ ሶስት ተወካዮችን እንደነበር መረጃው ይጠቁማል። በጋምቤላ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 52,487 (ሃምሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ሰባት) ሲሆኑ በተወካዮች ምክር ቤት ሊወክሉት የሚችሉት ቁጥር 52,487÷39,079=2 (ሁለት) ነው። ይሁን እንጂ በተጨባጭ ጋምቤላ ክልል መወከል የቻለው ሶስት ተወካዮችን ነበር። በሀረሪ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 60,357 (ስልሣ ሺህ ሶስት መቶ አምሳ ሰባት) ሲሆኑ በተወካዮች ም/ቤት ሊወክሉት የሚችሉት ቁጥር 60,357÷39,079=2 (ሁለት) ነው። በተጨባጭ ሀረሪ የወከለው ይኸንኑ 2 (ሁለት) ተወካዮችን ነበር።

ከዚህ አሃዛዊ መረጃ ማየት የሚቻለው አንዳንድ ክልል መወከል ከሚገባው በላይ ውክልና እንዲያገኝ የተደረገበትና አንዳንዱ ደግሞ መወከል ከሚገባው በታች የሆነ ቁጥር እንዲወክል የተደረገበት የዘፈቀደ አሰራርና አድሎ መኖሩን ነው። እዚህ ላይ መገምገም የተፈለገው ግን ከዚህም በከፋ መንገድ የመራጮች ድምፅ እኩል ዋጋ የማይሰጠው መሆኑን ነው። ይኸንን ግልጽ ለማድረግ በተጠቀሱት ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ምን ያክል መራጮች አንድ ተወካይ ለተወካዮች ምክር ቤት መላክ እንደቻሉ በማስላት የየክልሉ መራጮች ድምፅ እኩል ዋጋ እንደሌለው ማሳየት ይቻላል። በዚህም መሠረት በኦሮሚያ እያንዳንዱ 34 ሺህ ገደማ መራጭ ድምፅ አንድ ተወካይ (6,191,826÷177=34,982) ማስገኘት ሲችል፣ የጋምቤላ እያንዳንዱ 17 ሺህ ገደማ መራጭ ድምፅ አንድ ተወካይ ያስገኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ የሀረሪ እያንዳንዱ 3 ሺህ መራጭ ድምፅ ከሶማሌ እያንዳንዱ 99 ሺህ መራጭ ድምጽ ጋር እኩል አንድ ተወካይ ለተወካዮች ምክር ቤት መላክ ይችላል ማለት ነው። እንደዚሁም እያንዳንዱ 3 ሺህ የሀረሪ መራጭ ድምፅ ከትግራይ እያንዳንዱ 36 ሺህ መራጭ ድምፅ ጋር እኩል አንድ ተወካይ ለተወካዮች ምክር ቤት ይልካል። ከዚህ አነስተኛ ማነጻጸሪያ መረዳት የሚቻለው በትግራይ የሚገኙ መራጮች የሚሰጡት ድምፅ የሀረሪ መራጮች ከሚሰጡት ጋር እኩል ዋጋ የሌለው መሆኑን ነው።

ምክንያቱም በትግራይ 36 ሺህ እና በሀረሪ 3 ሺህ መካከል ያለው 33 ሺህ ገደማ የትግራይ መራጮች ድምፅ ዋጋ አልባ እንዲሆን በመደረጉ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በኦሮሚያ የሚገኙ መራጮች የሰጡት ድምፅ የጋምቤላ መራጮች ከሰጡት ጋር እኩል ዋጋ እንደሌለው መረዳት ይቻላል። ምክንያቱም በኦሮሚያ 34 ሺህ እና በጋምቤላ 17 ሺህ መካከል ያለው 17 ሺህ ገደማ የኦሮሚያ መራጮች ድምፅ ዋጋ አልባ እንዲሆን በመደረጉ ነው፡ በዚህ መንገድ የእያንዳንዱን ክልል መራጮች ድምፅና በተወካዮች ምክር ቤት ማግኘት የቻለውን ውክልና መጠን እያሰሉ ንጽጽር በመስራት በመራጮች ድምጽ መካከል ያለውን የዋጋ አለመጣጣም በሚገባ ማየት ይቻላል። የዚህ አይነቱ ችግር የአብላጫ ድምፅ ሥርዓት ቀጥተኛ ውጤት ሲሆን በዚህ መሠረት የተቋቋመው የተወካዮች ምክር ቤትም የዜጎች ውክልና በተመጣጣኝ መንገድ የሚንፀባረቅበት ነው ለማለት የማያስችል ከፍተኛ ችግር ያለበት ነው።

በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በክልሎችና በአካባቢ ደረጃ የሚመሠረቱ ምክር ቤቶች አባላት አመራረጥ ሥርዓት ምን እንደሆነ በግልፅ ባለመደንገጉ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ለማሸነፍ ይጠቅመኛል የሚለውን የምርጫ ስርዓት እንደፈለገው እየለዋወጠ እንዲጠቀም ልዩ ዕድል ሰጥቶታል:: የምርጫ ሥርዓቱን ሲቀያይር በምርጫው ለመወዳደር በሕግ የተመዘገቡትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳያማክር በድንገት ስለሚሆን ዝግጅታቸውንና ድካማቸውን ሁሉ ባልተጠበቀ ሁኔታ መና የሚያስቀርበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡ በዚህ ድብቅ ሥልት እየተጠቀመ በክልሎችና ከዚያ በታች ባሉ እርከኖች ደረጃ የሚኖሩትን ውክልናዎች ተገቢ ባልሆነ መንገድ ይቆጣጠራል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው በገጠር ውስጥ የሚኖር ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው የትምህርትና የኑሮ ደረጃም እጅግ ዝቅተኛ ነው:: ይኸንኑ አጋጣሚ እየተጠቀመ መራጮችን የሚያሳስቱ መረጃዎችን በመስጠት በእርዳታ መልክ የሚከፋፈልን እህል፣ ለራስ አገዝ ልማት ማስፋፊያ የሚሰጥ እርዳታና ብድርን፣ የኪራይ ቤትን፣ የእርሻ መሬትን፣ የማዳበሪያ እዳን፣ የአነስተኛ ቁጠባና ብድር አገልግሎትን አንድም በመያዣነት፣ አለዚያም በማስፈራሪነትና ወይም በማባበያነት እየተጠቀመ በተቸገሩ ወገኖች ላይ ሣይቀር ገኘው ፓርቲ ከፍተኛ ሙስና ይፈጽማል:: በዚህ ዓይነቱ የምርጫ ሙስና በድህነት ላይ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ይጥራል:: በድሆችና በድህነት ላይ እየነገዱ የፖለቲካ ትርፍ በማግኘት ዴሞክራት መስሎ ለመታየት የሚጥር ጉደኛ መንግሥት በምድራችን ውስጥ አለ ከተባለ የመጀመሪያውን ሥፍራ የሚይዘው እኛ አገር የመንግሥት ሥልጣን በኃይልና በብቸኝነት የተቆጣጠረው ህወሓት/ኢሕአዴግ ነው::

የምርጫ ሥርዓት ችግሮች በሚነሱበት ጊዜ መታለፍ የማይገባው አንድ ነጥብ ቢኖር በሕገመንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው ነው:: ይህ ድንጋጌ «የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሠጣቸው አናሣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ከ550 የማይበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አናሣ ብሔረሰቦች ከ20 የማያንስ መቀመጫ ይኖራቸዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይደነገጋል::» ይላል:: ይኸንኑ ድንጋጌ ተፈጻሚ ለማድረግ በአዋጅ ቁጥር 111/1987 አንቀጽ 15 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 7 በተገለፀው ሁኔታ የምርጫ ክልል 100 ሺህ ሕዝብ እንደሚያቅፍ፣ የተወካዮች ምክር ቤት የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል የሚላቸውን አናሣ ብሔረሰቦች ተወካዮቻቸውን መርጠው እንዲልኩ እንደሚያደርግ፣ የተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ክልሎችን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተመለከተው በተለየ ሁኔታ ሊወስን እንደሚችል፣ የምርጫ ክልሎች ዝርዝር ቦርዱ አጥንቶ በሚያቀርበው መሠረት በተወካዮች ምክር ቤት ተወስኖ ለሕዝብ እንደሚገለጽ፣ ለፌደራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአንድ የምርጫ ክልል አንድ ተወካይ ብቻ እንደሚመረጥ፣ በክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ከአንድ የምርጫ ክልል ምን ያህል ተወካዮች እንደሚመረጡ የምርጫ ቦርድ የሚመለከታቸውን ክፍሎች አስተያየት መሠረት በማድረግ እንደሚወስን በሕግ ተቀምጧል:: የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌና የአዋጁን መንፈስ ተከትሎ በ1987 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ የፌደራል ተወካዮች ምክር ቤት 546 አባላት የተወከሉ ሲሆን በክልል ምክር ቤቶች ደግሞ ዝቅተኛው (የሐረሪ) 36 አባላት ከፍተኛው ደግሞ (የኦሮሚያ) 354 አባላት ተወክለዋል::

በመጀመሪያ ደረጃ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት እስከ 550 ድረስ እንዲሆኑ የተወሠነበት ምክንያት ግልጽ አይደለም:: ኢትዮጵያ ሠፊ የግዛት ክልልና ብዙ ሕዝብ ስላላት እንዳይባል ከኢትዮጵያ የሚሠፋ የግዛት ክልልና ወደ 1 ቢሊዩን ገደማ ሕዝብ ያላት ሕንድ የፓርላማ አባሎች ቁጥር 550 ሲሆን ወደ 300 ሚሊዮን ገደማ ሕዝብ ያላት አሜሪካ የተወካዮች ምክር ቤት አባሎቿ ቁጥር ለረጅም አመታት ከ435 በልጦ አያውቅም:: በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት መሠረት በየ5 ዓመቱ ሰዎች ከሚቀያየሩ በስተቀር በቋሚነት የሚሠሩ እንደመሆናቸው የአገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም ይኸንን ያህል ቁጥር ያላቸው ተወካዮች በአስተማማኝ ደረጃ ለመሸከም የሚያስችል ጥንካሬ አለው ለማለት አገሪቱ የምትገኝበትን አስከፊ ድህነትና ኋላቀርነት እንዳላዩና እንዳልሰሙ መሆን ይጠይቃል:: በዚህ ላይ ደግሞ የምርጫ ሥርዓት የአብላጫ ድምጽ እንደመሆኑ በዚህ የምርጫ ስርዓት የሚመሠረት መንግስት በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ልዮ ልዩ አመለካከቶች፣ ማህበራዊ ጥንቅርና ጂኦግራፊያዊ ክልል በተገቢው ሁኔታና በተመጣጣኝ መንገድ ለመወከል የማይችል ድክመት ያለበት መሆኑ ሲጨመርበት የቁጥሩ መብዛት ለሀገሪቱ ከሚሠጠው ጥቅም ይልቅ በተለያየ መልኩ የሚያስከትለው ጉዳት ያመዝናል::

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ5 በተደነገገው መሠረት የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ እንደሚካሄድ፣ በውጤቱም መሠረት የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌደሬሽኑ ምክር ቤት እንደሚወስን ተገልፆል:: ይሁን እንጂ የምርጫ ክልሎችን አወሣሰን በዝርዝር የሚገልፀው አዋጅ ቁጥር 111/1987 ሕገ-መንግሥቱ ለፌደሬሽን ምክር ቤት የሠጠውን ሥልጣን ወደጐን በመተው በዚህ ረገድ ያለውን ሁሉንም ኃላፊነት ለተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ጠቅልሎ በመስጠቱ የተለያዩ ብሔረሰቦች በተለይም አናሣዎቹ በተወካዮች ምክር ቤት ተገቢነት ያለው ውክልና እንዲያገኙ የሚያስችል የምርጫ ክልል እንዲኖር ገንቢ አስተዋፅዖ ሊያደርግ የሚችለውን የፌደሬሽን ምክር ቤት ሚና ዋጋ ቢስ አድርጐታል:: በዚህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ አፈጻጸም ላይ ከተወካዮች ምክር ቤት ያነሠ የፓርቲ ወገንተኝነት ሊኖረው የሚችለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው:: ምክንያቱም የፌደሬሽን ምክር ቤት ከፓርቲ ውክልና ይልቅ ለብሔረሰብ ውክልና ትኩረት የሚሠጥ መሆኑ ስለማይቀር በተወካዮች ምክር ቤት የብሔረሰቦች ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖር የሚያደርግ የምርጫ ክልል እንዲኖር ከተደረገ ፓርላማው በተወሠነ ደረጃ የማህበራዊ ጥንቅር አንድ ነጥብ የሆነውን ጉዳይ ያሟላል ማለት ነው:: ነገር ግን የፌደሬሽን ምክር ቤት ሕገ-መንግሥታዊ ስልጣን በአዋጅ ስለታጠፈ የሚገባውን ሚና እየተጫወተ አይደለም:: በአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የተነሣ በአገራችን የሚካሄደው ምርጫ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ለመፍጠር የነበረውን ተስፋ በሚያጨልም አጣብቂኝ ውስጥ የገባበትን ሁኔታ እየጠቀሱ ከዚህ በሠፋ ደረጃ ማቅረብ ቢቻልም ዋና ዋና የሚባሉት ችግሮች ብቻ ተነስተዋል:: ቀጥሎ ደግሞ ከምርጫው መዋቅራዊ ችግሮችና ከምርጫ ሥርዓቱ ባህሪይ በመነጨ ሁኔታ የሚከሠቱትንና በሀገራችን ምርጫ ሂደት ከባድ ጉዳት እያደረሱ የሚገኙትን የአፈፃፀምና የአሠራር ችግሮች ማየት ያስፈልጋል::

## 2.4 የምርጫ አፈፃፀምና አሰራር ችግሮች

በኢትዮጵያ ውስጥ ከምርጫ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚታዩት ችግሮች ቀደም ሲል ከተነሱት መዋቅራዊና የምርጫ ሥርዓት ችግሮች የሚመነጩ ናቸው:: በአፈፃፀምና አሠራር የሚፈጠሩትን ችግሮች ከአደረጃጀትና ከምርጫ ሥርዓቱ ችግሮች ነጥሎ ለማየት መሞከር በመፍትሔ አፈላለጉ ረገድ ከፍተኛ ስህተት ላይ ይጥላል:: በወባ ለተጠቃ ሕመምተኛ የጉንፋን ማስታገሻ መድኃኒት እንደማዘዝ የሚቆጠር ስህተት ይፈጠራል:: በእርግጥ የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ ባህል አለመዳበር፣ አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ያልተማረና ዝቅተኛ በሆነ የኑሮ ደረጃ ላይ መገኘቱ በምርጫ አፈፃፀምና አሠራር ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ የለም ማለት አይደለም:: ኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው የኢኮኖሚ ኋላቀርነትና አጠቃላይ ድህነት የሚፈጥረው ጉድለት ቀላል አይደለም:: የመሠረተ ልማት አለመስፋፋት ተፅዕኖው ከባድ ነው:: የመገናኛ አውታር በሠፊው ባልተዘረጋበት አገር የተሳካ ምርጫ ማካሄድ አስቸጋሪ ነው:: አብዛኛው መራጭ ሕዝብ ወደሚኖርበት መንደር የሚደርስ መንገድና የትራንስፖርት አገልግሎት በሰፊው ካልተዘረጋ፣ ኤሌክትሪክና የኤሌክትሮኒክስ እንዲሁም የሕትመት ሚዲያ ሥርጭት ውስን ከሆነ፣ የስልክና የፖስታ አገልግሎት በሚገባ ካልተሟላ የምርጫ ተግባር ቀላል እንደማይሆን የታወቀ ነው:: የመራጩን ሕዝብ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ የሚከተል የአፈፃፀም ሥልትና ፕሮግራም ካልተቀየሰ በአፈፃፀም የሚሰለፍ በቂና የሠለጠነ የሰው ኃይል ማዘጋጀት ካልተቻለ፣ ለአፈፃፀም የሚረዱ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች በወቅቱ በሚፈለገው ጥራትና ብቃት በቦታው ተሟልተው ካልተገኙ የምርጫ ሥራን በተሳካ ሁኔታ ማካሄድ አይቻልም:: ነገር ግን እነዚህ ሁሉ አመቺ በሆኑበት አገርና ሁኔታ ሳይቀር ፖለቲካዊ አደረጃጀቱና የምርጫ ሥርዓቱ የማያሠራ ከሆነ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማድረግ ይከብዳል::

የተጠቀሱትና በምርጫ ተግባር ላይ ከባድ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ጉድለቶች ባሉበት አገርና ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ አደረጃጀትና ለዚያ አገር ልዩ ሁኔታ የሚስማማ የምርጫ ሥርዓት በቦታው ከተገኘ ከሞላ ጎደል የተሳካ ሊባል የሚችል ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ ይቻላል:: በኢትዮጵያ ሁኔታም የምርጫ ሥራን ፍሬቢስ ያደረገው ከባዱ ችግር ከዚሁ ዴሞክራሲያዊ ካልሆነ አደረጃጀትና ተስማሚነት ከሌለው የምርጫ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው:: በአገሪቱ ውስጥ ሥር ሰዶ የሚገኘውን አጠቃላይ ኋላቀርነትና ድህነት ደረጃ በደረጃ እየቀነሱ ወደተሻለ አቅጣጫ ለማምራት የሚያስችል የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዳይፈጠር መውጫ በሮችን ሁሉ ዘግቶ የቀለፈው ችግር ከፖለቲካ አደረጃጀቱና ከምርጫ ሥርዓቱ ጋር የተያያዘ ነው:: ስለዚህ የአገሪቱን ምርጫ አፈጻጸምና አሠራር ችግር ማየት የሚገባው በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ነው::

አሁን በአገሪቱ ያሉት የምርጫ አፈጻጸምና አሠራር ችግሮች እጅግ በርካታ እንደመሆናቸው ሁሉንም በዝርዝር ማቅረብ የማይቻል መሆኑ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም አይደለም:: ተገቢ ሊሆን የሚችለው አቀራረብ ጥቂት መሰረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንደ አብነት አንስቶ በማየት አጠቃላይ የችግሩን ሥፋትና ጥልቀት ለመገመት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው:: በዚህ ረገድ በቅድሚያ ሊነሳ የሚገባው የአፈፃፀም ችግር ከፍተኛ የቅንጅትና የማስተባበር ጉድለት መኖሩ ነው:: የምርጫ ሥራ የሁሉንም ዜጎች ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው:: የተለያዩ ተቋሞች ቡድኖችና ግለሰቦች በሠፊው ሊደግፉት የሚገባ ሥራ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የምርጫ ሁኔታ ደግሞ ከዚህ የተለየ ነው:: የምርጫ ሥራ ሥልጣን የያዘው ፓርቲና መንግሥት ኃላፊነት ብቻ እንደሆነ አድርጎ የመመልከትና ሌሎች አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ወገኖች ዳር ቆመው እንዲታዘቡ የመፈለግ ሁኔታ ይታያል:: ይኸ ችግር ከዕውቀት ማነስ ጋር የተያያዘ ቢሆንም በፍላጎትና ቅንነት ማጣትም የታጀበ ነው:: ብዙ ወገኖች ተሳትፎ የሚያደርጉበት ዕድል ከተፈጠረ በምርጫ ወቅት የሚሠራውን ማጭበርበርና ተንኮል ዜጎች የሚያውቁበት መንገድ ስለሚከፈት የምርጫን ሥራ በብቸኝነት ለማንቀሳቀስ ይፈለጋል:: የተለያዩ አቅም ያላቸውን ተቋሞች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች እያቀናጁ ከማሰማራትና ግልጽ በሆነ መንገድ ከማስተባበር ይልቅ ድርጅታዊ አሰራር በሚለው ድብቅ ዘዴ በየስርቻው ሕዝብ የማያውቃቸውና በምስጢር የሚሠሩ ማዘዣ ጣቢያዎችን እየፈጠሩ ነገሮችን ለማወሳሰብ ጥረት ይደረጋል:: በመንግሥት መገናኛ ብዙሃንና በነፃ ፕሬስ ተቋሞች መካከል የተቀናጀ እንቅስቃሴ እንዲኖር አይፈለግም:: እንደውም አንዱ ሌላውን በጥላቻ አይን እንዲመለከተው በመገፋፋት እርስ በርስ የሚቃረን መረጃ እያሰራጩ እንዲጠላለፉና ሕዝቡም ሀቁን መጨበጥ በማይችልበት ውዥንብር ውስጥ ገብቶ እስኪቸገር ድረስ ነገሮችን ለማሳከር ይፈለጋል:: በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ውስጥ እንኳ ቅንጅት እንዲፈጠር አይፈለግም:: ቴሌቪዥኑ የሚያቀርበውን የምርጫ መረጃ ሬዲዮ ያፈርሰዋል:: በሬዲዮ የሚቀርበው የምርጫ መረጃ በጽሑፍ ሚዲያ ከሚቀርበው ይቃረናል:: እውነተኛውን መረጃ መራጩ ሕዝብ እንዲያውቅ አይፈለግም::

የትምህርትና ምርምር ተቋሞች ተከታታይነት ባለው መንገድ የሲቪክ ትምህርት የሚሰጡበት የተቀናጀ አሠራር የለም:: ምርጫው ሊካሄድ አንድና ሁለት ወራት ሲቀሩ ከሚደረገው የተበታተነ ሽር ጉድ ባሻገር በሥርዓት የተደራጀና ተከታታይነት ያለው የሲቪክ ትምህርት የሚሰጥበት አቅጣጫ በሚገባ አልተተለመም:: በትምህርት ላይ ለሚገኙ ዜጎች የሚሰጥ የሲቪክ ትምህርት ፕሮግራም ተጀምሯል ቢባልም አጠቃላይ የአገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት በአንድ ፓርቲ ርዕዮተ ዓለም የተቃኘ ሆኖ በመዘጋጀቱ በሲቪክ ትምህርት ስም የተዘጋጀውም ፕሮግራም ለአንድ ፖለቲካ ቡድን ብቻ የሚጠቅም ፕሮፓጋንዳ እንጂ ዜጎችን በዴሞክራሲ አመለካከት የሚያንፅ ይዘት የለውም:: ዜጎች ስለምርጫ በግልጽ የሚወያዩበት፣ የሚከራከሩበትና ልምድ የሚለዋወጡበት ምቹ ሁኔታ የለም:: በዚህ ፋንታ ይኸንን የፖለቲካ ድርጅት ደገፋችሁ ያንን ተቃወማችሁ እየተባለ በገዥው ፓርቲ ካድሬዎችና ሰላዮች ብቻ ሳይሆን በምርጫ አስፈጻሚዎች ሳይቀር ዛቻና ማስፈራሪያ ስለሚደርስባቸው ነጻ ስሜት የላቸውም:: ምርጫ በደረሰ ቁጥር ኢትዮጵያዊያን ለከባድ ሰብዓዊ መብት ረገጣና ስቃይ ይጋለጣሉ:: በዚህም የተነሳ ምርጫ የሚል ነገር ጨርሶ ባይኖርና ስሙም ባይጠራ የሚፈልጉ ጥቂት አይደሉም:: በምርጫ ሰሞን ፖሊስ ጣቢያዎች ብቻ ሳይሆኑ የቀበሌ ጽህፈት ቤቶችም ወደማጎሪያ ጣቢያነት ይቀየራሉ:: ፖሊሱ፣ ካድሬው፣ የደህንነት ሠራተኛው፣ የቀበሌ ተመራጩ፣ የገዥው ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሳይቀሩ የፈለጉትን ዜጋ እያነቁ እስር ቤት በማስገባት ዘመቻ ይሰማራሉ:: በአገሪቱ የምርጫ ስራ የሚካሄድ ሳይሆን የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ የታወጀ ነው የሚመስለው:: ለወጉ የምርጫ አፈጻጸም አዋጅ የወጣ ቢሆንም የምርጫ አስፈፃሚ አካሉ የሚመራው ባልታወጀውና ድርጅታዊ ሥራ እየተባለ በሚታወቀው ድብቅ አሠራር ነው::

በአሁኑ አገዛዝ ሥር ካሉት ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ አሠራሮች መካከል በቅንጅት ጉድለቱ፣ በግልጽነት ማጣቱና በአድሏዊነቱ ከምርጫ አስፈፃሚ ተቋሙ ጋር የሚስተካከል የለም:: የኢትዮጵያን ምርጫ ለማስፈፀም በአዋጅ ሥልጣን የተሰጠው ተቋም በምርጫ ወቅት ዜጎች በነፃነት እንዲመርጡና እንዲመረጡ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የማድረግ አቅም ብቻ ሳይሆን ፍላጎት እንደሌለው በተግባር ታይቷል:: ምርጫን ሰበብ እያደረጉ ሥልጣን ላይ ያለው የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት፣ ገዥው ፓርቲና አባላቱ በዜጎች ላይ ሕገወጥ ወንጀል በአደባባይ ሲፈጽሙ እንዳላየና እንዳልሰማ ፀጥ ይላል:: የመራጩን ነፃ ውሳኔ እየተጋፋ የሚፈልገውን እንዳይመርጥ ግልጽ ተፅዕኖ ሲፈጽሙበት፣ ድምጹን ሲቀሙትና የድምፅ መስጫ ኮሮጆዎችን ከምርጫ ጣቢያ እየነጠቁ ሲወስዱ ትንፍሽ አይልም:: ይኸንን ጥፋት በፈጸሙ ላይ

ፖሊስ ክትትል እንዲያደርግ፣ አቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሠርት፣ ፍርድ ቤት ዳኝነት እንዲያይ ጥያቄ ማቅረብ አይፈልግም:: የመገናኛ ብዙሃንና ታዛቢዎች የሚፈፀመውን ጉድለት ይፋ እንዲያደርጉና ለሕዝብ እንዲያሳውቁ መረጃውን አይሰጥም:: ገዥው ፓርቲ የሚሰጠውን ትዕዛዝና መመሪያ እየተቀበለ የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ጉዳይ ሲያስፈፅም ይከርምና በመጨረሻ ጊዜ የምርጫውን ውጤት ተቀብሎ ያፀድቃል:: በምርጫ ተግባር እያንዳንዱ ተቋም፣ ቡድንና ግለሰብ በሕግ የተሰጠውን መብትና ግዴታ ጠብቆ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል ግልፅ አሠራር የለም:: እንዲሁም የምርጫው ተግባር ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ እንዲፈፀም አስተዋፅኦ ሊያደርጉ በሚገባቸው መካከል የተቀናጀ አሠራር አይታይም:: በምርጫው ተግባር እንዲኖር የሚፈለገውን ቅንጅት የሚፈጥርና ነጻና ትክክለኛ በሆነ የምርጫ ሥርዓት ላይ ተመሥርቶ የመራጩን ሕዝብ ድጋፍ ያገኘ የፖለቲካ ሥርዓት በአገሪቱ ለማቋቋም አልተቻለም::

በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው ምርጫ ከሚታዩት የአፈጻጸምና አሠራር ጉድለቶች መካከል ሊጠቀስ የሚገባው ሌላ ነጥብ ሕገ-መንግሥቱ የደነገጋቸውን ሕጋዊ ሥርዓቶች ለማስፈፀም የሚያስችሉ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች አለመኖራቸው ነው:: በአንድ በኩል አዋጆች ፀድቀው ከመውጣታቸው በፊት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ወገኖች እንዲመክሩባቸውና ሃሳብ እንዲሰጡባቸው የሚያስችል ምቹ መድረክ እየፈጠሩ በጥንቃቄ በማዘጋጀት ረገድ ከፍተኛ ችግር አለ:: በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን ላይ ያለውን ፓርቲ የፖለቲካ አጀንዳ ለማሳካት ሲባል በቂ ዝግጅት ሳይደረግባቸው በችኮላ የሚወጡ አዋጆች አንዳንድ ጊዜ የሕጎች ሁሉ የበላይ ነው የሚባለውን ሕገ መንግስት የሚቃረኑበት ሁኔታ አለ:: ሕገመንግስቱን የሚቃረን ይዘት ካላቸው አዋጆች መካከል አንዱ የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግሥት ጋር ለማጣጣም የወጣው አዋጅ ቁጥር 111/1987 ነው:: ይህ አዋጅ በአጠቃላይ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚቃረን ይዘት ያለው ቢሆንም ሁለት ጉዳዮችን ብቻ እንደማስረጃ በማቅረብ በሕገ-መንግሥቱና በአዋጁ መካከል ያለውን ቅራኔ ማሳየት ይቻላል:: የመጀመሪያው ነጥብ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ 5 እንደተገለፀው የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደሚወስን የተደነገገ ቢሆንም አዋጅ ቁጥር 111/1987 ደግሞ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የምርጫ ክልሎችን የሚወስነው የተወካዮች ምክር ቤት እንደሚሆን ተቀምጧል:: ይኸ ሥልጣን ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ወደተወካዮች ምክር ቤት የተዛወረው ከሕገመንግስቱ ድንጋጌ ጋር በሚጻረር መንገድ ነው:: ሕገ-መንግሥቱ በግልፅ ለይቶ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ብቻ የሰጠውን ሥልጣን በአዋጅ ወደሌላ አካል የተዛወረበት ሁኔታ የተገለፀ ባይሆንም ምንአልባት ለሁለቱ ምክር ቤቶች ስለምርጫ ክልል አወሳሰን በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠውን የጋራ ሥልጣን መሠረት አድርጎ የተፈፀመ ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ እንዳይኖር ይኸንን መንፈስ ያዘለ ሕገ-መንግሥታዊ ደንጋጌ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የለም:: የተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ሕጎችን የማውጣት ሥልጣን እንዳለው በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል «መ» መደንገጉ የሚታመን ቢሆንም ለአንድ ሕጋዊ አካል በግልጽ ተለይቶ የተሰጠን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት መቀማት ግን በሕግ የተፈቀደ አይደለም:: በሕገ-መንግሥቱ ለሁለቱ ምክር ቤቶች በተሰጣቸው የጋራ ሥልጣን ላይ ተመሥርቶ የተፈፀመ ቢሆን እንኳ በዚህ መንፈስ ግልጽ ሆኖ መውጣት ሲገባው አዋጁ የምርጫ ክልሎችን መወሰን የተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣን ብቻ እንዲሆን አድርጎ መደንገጉ ሕገ-መንግሥቱን የሚቃረን ከመሆን አያግደውም::

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል «ሀ» እስከ «ሐ» በተደነገገው መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዳለው የታወቀ ነው:: ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 111/1987 ይኸንን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በማጥፋት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 በፊደል ተራ «ለ» እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው በዕጩ ተወዳዳሪነት ለመመዝገብ የሚችለው የሚወዳደርበትን ብሔራዊ ክልል ቋንቋ ካወቀ መሆኑ ተገልፆል:: የምርጫ አስፈጻሚ ተቋሙ ሕገ-መንግሥቱ ያረጋገጠውን መብት ወደጎን በመተው ይኸንኑ በሚፃረር ሁኔታ የወጣውን አዋጅ በጥብቅ ለማስፈፀም ሲል በተለያዩ ምርጫዎች ተወዳዳሪ ሆኖ ለመመዝገብ ዜጎች ያቀረቡትን ጥያቄ ውድቅ እንዳደረገ ይታወቃል:: በእነዚህ በተጠቀሱት የአዋጁ አንቀጾች ላይ ብቻ እንኳ በመመሥረት አዋጅ 111/1987 ሲገመገም በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተደነገገው ሕገ-መንግሥቱ የአገሪቱ የበላይ ሕግ በመሆኑና ማንኛ ውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ

ሕገ-መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት ስለማይኖረው ሕገወጥ አዋጅ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

ይህ አዋጅ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር ተቃራኒ ይዘት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ደግሞ ገዥውን ፓርቲ ለመደገፍ በሚያስችል አፈጻጸም የሚታገዝ መሆኑ ሌላው የአሠራር ችግር ነው፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 በፊደል «ሠ» እንደተደነገገው በዕጩነት የሚመዘገብ የፖለቲካ ፓርቲ በሚወዳደርበት ክልል ከ500 የማያንስ የሕጋዊ መራጮች የድጋፍ ፊርማ፣ በግሉ የሚቀርብ ተወዳዳሪ ደግሞ ከአንድ ሺህ የማያንስ የሕጋዊ መራጮች የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ እንዳለበት በግልፅ ሰፍሯል፡፡ ይሁን እንጂ በገዥው ፓርቲ የቀረበ ሲሆን ተገቢው ሕጋዊ ማጣራት ሳይደረግ ተመዝግቦ የዕጩነት መታወቂያ ካርድ ይሰጣል፡፡ በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በግል ለሚቀርቡ ዕጩዎች ሲሆን ግን አላስፈላጊ በሆነ ውጣ ውረድ እንዲንገላቱ ይደረጋል፡፡ በዕጩዎች ምዝገባ ላይ የሚነሱ አቤቱታዎች በወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ውሳኔ ስለማያገኙ ለዞን፣ ለክልል ምርጫ አስፈጻሚ፣ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እየቀረበ በተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎችና በግል የሚቀርቡ ዕጩዎች የሚያባክኑት ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በፖለቲካ ሹመት የተመደበ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም የመንግስት አስተዳደር የሚያገለግል የአስተዳደር ሠራተኛ፣ ዳኛ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወታደር ወይም ፖሊስ በራሱ ወይም በፖለቲካ ፓርቲ አማካይነት ዕጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ቢቀርብ የያዘውን የመንግሥት ሥራ እንደሚለቅ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አንቀጽ በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በአንዳንድ የግል ተወዳዳሪዎች ጥብቅ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ሲደረግ በገዥው ፓርቲ እጩዎች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ ይልቁንም የገዥው ፓርቲ እጩዎች ከመንግስት የሚከፈላቸው ደሞዝ ሳይጓደል፣ ከመንግስት ካዝና ወጪ በሚደረግ ገንዘብ የውሎ አበል እየተከፈላቸው፣ የመንግሥት መኪናና ነዳጅ እየተጠቀሙ የምርጫ ውድድር ያደርጋሉ፡፡ በዚሁ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት የመንግሥት ሠራተኞች በመንግሥት አገልግሎት ላይ ባሉበት ጊዜ በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የበላይ አመራር አካል የኃላፊነት ቦታ መያዝ እንደማይችሉና በፖለቲካ ውድድር ጊዜ ማንኛውንም ተወዳዳሪ ለማስመረጥ በመደገፍ በመናገር፣ በመፃፍና በመሳሰሉት ተሳታፊ እንደማይሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህም ረገድ ግጼታው የሚፀናባቸው በተቃዋሚ ፓርቲዎችና አንዳንድ በግል የሚቀርቡ ተወዳዳሪች ላይ ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ አባሎችማ መደገፍ፣ መናገርና መጻፍ ብቻ ሳይሆን በምርጫ ሰሞን ከአበል ክፍያ ጋር የእረፍት ፈቃድ እየተሰጣቸው የመራጩን ሕዝብ እጅ በመጠምዘዝና የድምጽ ኮረጆዎችን በመገልበጥ ግዳጅ በግልፅ ይሰማራሉ፡፡ የዚህ አንቀጽ ችግር የዜጎችን የመምረጥና የመመረጥ እንዲሁም የፈለጉትን አመለካከት የመከተልና የፈለጉት ድርጅት አባል የመሆን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በመቀማት ሳይወሰን ይኸንኑ ሕገወጥ ድንጋጌ እጅግ በሚያሳፍር አድሎ ገዥውን ፓርቲ በሚጠቅምና ተቃዋሚዎቹን ብቻ ለይቶ በሚጎዳ አሠራር ተፈጻሚ የሚሆንበት ሁኔታ መኖሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገው ምርጫ ትክክለኛ እንዳልሆነ በሚገባ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በአዋጅ አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1 ዕጩዎች ከባድ የወንጀል ድርጊት ፈጽመው ካልሆነ ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስኪጠናቀቅ ድረስ እንደማይያዙ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች የምርጫ ወቅት እየተጠበቀ ሕጋዊ ባልሆነ ሥርዓት ይታሰራሉ፣ ይገረፋሉ፣ ግድያ ሳይቀር ይፈጸምባቸዋል፡፡ ለምን እንደታሰሩ ጥያቄ ሲቀርብ ብዙ ጊዜ የሚሰጠው መልስ የቤት ኪራይና የመሬት ግብር ስላልከፈሉ፣ ብድርና የማዳበሪያ እዳ ስላልከፈሉ የሚል ነው፡፡

በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 1 የምርጫ ውድድር መጠናቀቅ ያለበት ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ ከሁለት ቀናት በፊት እንደሆነ ቢደነገግም የገዥው ፓርቲ ዕጩዎች ውድድር የሚጠናቀቀው በፈለገው ዓይነት መንገድ የፓርላማ ወንበር ማግኘታቸው ሲታወቅ ብቻ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 1 ማንኛውም ዕጩ ወይም ደጋፊ የመናገር፣ የመጻፍ፣ ደጋፊዎችን የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማደራጀት፣ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች የመጠየቅና የማግኘት መብት እንዳለው ቢደነገግም የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች ይኸንን መብት ለመጠቀም እጅግ ከባድ ፈተና ያጋጥማቸዋል፡፡ መሰብሰብ በህገ መንግስት በማንም የማይሰጥና የማይነጠቅ የዜጎች መብት ሆኖ የተደነገገ ቢሆንም ከዚህ ድንጋጌ በሚቃረን ሁኔታ በተቋቋሙ የፈቃድ ቢሮዎች ተቃዋሚዎች የስብሰባ አዳራሽና የስብሰባ ፈቃድ ለማግኘት ውስብስብ በሆነ የቢሮክራሲ

ውጣውረድ ማለፍ ይኖርባቸዋል:: መረጃ ጠይቆ ለማግኘት ደግሞ ጨርሶ የማይቻል ነው:: የመንግሥት ኃላፊዎች ለተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎች መረጃ መስጠትን እንደውርደት ይቆጥሩታል::

እንደገና በአዋጁ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉትን መገናኛ ብዙሃን ማለትም ሬዲዮን ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን የፖለቲካ ድርጅቶችና የዕጩዎች ደጋፊ የሆኑት የሕብረተሰብ ክፍሎች ያለ አድሎ ለመጠቀም መብት እንዳላቸው ቢደነገግም ተግባራዊ ሆኖ አያውቅም:: በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ዕጩዎች በመገናኛ ብዙሃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት እንዳላቸው ቢደነገግም ለታይታ ያህል የ5 ደቂቃ የአየር ጊዜ ተፈቀደ ከመባሉ በስተቀር ተግባራዊ አልተደረገም:: በነፃ የአየር ጊዜ መጠቀም ቀርቶ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ገንዘብ ከፍለው የአየር ጊዜ ለማግኘት የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ:: መተላለፍ የሚገባ ሃሳብ ጊዜ ካለፈበት በኋላ ወይንም ለአድማጭ የማይመች የሥርጭት ሰዓት እየተመረጠ ይተላለፋል:: በሚተላለፍበት ጊዜ ደግሞ ሃሳቡ እየተቆራረጠ፣ ትርጉም በማይሰጥና የተዛባ ግንዛቤ በሚያስጨብጥ መንገድ እየተዘበራረቀ እንዲተላለፍ ይደረጋል:: የገዥው ፓርቲ ዕጩዎች ሃሳብ ግን መደበኛዎቹ የስርጭት ፕሮግራሞች እየታጠፉ፣ ተስማሚ የሆነ የሥርጭት ጊዜና ረጅም የሆነ ሰዓት እየተመደበላቸው ለሳምንታትና ለወራት በተከታታይ መንገድ ይሰራጫሉ:: የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ለገዥው ፓርቲ ዕጩዎች የተለየ ድጋፍ ማድረጋቸው ሳይበቃ የተቃዋሚ ፓርቲዎችንና ዕጩዎቻቸውን በሚጎዳ ሁኔታ በእቅድ የተዘጋጀ የማጥላላት ፕሮግራም ከፍተው የተቀነባበረ ዘመቻ ያካሂዳሉ::

በአዋጁ አንቀጽ 51 ደግሞ በማናቸውም ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አካላትና ኃላፊዎች የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ እንዲሳካ ለማድረግ በየኃላፊነታቸው ሥር የሚገኙትን ሬዲዮ ጣቢያዎች፣ የስብሰባ አዳራሾች፣ ጋዜጦችና የመሳሰሉትን ዕጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ያለ አድሎ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ እንዳለባቸው በሚል የተደነገገ ቢሆንም ሚዲያዎችንና የስብሰባ አደራሾችን በኃላፊነት የሚቆጣጠሩት የገዥው ፓርቲ ግንባር ቀደም ካድሬዎች እንደመሆናቸው ሕጉ ተፈጻሚ የሚሆንበት እድል የለም:: የትኛው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ካድሬ ነው የራሱን ፓርቲ ለሚቃወሙ ፓርቲዎችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሚዲያና የስብሰባ አዳራሽ ያለ አድሎ እየፈቀደ ነፃ የውድድር ሜዳ የሚያዘጋጀው? እንዲህ ዓይነት ቅንነትና የኃላፊነት ስሜት አሁን ሥልጣን ላይ ካለው ገዥ ፓርቲ ሊገኝ ቀርቶ ሊታሰብ የሚችል ነገር አይደለም:: የፖለቲካ ሥራ ለጽድቅ ተብሎ የሚከናወን ባይሆንም እንኳ ተቀባይነት ባላቸው የሕግ ሥርዓቶችና የሞራል ኃላፊነቶች መመራት የሚገባው ትልቅ ተግባር መሆኑ አይካድም:: ሕወሓት /አሕህአዴግ ደግሞ በሕጋዊ ሥርዓቶችና ሚዛናዊ በሆነ የኃላፊነት ስሜት የሚመራ ተግባር ለመፈፀም የሚያስችል ተፈጥሯዊ ባሕሪና አቅም የሌለው መሆኑ የሚታወቅ ነው:: በመንግሥትና በሕዝብ ቁጥጥር ሥር የሚገኙትን የሚዲያ ዘርፎችና የመሰብሰቢያ አዳራሾች በፈለገው ጊዜና በፈለገው መንገድ በነፃ ለመጠቀም ከልካይ የሌለበት ገዥው ፓርቲ እነዚህን አገልግሎቶች በገንዘቡ፣ በጉልበቱና በእውቀቱ ያቋቋመና አሁንም በሚከፍለው ግብርና ልዩ ልዩ መዋጮ የእነዚህን ተቋሞች ሕልውና እየጠበቀ የሚገኝ ሕዝብ በክፍያ እንኳ ለመጠቀም ሲጠይቅ የእምቢተኝነት መልስ መስጠቱ ሕግ የማይገዛውና የኃላፊነት ስሜት የሌላው ለመሆኑ ጥሩ ማስረጃ ነው:: የምርጫ ሕጉን ቀርቶ ሕገ-መንግሥቱንም እንደሚጨፈልቅ በብዙ ማስረጃ የታየ ነው::

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 1 ዕጩዎችን ካቀረበ ፓርቲ በቀረበለት አቤቱታ መሠረት በምርጫው ሂደት አዋጅን የሚጥስ ድርጊት ለመፈጸሙ በቂ መረጃ ካገኘ ድርጊቱ እንዲቆም ቦርዱ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ተደንግጓል:: ነገር ግን ከአንድ ሺህ አንድ ጊዜ በላይ አቤቱታ ቢቀርብለትም የገዥውን ፓርቲ አሸናፊነት የሚያዳክም ስለሚመስለው ትዕዛዝ አይሰጥም:: ነፃ ተቋም ባለመሆኑም ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችል አቅም የለውም:: እንዲህ አይነት ድርጊት ቢፈጽም ደግሞ እንደተቋም ሕልውናውን ጠብቆ ሊቀጥል እንደማይችል ይታወቃል::

አንዳንድ ጊዜ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ተአምር ከተፈጠረ የተፈፀመው ድርጊት እንደአጋጣሚ የአበዳሪ መንግሥታትና ለጋሽ ድርጅቶችን ትኩረት የሚስብ ሆኖ ከተገኘና የእነርሱ ግፊት ከበረታ ብቻ ነው:: ለዚያውም የተፈፀመው ድርጊት በመላ አገሪቱ በሚገኙ በሁሉም የምርጫ ክልሎች ሆኖ ሳለ የቦርዱ ትዕዛዝ የሚሰጠው የገዥውን ፓርቲ አሸናፊነት ጥያቄ ውስጥ እንደማይጥሉ በሚያምንባቸው የተመረጡ ጥቂት የምርጫ ክልሎች ብቻ ነው:: ሌላው ቀርቶ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን በመጣስ የሚፈጸምና የምርጫ ሂደትን

የሚያደናቅፍ ባሕሪ ያለው ተግባር ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ቦርዱ ጉዳዩን ወደሚመለከተው አካል ሊመራው እንደሚችል መደንገጉ እየታወቀ በምርጫ ሰበብ ንጹሃን ዜጎችን የገደሉ፣ ከሕግ ውጭ አስረው ሰቆቃ የፈፀሙ፣ ንብረት የዘረፉ፣ ቤት ያቃጠሉ፣ ለስደት የዳረጉና ሴቶችን አስገድደው የደፈሩ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎችና ታጣቂዎች በሕግ እንዲቀጡ ለማድረግ አልቻለም።

ማንኛውም መራጭ ድምፅ ለመስጠት የሚችለው በመራጭነት በተመዘገበበት የድምፅ መስጫ ጣቢያ ብቻ መሆኑ በአዋጁ የተደነገገ ቢሆንም በገጠሩ የአገሪቱ ክፍል የምርጫ አስፈፃሚዎቹ በሚመቻቸው የትኛውም ሥፍራ ድምፅ እንደሚያስጡ የታወቀ ነው። የድምፅ መስጫ ሰዓቱም ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ከጧቱ 12 ሰዓት እስከምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ እንደሚሆን በአዋጁ በግልፅ ተቀምጧል። ይሁን እንጂ አንዳንድ የውጭ ታዛቢዎች ሊደርሱባቸው ከሚችሏቸው ትላልቅ ከተሞች ውጭ ያሉ ብዙዎቹ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከቦርዱ ውሣኔ ሳይደርሳቸው በራሳቸው ፈቃድ ለቀናት እንዲቀጥል ያደርጉታል።

በአዋጁ አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 1 ለምርጫ ማስፈፀም ሥራ ከተሰማሩት በስተቀር መራጮች ያልሆኑና ድምፃቸውን የሰጡ ሰዎች ከድምጽ መስጫ ጣቢያው ክልል ውስጥ መገኘት እንደሌለባቸው ተደንግጓል። የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች በመንግሥት አስፈፃሚ አካል ውስጥ ሥልጣን ያላቸው ኃላፊዎችና የኮር አባላት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን ሙሉ በሙሉ በሚቆጣጠሩበትና በጣቢያው ውስጥ በአካል ተገኝተው ማን ለማን ድምፅ እንደሚሰጥ እየተመለከቱ ለፓርቲያቸው ድምፅ የሚሰጠውንና ተቃዋሚዎችን የሚመርጠውን ለይተው ለማወቅ በሚችሉበት አሠራር የድምፅ አሰጣጥ ተግባር ይከናወናል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ማንኛውም ሰው ከድምፅ መስጫ ጣቢያው በአምስት መቶ ሜትር ዙሪያ ክልል ውስጥ መሣሪያ በመያዝ ወይም ፀጥታን በሚያደፈርስ አኳኋን መገኘት እንደሌበት ተደንግጓል። የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ዕጩ ተወዳዳሪዎችና የኮር አባላት ግን ይህንን አያከብሩም እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን ደህንነት ለማስከበር የፖሊስ ኃይል እንዲመደብላቸው የሚመለከተውን አካል እየጠየቁ እንደሚያሰማሩ ተደንግጓል። ይሁን እንጂ የሚመደበውን ኃይል የድምፅ መስጫ ጣቢያውን ደህንነት ለማስከበር ሳይሆን የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ዕጩ ተወዳዳሪዎች አባላትና ደጋፊዎች በማንገላታት ተግባር እያሰማሩ የዜጎችን መብት በሚረግጥ አኳኋን ይጠቀበሙታል።

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 63 መሠረት ጋዜጠኞች የመለያ ማስረጃቸውን ከያዙና ድምፅ የመስጠቱን ሂደት የሚያደናቅፍ ተግባር እስካልፈፀሙ ድረስ ወደድምፅ መስጫ ጣቢያዎች እንዲገቡ ይፈቀድላቸዋል። ነገር ግን በዚህ አዋጅ የመንግስትና የገዥው ፓርቲ ጋዜጠኞች እንዲጠቀሙ ሲፈቀድ ለግል ጋዜጠኞች ክልከላ ይደረጋል።

በአዋጁ አንቀጽ 65 ንዑስ አንቀጽ 1 ምርጫው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ቆጠራ በድምጽ መስጫ ጣቢያ እንደሚደረግ የተደነገገ ቢሆንም የገዥው ፓርቲ ካድሬዎችና በምርጫ አስፈፃሚነት ተመድበው የሚሠሩት የኮር አባላት በፈለጉት ቦታና ጊዜ በድብቅ ቆጠራ ያካሂዳሉ። በዋና ዋና ከተሞች ውስጥ ሳይቀር የዚህ ዓይነቱ ድርጊት በተደጋጋሚ ሲፈፀም የታየ ነው። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በድምፅ መስጫ ጣቢያ የተደረጉ ቆጠራዎች ውጤት ወዲያውኑ ለሕዝብ በይፋ እንደሚገለፁና በወረዳ የተደረጉ ቆጠራዎች ውጤት መቼ ለሕዝብ ይፋ እንደሚደረጉ የተደነገገ ቢሆንም በግድም ሆነ በውድ ማለፍ የሚገባው የገዥው ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪ የሚያሸንፍበት ሁኔታ እስኪመቻች ድረስ ይፋ አይደረግም።

ለዚህ ጥሩ ማስረጃ የሚሆነው በ1992 ዓ.ም ተካሂዶ በነበረው የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አባልነት በሚኖሩበት የምርጫ ክልል ተወዳድረው የነበሩትና በዚያ ጊዜ የከተማው መስተዳድር ሊቀመንበር የነበሩት የገዥው ፓርቲ ካድሬ የተመረጡበት ሁኔታ ነው። እኒህ ግለሰብ በተወዳደሩበት የምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኙ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች የተደረጉ የድምጽ ወረቀት ቆጠራዎች ተጠቃለው ውጤቱ ለወረዳው ምርጫ ድሕፈት ቤት እንዲደርስ ተደረገ። በወረዳ ደረጃ ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ ማለፍ የሚያስችላቸውን ድምፅ ሳያገኙ ቀሩ። የተቃዋሚ ፓርቲዎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ራሱ ገዥው ፓርቲ ያቀረባቸው የተወሰኑ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ሳይቀሩ ከእርሳቸው የበለጠ ድምፅ አገኙ። ነገር ግን ገዥው ፓርቲ የሚፈልገው በሕዝብ ድምፅ የተመረጡትን ሳይሆን ይኸንን

ግለሰብ ስለነበር የምርጫው ውጤት ይፋ መሆኑ ቀርቶ አስፈፃሚዎቹ ውጤቱን «በድርጅታዊ ሥራ» ለመቀየር በሚቻልበት አሳፋሪ ተግባር ተጠመዱ:: ከአራት ቀን መዘግየት በኋላ በምርጫ አሸናፊ የሆኑትን የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎችና የተሰወሩ የገዥው ፓርቲ ዕጩዎችን በመጣል ገዥው ፓርቲ የሚፈልጋቸውን ግለሰብ እንዲያልፉ በማድረግ የመራጩን ድምፅ ቁጥር ከሕግ ውጭ ቀይረው መዘገቡት:: በዚህ መንገድ «ተመረጡ» ተባለና በድጋሚ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ሊቀመንበርነቱ ሥልጣን ተሰጣቸው:: ሥልጣኑን በድጋፍ የወሰዱት ግለሰብ ሁለት ዓመት ከአራት ወራት ገደማ እንደቆዩ ገዥው ፓርቲ «በፀረ-ዴሞክራሲ፣ በፀረ-ልማት፣ በፀረ-ኢንቨስትመንት» ጥፋት ወንጀለኛ አደረጋቸው:: ሕዝብ የፈለገውን ሳይሆን ገዥው ፓርቲ የፈለገውን ሥልጣን ላይ እንደሚያስቀምጥና ሳይፈልጋቸው ሲቀር ደግሞ መራጩን ሕዝብ ሳያማክር እየወረወረ እንደሚጥል ከዚህ ግለሰብ የተሻለ ማስረጃ የለም::

በአፈፃፀም ረገድ መነሳት የሚገባው ሌላው ነጥብ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 7 «ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል::» የሚለውን አንቀጽ በሥራ ላይ ለማዋል የወጣው አዋጅ አፈፃፀም ነው:: አዋጅ ቁጥር 88/1989 የወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴክሞራሲያዊ ሪፑብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በመራጮቻቸው አመኔታ በማያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ የወጣ አዋጅ ነው:: በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 አንድ ተመራጭ የመራጮች አመኔታ የለውም የሚልባቸው ሁኔታዎች ተደንግገዋል:: እነዚህ የአዋጁ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑትም የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት እንደሚሆን በተገለጸው መሠረት ደንብ ቁጥር 2/1991 ወጥቷል:: ይህ ደንብ በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤቶች አባላት የመረጣቸውን ሕዝብ አመኔታ በሚያጡበት ጊዜ ከአባልነት የሚያግድበትን የአፈፃፀም ስርዓት ለመወሰን የወጣ ነው:: ቀደም ሲል አዋጅ ቁጥር 88/1989 በሚወጣበት ጊዜ በተለይም በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 «አንድ ተመራጭ አመኔታ የለውም ሊባል የሚችለው በተወከለበት የምርጫ ክልል በሚገኙ 10,000 (አሥር ሺህ) መራጮች አሳሳቢነት የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የወረዳ ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምፅ ተወካዩ ተመልሶ እንዲጠራ ውሳኔ ያሳለፉ እንደሆነ ነው» የሚለው አወዛጋቢ ነበር:: አወዛጋቢ የሆነውም የወረዳ ምክር ቤቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ እንዲሰጡ የተደረገበት ሁኔታ በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ የያዘ ፓርቲ የተቃዋሚውን ፓርቲ ተወካዮች ወይም የማይፈልገውን የሕዝብ ተመራጭ ለማገለል ሊጠቀምበት ይችላል የሚለው ስጋት ነበር:: እንደገና ቦርዱ ይኸንን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ ያወጣው የአፈጻጸም ሥርዓት ደንብ ቁጥር 2/1991 ግልፅነት የጎደለውና አሻሚ ለሆነ አተረጓጎም የተጋለጠ ሆኖ ተዘጋጅቷል:: የነበረው ሥጋት ትክክለኛነትም ከሕወሃት በተባበሩት 9 የፓርላማ አባላት ላይ የተወሰደው እርምጃ አረጋግጧል::

በምርጫ አፈፃፀም ላይ እኩል የውድድር እድል እንዳይኖር መሰናክል ከሚሆኑት ምክንያቶች አንዱና ዋናው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለባቸው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ነው:: መንግስት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድጎማ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት በህግ የተደነገገ ቢሆንም እስካሁን ይህንን ኃላፊነቱን ተወጥቶ አያውቅም:: ተቃዋሚዎች ከማንኛውም የውጭ መንግስት፣ ድርጅትና ዜጋ ማንኛውንም እርዳታ እንዳይቀበሉ በህግ ታግደዋል:: የኢትዮጵያ ህዝብ ተቃዋሚዎችን በገንዘብ ረድቶ ማጠናከር ይቅርና ለራሱም ዳቦ ገዝቶ ለመብላት ተቸግሯል:: ፓርቲዎችን ለመርዳት አቅም ያላቸው ጥቂት የህብረተሰብ ክፍሎች ቢኖሩም የገዥውን ፓርቲ ተጽዕኖ በመፍራት በሰቀቀን የሚኖሩ ናቸው:: አንድ ፓርቲ ያለገንዘብ አቅም በየከተሞቹና በገጠር አካባቢዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች ከፍቶ፣ ህዝቡን በብቃት አደራጅቶና በብቃት ቀስቅሶ በምርጫ ብቁ ተወዳዳሪ ሊሆን አይችልም:: የንግድ ድርጅቶች ከፍቶ በብዙ ቢሊየን ብር የሚነግድና የህገሪቱን ሁለንተናዊ ሀብት በብቸኝነት የተቆጣጠረ ኃይል አንድ ብስክሌት ከሌላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በምርጫ እየተወዳደረ በዚህ አገር ነፃና ፍትሃዊ የምርጫ ሂደት ማየትም ሆነ ዴሞራሲያዊ ስርዓትን መገንባት አይቻልም::

ከዚህ ሌላ ጎልቶ የሚታይ የአፈፃፀም ችግር ምርጫውን የሚታዘብ የአገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎችን በሚመለከት የሚደረገው ተፅዕኖ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል የዴሞክራሲ ሥርዓት ባለመኖሩ የምርጫውን ሂደት የሚታዘቡ አካላት ተሳትፎ እንዲኖርና እውነቱን ሕዝብ በይፋ እንዲያውቀው በማድረግ እገዛ እንዲያደርጉ በተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል ከፍተኛ ፍላጎት አለ:: ዓለም-አቀፉ ሕብረተሰብም ታዛቢዎችን እየመደበ የኢትዮጵያ ምርጫ ሂደት እንዲከታተልና ለዴሞክራሲ ሥርዓት መፈጠር የበኩሉን

አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ጉጉት አለ:: በዘመናችን አስተሳሰብ ዴሞክራሲን በአንድ አገር የመፍጠር ጥያቄ ዓለም-አቀፍ ትርጉም ያለውና የሁሉንም ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑ ተቀባይነት አግኝቷል:: ምክንያቱም የአንድ አገር ሕዝብ ዴሞክራሲ ሲያጣ የሚከተለው የሰላም መጥፋትና የልማት ዕድል መዘጋት ጉዳቱ በዚያ አገር ተወስኖ የሚቀር እንዳልሆነ የታመነበት በመሆኑ ነው:: ችግሩ ለጎረቤት አገሮች፣ ለአህጉርና ለአለም መትረፉ የማይቀር ነው:: የዓለምን ሰላም፣ ደህንነትና ልማት የመንከባከብ ኃላፊነት ያለበት አለም አቀፉ ሕብረተሰብ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ መካሄዱን መታዘብ ይኖርበታል:: የዚህ ዓይነቱን ሚና በሌሎች አገሮች እንደሚጫወትና ጠቃሚ ውጤትም እንዳስገኘ ይታወቃል:: በአገራችንም በግንቦት 1992 ከተካሄደው የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ በፊት በተካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ መልካም ተሳትፎ ያደረገ ቢሆንም በ1992 ምርጫ የመንግሥት ፈቃደኝነትና ተባባሪነት በመጥፋቱ የዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ተሣትፎ ተገድቧል:: አገር ውስጥ ያሉት የውጭ ዲፕሎማቶች የተወሰነ ሙከራ ማድረጋቸው ባይቀርም በአገሪቱ የመልክዓ ምድር ስፋትና በእነሱም በኩል ባለው የሰው ኃይል ውስንነት በሚፈለገው መጠን የአገሪቱን የምርጫ ሂደት ሙሉ በሙሉ ለመታዘብ አልቻሉም:: የምርጫን ሂደት በመታዘብ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውና በሚያቀርቡት ትክክለኛ መረጃ ትልቅ ከበሬታ ያገኙ ተቋሞች፣ የመንግሥታት ተወካዮች፣ ዓለም-አቀፍ የሰው ልጅ መብት ተንከባካቢ አካላት፣ ፈቃደኛ ቡድኖችና ግለሰቦች ወደ አገር ወስጥ ገብተው ለመታዘብ ፍላጎት ቢያሳዩም መንግሥት እንዲገቡ ሊተባበር ባለመቻሉ የግንቦቱ 1992 አገር-አቀፍ ምርጫ ብቁ ታዛቢዎች በሌሉበት ሁኔታ ተካሂዶ በሚያሳዝን ሁኔታ ተጠናቀቀ:: ቀደም ሲል እንደተገለፀው በአገር ውስጥ የሚገኙ የውጭ አገር ዲፕሎማቶች ካደረጉት ተሣትፎ ሌላ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ ጥረት ቢያደርግም በመላ አገሪቱ የተካሄደውን ምርጫ የሚሸፍን እንቅስቃሴ ለማድረግ በነበረው የአቅም ውስንነት የሚፈለገውን ያክል ሊሠራ አልቻለም:: ነጻ ታዛቢዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ትብብር ያላሳየው ገዥው ፓርቲና መንግስት በዚህ ረገድ ከየአቅጣጫው የደረሰበትን ወቀሳ ለመከላከል ይረዱኛል የሚላቸውን ዘዴዎች ሁሉ ለመጠቀም ሙከራ አድርጓል:: አንደኛው ዘዴ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እያስመሰለ በከፈታቸውና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የራሱን ጥቅም እንዲያራምዱ ያቋቋማቸውን ድርጅቶች በነፃ ታዛቢነት ስም አሠማርቶ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ ተካሂዷል የሚል የፈጠራ ሪፖርት እያዘጋጀ ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲያሰራጩ ማድረግ ነው::

ጥቂት ወጣቶችና ሴቶች የፓርቲ አባላቱን አሰባስቦ በአዲሰ አበባ ከተማ ያቋቋማቸውንና የወጣትና የሴት ዴሞክራሲ ድርጅት የሚላቸውን በነፃ ታዛቢነት ስም አሠማርቶ የምርጫውን ሂደት የሲቪል ማኅበራት እንደታዘቡት ለማስስመሰል ሞክሯል:: ይሁን እንጂ በሲቪል ማኅበርና በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ስም ምርጫውን ለመታዘብ ከተሠማሩት የአገር ውስጥ ታዛቢዎች መካከል ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባዔ (ኢሰመጉ) በስተቀር ከገዥው ፓርቲ ተፅዕኖ ነፃ የሆኑ ስላልነበሩ የሚገባ አስተዋጽኦ አላደረጉም:: በአዋጅ ቁጥር 111/1987 አንቀጽ 23 በሕግ እውቅና ያላቸው የፖለቲካ ድርጀቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተወካዮቻቸው አማካይነት የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ እንደሚችሉ የተደነገገ ቢሆንም ተግባር ላይ ሲውል ከፍተኛ ችግር ታይቷል:: በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች በየምርጫ ጣቢያው የሚመድቧቸውን ታዛቢዎች ሕግ ከሚያቀደው ሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ በምርጫ ጣቢያ ተገኝተው እንዳይታዘቡ ይከለክላሉ:: የምርጫውን ሂደት አውከዋል የሚል የፈጠራ ክስ እየተፈለገ ከመታዘብ ሥራቸው እንዲታገዱ ይደረጋል:: ዛቻና ማስፈራራት ይፈፀምባቸዋል:: በአጠቃላይ ነፃና ወገንተኛ ያልሆኑ የውስጥና የውጭ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት እንዲታዘቡ ስለማይፈለግ በመታዘብ ሂደት ጠቃሚ ነገር ማግኘት አልተቻለም::

በኢትዮጵያ ምርጫ ሂደት የሚታዩት የአፈፃፀምና የአሠራር ችግሮች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ አይተናል:: በጽሑፍ ዘርዝሮ ለመጨረስ የማይቻሉና ብዙ ያልተጠቀሱ ችግሮች አሉ:: ዋናው ነገር እነዚህ የአፈፃፀምና የአሠራር ችግሮች በዋናነት የሚመነጩት በአገሪቱ ውስጥ የሚገኘው አገዛዝ ከፈጠራቸው መዋቅራዊና የምርጫ ሥርዓት ባህርይ መሆኑን መገንዘብያስፈልጋል:: የምርጫ አፈፃፀምን በተመለከተ የቱንም ያህል ጥሩ የሚል የምርጫ ህግ ቢወጣ እንኳ የከተማ ቤቶችና የገጠር መሬት በመንግስት እጅ ሆነው እስከቀጠሉ ድረስ የህዝቡ የመምረጥ ነፃነት ምንጊዜም አደጋ ውስጥ መሆኑ የማይቀር ነው::

በኢትዮጵያ የምርጫ ሂደት ያሉት ችግሮች የሚመነጩበትንና የችግሮቹን ባሕሪይ ውስብስብነት መረዳት አንድ ጉዳይ ሲሆን ከእነዚህ ችግሮች መላቀቅ የሚቻልበትን መፍትሔና አማራጭ ሃሳብ ማቅረብ ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው:: በዚህ ርዕስ የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች እንደተብራራው

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ያሉት ጠቃሚ የሆኑ የምርጫ ችግር አፈታት ልምዶች በተወሰነ ደረጃ ተዳሰዋል፡፡ አገራችን ከእነዚህ ልምዶች የምትማረውና ለራሷ ልዩ ሁኔታ እንደሚስማማ እያደረገች ልትጠቀምበት የምትችለው ብዙ ነገር እንዳለ ይታመናል፡፡ የራሳችንም የምርጫ ችግሮች መዋቅራዊ ገፅታ ያላቸው፣ ከምርጫ ሥርዓቱ ጋር የተያያዙ በአፈፃፀምና አሠራር የሚንፀባረቁ መሆናቸው ሲተነተን ጎን በጎን መፍትሔዎችና አማራጮች ምን እንደሚሆኑ መገመት በሚያስችል መንገድ ቀርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን የመፍትሔ አማራጮች እንደገና ባጭሩ በማየት በኢትዮጵያ ስላለው የምርጫ ችግር አፈታት ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

# 2.5 ለምርጫ ችግሮች መፍትሔ የሚሆኑ አማራጮች

## 2.5.1 ለውጥ የሚያስፈልጋቸው የሕግና የአደረጃጀት ጉዳዮች

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የምርጫ ችግሮች እርስ በርስ የሚደጋገፉና የተቆላለፉ መሆናቸው ቀደም ሲል በቀረቡት ገለፃዎች እንደተብራራ ሁሉ ለችግሮቹ መፍትሔ ይሆናል ተብሎ የሚቀርብ አማራጭ ለሌሎቹም ችግሮች መፈታት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ይኖራል፡፡ በሌላ አገላለፅ እንደየችግሮቹ ፀባይ የሚቀርቡት የመፍትሔ አማራጮች የተለያዩ ቢሆኑም አንዱ ሌላውን የሚቃረን ሳይሆን ይልቁንም አንደኛው የመፍትሔ አማራጭ ለሌላው ደጋፊ ስለሚሆን መፍትሔውን የተሟላ በሚያደርግ ሁኔታ የተጣጠሙ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልገው የሚቀርቡ የመፍትሔ አማራጮች ችግሩን ለጊዜው የሚያስታግሱ ብቻ ሳይሆኑ ከመሠረቱ የሚያስወግዱ መሆናቸው ላይ ነው፡፡ በእርግጥ የምርጫ ችግሮች ለሁልጊዜም እንዳይፈጠሩ ለማድረግ የሚያስችል የመፍትሔ አማራጭ ማቅረብ የማይቻል ነገር ነው፡፡ ይኸንን ማድረግ የቻለ የዴሞክራሲ ሥርዓት የለም፡፡ ነገር ግን ችግሮቹ ቢፈጠሩ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ የሚያገኙበትን አማራጮች በሕግ ሥርዓታቸው ውስጥ በግልፅ አስቀምጠው ተገቢ መፍትሔ የሚሰጡ የዴሞክራሲ ሥርዓቶች መኖራቸውን መጠራጠር አይቻልም፡፡ በእኛም አገር ማድረግ የሚቻለውና ማድረግም የሚያስፈልገው ይኸንኑ ነው፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት የምርጫ ችግሮች ሲከሰቱ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያደርግ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን የችግሩ ዋነኛ መነሻው ራሱ ሕገ-መንግሥቱ መሆኑ ቀደም ሲል የአገሪቱ የምርጫ ችግሮች ምንጭና ባሕሪይ ሲተነተን በግልፅ ተቀምጧል፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያን የምርጫ ችግሮች ለመፍታት ሲታሰብ የመጀመሪያው አማራጭ ሆኖ መቅረብ የሚገባው ሃሳብ ሕገ-መንግሥቱ ዴሞክራሲያዊ ይዘት ሊኖረው ይገባል የሚለው ነው፡፡ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መፈጠር ዋስትና የሚሆን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በኢትዮጵያ እንዲኖር ከተፈለገ ከሁሉም በፊትና ከሁሉም በበለጠ መኖር ያለበት በዴሞራሲያዊ መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ የተመሠረተ ሕገ-መንግሥት ነው፡፡ ይህ በሌለበት ሁኔታ ስለዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ኢዴፓ የሚታገልለት ቀዳሚ ዓላማም በአገሪቱ ዴሞራሲያዊ ሕገ-መንግሥት እንዲኖርና በዚህ ሕገ-መንግሥት መሠረት ከዜጎች ነፃ ምርጫና ውሳኔ ሥልጣኑ የሚመነጭ ዴሞራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ ነው፡፡

ስለዚህ የመጀመሪያው አማራጭ መፍትሔ አሁን ያለውና ለዴሞክራሲ መርሆዎች ተፃራሪ በሆኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶች የተሞላው ሕገ-መንግሥት ይዘቱ ተቀይሮ በዴሞክራሲ እሴቶች መተካት አለበት የሚለው ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱን በዴሞክራሲያዊ መርሆዎችና እሴቶች ላይ እንዲመሠረት ማድረግ ማለት በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ካለው ፖለቲካዊ አወቃቀር ለሚመነጩት፣ ከምርጫ ሥርዓቱ ጋር ተያይዘው ለሚከሰቱትም ሆነ በአፈፃፀምና አሠራር ረገድ ለሚንፀባረቁት የምርጫ ችግሮች መሠረታዊ መፍትሔ ማስቀመጥ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በዘለቄታው ከምርጫ ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያደርግ ቋሚ መሠረት መገንባት ማለት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መመሥረት የሚያገለግል ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ ከተፈለገ ለብዙሃን ፓርቲ ሥርዓት የሚያመች ፖለቲካዊ አደረጃጀት መፈጠሩን በማያሻማ መንገድ የሚያስቀምጥ ሕገ-መንግሥት መኖር አለበት፡፡ አሁን ያለው ሕገ-መንግሥት

የብዙሃን ፓርቲ መኖርን ተቀብሎ ነገር ግን በመንግሥት ሥልጣን አካላት መካከል ሚዛናዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዳይኖር በማድረጉ እዚያው በዚያው የሰጠውን ነፃነት መልሶ የሚቀማ ስለሆነ በነፃ የሕዝብ ምርጫና ውሳኔ የሚመሠረት ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል አይደለም። ሕገ-መንግሥቱ በሕግ-አውጭው፣ ሕግ-አስፈፃሚውና ሕግ-ተርጓሚው መካከል ሚዛናዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖርና አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበት የግንኙነት ሥርዓት በመፍጠር ፋንታ ሥልጣን በአስፈፃሚው እጅ እንዲያውም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥር ተጠቃሎ እንዲገባ በመፍቀዱ ትርጉም ያለው የብዙሃን ፓርቲ ተሳትፎ እንዲኖር የሚያስችል አይደለም። ይልቁንም የመንግሥት ሥልጣን መመሥረት የቻለ ፓርቲ የአስፈፃሚውን አካል ለራሱ የበላይነትና ገናናነት በሚጠቅም ነገር ግን ሌሎችን ፓርቲዎች ለመጉዳት በሚረዳው መንገድ እንዲገለገልበት የሚያደርግ ነው። ሕገ-መንግሥቱ በተለያዩ የመንግሥት ሥልጣን አካላት መካከል ሚዛናዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖርና አሁን ያለው ወደአንድ ወገን ያደላ ግንኙነት እንዲቀየር በሚያስችል ይዘት ከተቀረፀ ትርጉም ባለው ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን የብዙሃን ፓርቲ ሥርዓት ይኖራል። ዜጎች አመለካከታቸውንና ጥቅማቸውን እንደሚወክል ለሚተማመኑበት ፓርቲ በነፃነት የድምፅ ድጋፋቸውን ለመስጠት መብት ይኖራቸዋል። በዜጎች ነፃ ምርጫ ሕጋዊ የሕዝብ ውክልና ያገኘ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት በአገሪቱ ይመሠረታል። የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚበቅለውና አድጎ ለፍሬ የሚበቃው በዚህ ዓይነት መንገድ ከተዘራ ብቻ ነው።

አሁን በሥራ ላይ ያለው ሕገ-መንግሥት የመንግሥት ሥልጣን በአስፈፃሚው ሥር በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ውስጥ ተጠቃሎ እንዲገባ መፍቀዱ ያስከተለው ሌላው ችግር የአገሪቱ ምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ሊቋቋምና ሊሠራ እንዲችል ያለማድረጉ እንደሆነ ቀደም ሲል ተገልጿል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲኖር ከተፈለገ የተሻለው የመፍትሔ አማራጭ የምርጫ ቦርዱና አስፈፃሚ አካላቱ በመንግሥት አስፈፃሚው አካል ሙሉ ተፅዕኖ ሥር ከወደቁበት አደረጃጀት እንዲላቀቁ ማድረግ ነው። በብሔራዊና ከዚያም በታች ባሉት የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ውስጥ ያለው የሰው ኃይል የመንግሥት ሲቪል አስተዳደር በሚፈቅደው ሥርዓት መሠረት ከሚቀጠሩት ሞያተኞችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በስተቀር ሌላው ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከሲቪክ ተቋሞች፣ ከታዋቂ ግለሰቦችና ገለልተኛ አቋም ካላቸው ሌሎች አካላት የተውጣጣ መሆን አለበት። በዚህ መንገድ ለአንድ ብቸኛ ፓርቲ የማይወግን የምርጫ ተቋም በአገሪቱ ካልተፈጠረ የመንግሥት ሥልጣን የሚመሠርት ፓርቲ ባርኔጣውን እየቀያየረ ሲፈልግ መንግሥት፣ ሲፈልግ ፓርቲ፣ ሲፈልግ የምርጫ ቦርድ፣ ሲፈልግ ደግሞ የምርጫ አስፈፃሚ በመሆን ሥልጣኑን ሲያራዝም ይኖራል እንጂ ነፃ ምርጫና በዚህ ላይ ተመሥርቶ የሚገነባ የዴሞክራሲ መንግሥት መፍጠር አይቻልም።

በተመሳሳይ መንገድ ከመንግሥት አስፈፃሚው አካል ሙሉ ተፅዕኖ ነፃ የሆነ የምርጫ ክልል ኮሚሽን ማቋቋም ጠቃሚ ነው። የመንግሥት ሥልጣን መመሥረት የቻለ ፓርቲ በምርጫ ክልል አወሳሰን ረገድ ለራሱ አሸናፊነት ብቻ የሚጠቅመውና ሌሎችን ለመጉዳት የሚያስችለው የአከላለል ቴክኒክ እንዳይጠቀም ወይም «ጀሪ ማንደሪንግ» እንዳይፈጽም ለአንድ ፓርቲ ብቻ የማያገለግል ተቋም መፍጠር ያስፈልጋል። በብዙዎቹ የዴሞክራሲ ሥርዓቶች ይኸ ተቋም ትኩረት የሚሰጠውና የምርጫ ችግሮች ማስወገጃ አንድ ዘዴ ተደርጎ የሚሰራበት ነው፡ በእኛ አገር ሁኔታ የምርጫ ክልል ለመወሰን የሚያስችል ጥናት እንዲያቀርብ ሥልጣን የተሰጠው ለምርጫ ቦርዱ ቢሆንም የምርጫ ሥራ ሠፊና ውስብስብ እንደመሆኑ ከሌሎች ኃላፊነቶቹ ጋር ደርቦ ለመሥራት አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ሁለቱም ራሳቸውን ችለው በነፃነት እንዲደራጁና የምርጫውን ተግባር በብቃት እንዲወጡ ማድረግ የተሻለው አማራጭ ነው። እዚህ ላይ እስካሁን ድረስ በአንድ ተቋም ይሠራ የነበረውን ስራ ሁለት ተቋሞች እንዲሠሩት የሚቀርብ አማራጭ ሀብትን (ሪሶርስን) በቁጠባ ከመጠቀም አኳያ ተገቢነት የለውም የሚል ክርክር ሊያስነሳ ይችላል። ከመጀመሪያ ደረጃ እስካሁን ሲሠራ የነበረው የምርጫ ሥራ በዴሞክራሲያዊ ይዘቱም ይሁን በሪሶርስ ቆጣቢነቱ የሚመሰገንና እንደጥሩ ማነፃፀሪያ የሚቀርብ አይደለም። ተቋሙ የምርጫ ቦርድ የሚል ስም የተሰጠውና መዋቅሩን ከላይ እስከታች ዘርግቶ እንዲሠራ የተደረገው ምርጫን የሚያስፈጽም ራሱን ችሎ የሚሠራ ነፃ አካል የተፈጠረ በማመሰል በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ከየአቅጣጫው የሚቀርብበትን የሕጋዊነት ጥያቄና ተቃውሞ ለመከላከል ነው።
ከዚህ ሌላ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ስም ከውጭ መንግሥታትና ድርጅቶች ብድርና ዕርዳታ ለማግኘት ሲባል ነው። ይህ ተቋም በራሱ ነፃ ሆኖ የተደራጀና የሚሠራ ባለመሆኑ ሥልጣን ላይ ካለው ፓርቲ ትዕዛዝና መመሪያ ውጪ የሚሠራው አንዳች ፋይዳ ያለው ነገር የለም።

እንዲያውም በአገር ስም ለምርጫ ማስፈጸሚያ እየተባለ የሚመደብ በጀት፣ ከውጭ የሚገኝ ብድርና እርዳታ ለአንድ ፓርቲ አጀንዳ ማስፈፀሚያ እንዲውል በማድረግ ከፍተኛ ብክነት የሚፈፀምበት ተቋም ነው ማለት ይቻላል፡፡ እስካሁን ድረስ የምርጫ ክልልን የሚመለከት ጥናት እያቀረቡ የማስወሰኑን ተግባር ከሌሎች የምርጫው ሥራዎች ጋር ደርቦ የምርጫ ቦርዱ እንዲያከናውን የተደረገው ሥልጣን ከያዘው ፓርቲ ውጭ ላሉት ፓርቲዎች ጥቅምና ጉዳት የሚጨነቅበት ሁኔታ ስላልነበረ ነው፡፡ ምክንያቱም የምርጫ ክልልን የማጥናት ሥራ ከባድ የሚሆነው የብዙ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን ጥቅም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለማስጠበቅ የሚያስችል ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ የአንድን ፓርቲ ትዕዛዝ ብቻ ተቀብሎ አንዲት ነጥብ እንኳ ሳትዛነፍ እንዲያስፈጽም ለተቋቋመ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም የሁሉንም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ፍላጎት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚያስጠብቅ የምርጫ ክልል እንዲኖር ለማድረግ መጨነቅ አስፈላጊ ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ ነፃ የምርጫ ክልል ኮሚሽን ማቋቋም ሲባል ዋናው ነገር ትልቅ መዋቅር በመላ አገሪቱ መዘርጋት ማለት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የምርጫ ክልልን ለማጥናት ጥቂት የካርታ ሥራና የሥነ ሕዝብ ባለሞያዎቾን የሥራ ጥራትና ቅልጥፍናን የሚያረጋግጡ ዘመናዊ የቴክኒክ መሣሪያዎችንና ለአንድ ፓርቲ ብቻ ወገንተኝነት የሌለው አመራር የሚገኝበት ተቋም መፍጠር ማለት ነው፡፡ ለምርጫ ክልል ጥናት ራሱን የቻለ ባለቤት ስለተፈጠረ ሌሎች የመንግሥትና የሕዝብ አካላት በዚህ ረገድ ምንም አስተዋፅኦ አያደርጉም ማለት አይደለም፡፡ መረጃ በመስጠት፣ ሁለገብ ትብብርና ድጋፍ በማድረግ ልዩ ልዩ የመንግሥትና የሕዝብ አካላት ከሚሰጡት አገልገሎት በተጨማሪ የምርጫ ኮሚሽኑ ጥናት የሚወሰነው በፌዴራሉ ሕግ-አውጪ አካል ነው፡፡ ከምርጫ ቦርዱ ጋር ደግሞ የሚደጋገፉባቸው መስኮች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉት ዘዴዎች የሥራ ቅንጅት እንዲፈጠር በማድረግ ለዚህ ተቋም የሚያስፈልገውን ሀብት (ሪሶርስ) መጠን አነስተኛ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ ወገንተኛ ባልሆነ የምርጫ ክልል ጥናት ላይ የተመሠረተና ወገንተኛ ባለሆነ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋም የሚካሄድ ምርጫ ሲኖር በአገሪቱ ውስጥ ነፃ ምርጫ በማድረግ ዴሞራሲያዊ መንግሥት ለመመሥረት ይቻላል፡፡

ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑትና አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕገ-መንግሥት በአስፈፃሚው የመንግሥት አካል ሙሉ ተጽዕኖ ሥር እንዲወድቁ ከተደረጉት ተቋሞች መካከል የፍትሕ ሥርዓቱ አንዱ ነው፡፡ የፍትሕ ሥርዓቱ ነፃ የዳኝነት አካል እንዲሆንና ሕግ በመተርጎምም ረገድ ሠፋ ያለ ሚና እንዲጫወት በሕግ አስፈፃሚው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን የተደረገበት ሁኔታ መቀየር ይኖርበታል፡፡ ሕጉ «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» በሚባል የአንድ ፓርቲ ርዕዮተ-ዓለም የተቃኘ መሆኑ ቀርቶ የዜጎችን መብት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲያስከብርና የሕግ የበላይነትን በማስጠበቅ በመላ አገሪቱ ፍትሕን እንዲያሰፍን በሚያስችለው መርህ ላይ ተመሥርቶ መዘጋጀት አለበት፡፡ በዳኝነት ሥራ የሚመደቡ ሰዎች የሕግ ሞያና ሥነ-ምግባር ያላቸው እንዲሆኑ መደረግ አለበት፡፡ በእውቀትና በሞያ ሥነ-ምግባር እየተመዘኑ የሚመደቡበት ግልፅ አሠራር እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ በዘርና በፖለቲካ ታማኝነት ላይ ተመሥርቶ ዳኛን መምረጥና በዳኝነት ሥራ ውስጥ መመደብ የፍትህን ትርጉም የሚያጠፋ አሠራር በመሆኑ መለወጥ ይኖርበታል፡፡ አሁን በአገሪቱ ያለው የፍትሕ መዋቅርና አሠራር ነፃ ምርጫ እንዲኖር እገዛ የሚያደርግ ሳይሆን የመንግሥት ሥልጣን የያዘውን ፓርቲ ጥቅም ብቻ ለመንከባከብ የቆመ፣ ነፃነትና ገለልተተኝነት የሌለው ደካማ ተቋም ነው፡፡ ከሕግ ማሠልጠኛ ተቋማት የተመረቁ፣ ብቁ ሞያና የሥራ ልምድ ያላቸው የሕግ ሰዎች ቢኖሩም ከእነርሱ ያነሰ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በዘራቸውና በፖለቲካ ታማኝነታቸው ምክንያት የኃላፊነቱን ቦታ እንዲይዙና ከፍተኛ ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኙ ስለሚደረግ ብዙዎቹ ከዳኝነትና አቃቤ ሕግነት ሥራ እየለቀቁ ይወጣሉ፡፡ እዚያ ለመቆየት የቻሉ ጥቂት ሞያተኞች ቢኖሩም በሰበብ አስባቡ በሚደርስባቸው ጫና ብዛት አንገታቸውን ደፍተው ለመቀመጥ የተገደዱ ናቸው፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ከገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ማሠልጠኛ ተቋም (ከሲቪል ሰርቪስ) የሚወጡና የአጫጭር ጊዜ ሥልጠና የሚሰጣቸው የኮር አባላት በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ በሠፊው ተመድበው የሚሠሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በዚህም የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው ፍትሕና የሕግ የበላይነት ሳይሆን አድሎና የካድሬ ዳኝነት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የፍትህ አደረጃጀትና አሠራር ተቀይሮ እውቀትና የሞያ ሥነ-ምግባር ያላቸው፣ ከዘርና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ የሆኑ ባለሞያዎች የሚሠሩበት ነፃ የዳኝነት ተቋም መፈጠር ካልቻለ ነፃ ምርጫ ለማካሄድ ምንም መተማመኛ ዋስትና ሊኖር አይችልም፡፡ አንድ ሥልጣን የያዘ ፓርቲ በምርጫ ጊዜ የሚፈጥረውን ሕገወጥ ተግባር በሕግ ለመቋቋም የዚያ ፓርቲ ካድሬዎች በዳኝነት ተሰይመው በሚኙበት ችሎት ክስ መመሥረትና ፍትሕ መጠበቅ የማይታሰብ ነው፡ በዴሞክራሲ ሥርዓቶች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃነት

የሚጠበቀው ነፃ ሆነው በተደራጁና በሚሠሩ የፍትሕ ተቋሞች ነው በአሜሪካ የሚካሄድ ምርጫ የሕግ ግድፈት ቢገኝበት ይኸንን የሚያርመው ከፓርላማውና ከፕሬዚዳንቱ ሙሉ ተፅዕኖ ነፃ የሆነው የአገሪቱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፈረንሳይና በጀርመን ከምርጫ ጋር በተያያዘ ሁኔታ እንዲህ ዓይነት ችግር ቢከሰት የሕገ-መንግሥት ጉባዔ የሚባሉትና በነፃነት የሚሠሩት ከፍተኛ የፍትሕ ተቋሞች ፈጥነው ሕጋዊ ውሳኔ ይሰጡበታል፡፡ በኢትዮጵያም የሕግ አስፈፃሚውን ኮቴ እየተከተለ ሳይሆን በሕግ እየተመራ የሚሠራ ነፃና ለአንድ ፓርቲ የማይወግን የፍትሕ ሥርዓት መደራጀት አለበት፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ ለማካሄድ ከፍተኛ ችግር ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንደኛው የመከላከያ፣ የፖሊስና ደህንነት ተቋሞች በአብዛኛው በአንድ ፓርቲ ካድሬዎችና አባላት የተዋቀሩና የሚመሩ መሆናቸው ነው፡፡ አንድ ፓርቲ ሥልጣን በኃይል ለመያዝ ባካሄደው የትጥቅ ትግል ራሱ መልምሎ፣ አሠልጥኖና አስታጥቆ ያሰለፋቸውን ወይንም በጦርነት ምርኮኛ ያደረጋቸውን ታጣቂዎች የአገር መከላከያ መሪዎችና አባሎች እንዲሆኑ ማድረጉ ለሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት፣ ለጠቅላላው ሕዝብና አገር ደህንነት በታማኝነት የሚቆም የመከላከያ ተቋም የሚፈጠርበትን ዕድል ዘግቶታል፡፡ የፖሊስና የደህንነት ተቋሞችም የዜጎችን ሰላምና ደህንነት በእኩል ደረጃ ለመጠበቅና ለሕግ ታማኝ ሆነው ለመሥራት የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ አብዛኞቹ የእነዚህ ተቋሞች አባላት በተለይም አመራሩ ላይ ከታች እስከ ላይ የተሰገሰጉት የአንድ ፓርቲ ሰዎች ናቸው፡፡ አነዚህ በመከላከያ፣ በፖሊስና ደህንነት ተቋሞች ውስጥ በብዛት የተሰገሰጉት የአንድ ፓርቲ አባላት «ሕይወት ገብረንና የሰው ደም አፍስሰን በጠመንጃ የያዝነውን ሥልጣን በምርጫ ሰበብ አሳልፈን መስጠት አይገባንም» ብለው የሚያምኑና በነፃ ምርጫ ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ያላቸው ናቸው፡፡ ወደ እነዚህ ተቋሞች በየጊዜው የሚገባ አዲስ ኃይል ነፃ ምርጫን መከልከል የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች መንጠቅ መሆኑን እንደሚገነዘብ ቢታወቅም በአመራሩ ቦታ ላይ የመቀመጥ ዕድል ስለሌለው በወታደራዊ ሥምሪትና ግዳጅ አፈፃፀም ረገድ ውሳኔ ሊሰጥ አይችልም፡፡ በዚህም የተነሳ እነዚህ ለሕገ-መንግሥት ታማኝ መሆንና ለአገር ሰላምና ለዜጎች ደህንነት ዘብ መቆም የሚባቸው ተቋሞች የአንድ ፓርቲ ሕልውና ማስጠበቂያ መሣሪያዎች ሆነዋል፡፡

ምርጫ በመጣ ቁጥር የታጠቁትን መሣሪያ በዜጎች አናት ላይ እየደገኑ የፓርቲያቸውን ሥልጣን ይጠብቃሉ፡፡ እነዚህ ተቋሞች ከፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ ሆነው የሚደራጁበትና የሚሠሩበት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ካልተፈጠረ በነፃ ምርጫና በሕዝብ ውሳኔ የመንግሥት ሥልጣን ዝውውር ይመጣል ብሎ መጠበቅ አይቻልም፡፡ በመከለካያ፣ ፖሊስና ደህንነት ስብጥር ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት ይገባል፡፡ የማዕረግ እድገት፣ ሹመትና ሽልማት በችሎታ በአገልግሎትና በግዳጅ አፈፃፀም ብቃት ላይ ብቻ መመሥረት አለበት፡፡ የዘርና የፖለቲካ ታማኝነትን መሠረት በማድረግ እድገት፣ ሹመትና ሽልማት መስጠት መዘዙ ተቋሞቹ በነፃ ምርጫ ላይ ገለልተኛ እንዳይሆኑ በማድረግ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በአገር ሕልውናና ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ነው፡፡ የእነዚህ ተቋሞች አመራር ከአንድ ፓርቲ እጅ እንዲወጣ የሚያደርግ ሕገ-መንግሥታዊ መተማመኛ መፍጠር፣ አደረጃጀታቸውን መለወጥና ማኅበራዊ ጥንቅራቸውን እንደገና መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ይኸንን ማድረግ ከተቻለ በነፃ ምርጫ ሰበብ ዜጎችን የሚያፍንና የሚጨፈጭፍ የአንድ ፓርቲ ሎሌ ሳይሆን ዜጎችን በእኩልነት የሚያይ፣ መብታቸውን የሚያከብር፣ ለሕገ-መንግሥት ታማኝ የሆነ፣ ለአገርና ለሕዝብ ሰላምና ደህንነት አስተማማኝ ዘብ ሆኖ መቆም የሚችል የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት ተቋም ይፈጠራል፡፡ እንዲህ ዓይነት ተቋም ሲሆን ደግሞ የዜጎችን ነፃ ውሳኔ ለመጋፋት የሚቃጣ አምባገነን ሥርዓት ይጠፋል፡፡ በምትኩ የሥልጣን ምንጩ ኃይል ሳይሆን የዜጎች ነፃ ምርጫ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይመሠረታል፡፡

## 2.5.2 የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም

የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን በሕዝብ ሃብት የሚተዳደሩ የሕዝብ ንብረት እንደመሆናቸው አንድ ሥልጣን የያዘ ፓርቲ በብቸኝነት ሊመራቸው፣ ሊቆጣጠራቸውና ሊገለገልባቸው አይገባም፡፡ የሕዝቡ ዐይንና ጆሮ ሆነው መሥራት እንዲችሉ በመገናኛ ብዙሃን አመራር፣ ቁጥጥርና አሠራር ሕዝቡ ተሣትፎ የሚያደርግበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

ሕዝቡ ከአንድ ፓርቲና መንግሥት የሚመነጭ ሃሳብና አስተያየት ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ፓርቲዎች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች የሚመጡ ልዩ ልዩ አመለካቶችን በመገናኛ ብዙሃን ማድመጥ ይፈልጋል፡፡ ከተለያዩ ምንጮች የሚቀዱ ዜናዎችና መረጃዎችን ማግኘት መብቱ ነው፡፡ ዕውነት

ከአንድ ወገን ብቻ የሚገኝ ባለመሆኑ ከተለያዩ ምንጮች ሚዛናዊ መረጃዎችን እየሰበሰቡ ለሕዝቡ ማሳወቅ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን ግዴታ ነው። ሕዝቡ ሚዛናዊ መረጃ የማግኘት መብቱንና የመገናኛ ብዙሃን ደግሞ ይኸንኑ ሚዛናዊ መረጃ ለሕዝቡ የማሰራጨት ግዴታቸውን እንዲወጡ በአደረጃጀታቸውና አሠራራቸው ሕዝቡ ሙሉ ተሣትፎ ማድረግ መቻል አለበት። ሕዝቡ ለእነዚህ ተቋሞች ሕልውና የሚያገለግል መዋጮና ግብር የመክፈል ግዴታ ብቻ ሳይሆን የመረጃ ምንጭ በመሆን፣ በአመራር ተሣትፎ በማድረግ፣ አሠራራቸውን በመቆጣጠር፣ በመተቸትና በማረም ሠፊ አስተዋፅኦ የማድረግ መብት አለው። ሕዝቡ ይኸንን መብቱን ለመጠቀም እንዲችል የመገናኛ ብዙሃኖችን የሚመሩት ቦርዶችና ልዩ ልዩ አካላት ሲዋቀሩ ከአንድ ፓርቲ አባላት በሚወከሉ ሰዎች ብቻ መሆን አይገባውም። /የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣/ የነፃ ፕሬስ ተወካዮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪል ተቋሞች የተለያዩ ሞያተኞችና ታዋቂ ዜጎች በቦርድ አባልነትና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አመራር ሥራ ውስጥ ተሣትፎ ማድረግ አለባቸው።

በብዙዎቹ የዴሞክራሲ ሥርዓቶች የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ መገልገያ እንዳይሆን የሚከላከሉበት አንዱ ዘዴ እነዚህ ተቋሞች በሚመሩት ቦርዶች ውስጥ የሕብረተሠቡን ልዩ ልዩ አመለካከት የሚወክሉ የፓለቲካና የሲቪል አካላት በአባልነት እንዲሣተፉ ማድረግ ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ አገሮች ሥልጣን የያዘ ፓርቲ የመገናኛ ብዙሃንን በሞኖፖል መጠቀም በመቻሉ የመራጩን ሕዝብ ድምፅ ለመግዛት ይጠቀምበታል በሚል ሥጋት በመንግሥት ሥር የሚገኙ ሬዲዮ ጣቢያዎች ሥርጭት ከአገራቸው ግዛት ክልል ውጭ ብቻ እንዲደመጥ የሚያደርጉበት አሠራር አለ። አንዳንዶቹ ደግሞ የመገናኛ ብዙንን አገልግሎት አሠጣጥ የሚከታተልና ጉድለቶቹን ለማረም የሚረዳ ሃሣብ የሚያቀርብ ከሕዝብ የተለያዩ ክፍሎች የተውጣጡ ተወካዮች በአባልነት የሚገኙበትና ለአንድ ፓርቲ ብቻ የማይወግን ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ያቋቁማሉ።

አንዳንድ የመንግሥት ሥልጣን የያዙ ፓርቲዎች የመራጩን ድምፅ ለመግዛት በመገናኛ ብዙሃን አጉል ተስፋ መስጠት፣ የማይፈፅሙትን ቃል መግባት፣ ተለይተው የማይታወቁ መረጃዎችንና ዜናዎችን ማሠራጨት፣ ተቀናቃኞቻቸውን ማጥላላትና የመሳሰሉ ጉድለቶችን መፈፀማቸው ከተረጋገጠ የመገናኛ ብዙሃን ተቆጣጣሪ ኮሚቴው ጉዳዮን በተለያዩ መንገዶች ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል። በተለይ ደግሞ ለብዙ አመታት ሥልጣን ይዘው የሚረባ ነገር መሥራት ሳይችሉ በምርጫ ዋዜማ ለሥራ አጦች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ፣ ቤት ለሌላቸው ቤት እንደሚሠሩ፣ ለልማትና ለኢንቨስትመንት ልዩ ድጋፍና ጠንካራ የብድር አገልግሎት እንደሚሰጡ፣ የጡረታ አበል እንደሚጨምሩ፣ ለሠራተኛው የደሞዝ ጭማሪና ልዩ ልዩ ጥቅሞችን እንደሚያሚሉ፣ ለነጋዴው ምቹ ገበያ እንደሚፈጥሩ፣ ለአምራቹ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት እንደሚያሻሽሉ፣ ለሸማቹ የዋጋ ቅናሽ እንደሚያደርጉ፣ ወዘተ. ቃል የሚገቡ መንግሥታት ያጋጥማሉ። መገናኛ ብዙሃን እንደዚህ ዓይነት መናኛ ፕሮፓጋንዳ እንዳይካሄድባቸውና መራጩ ሕዝብ ነፃ ውሣኔ ለማድረግ ያለውን አቋም የሚጐዳ ዜና እንዳይሠራጭባቸው ኮሚቴው ጥብቅ ክትትል ያደርጋል። በመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች የተለያዩ የሕዝብ አመለካከቶችን የሚወክሉ ግለሰቦችና ፓርቲዎች አድሎና ልዩነት ሳይደረግባቸው በዕኩልነትና በነፃነት ሊገለገሉባቸው መቻላቸውን ኮሚቴው ይከታተላል። በኢትዮጵያም ሥልጣን ላይ ያለው ፓርቲ በመንግሥትና በራሱ የግል ሚዲያዎች የመራጩን ሕዝብ ድምፅ ለመግዛት የማይሰጠው ተስፋና የማያሰራጨው ፕሮፓጋንዳ የለም። ዜጐች ለ12 ዓመታት ከአስከፊ ድህነት መውጣት የሚችሉበት መፍትሔ ባለማግኘታቸው በርሃብ በሚያልቁበትና የዓለም-አቀፍ ዕርዳታ እየተሠፈረላቸው በሚኖሩባት አገር ስለኤኮኖሚ ዕድገት፣ ስለኑሮ መሻሻልና ስለምርት መትረፍረፍ በመገናኛ ብዙሃን ጧት ማታ መግለጫ ይሠጣል። በደርግ ጊዜ የተጠኑ፣ ግንባታቸው በጅምር ላይ የነበሩና እንደውም አንዳንዶቹ ተጠናቀው በልዩ ልዩ ምክንያት ሥራ ሳይጀምሩ የነበሩትን ፕሮጀክቶች በምርጫ ዋዜማ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት እያዘጋጁ ድምፅ የሚገዙበት ሁኔታ ታይቷል። ለራስ አገዝ፣ ለሴፍቲኔት፣ ለሥልጠና ወዘተ. እየተባለ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በምርጫ ዋዜማ የሚለቀቅበት ሁኔታ በሚገባ ታይቷል። ይኸንን ድምፅ የመግዛት ፕሮጀክት የፕሮፓጋንዳ ሽፋን እንዲያገኝ በልዩ ዝግጅት የሚደግፉት የመገናኛ ብዙሃን ናቸው። የተቃዋሚ ድርጅቶች ደግሞ ገንዘብ ከፍለው ማስታወቂያ ለማስነገር እንኳ የሚቸገሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ይኸንን አድልዎ ከመገናኛ ብዙሃን አገልሎት መስጫ ተቋሞች ለማስወገድ የመገናኛ ብዙሃን ቁጥጥር ኮሚቴ ማቋቋም ያስፈልጋል።

የዚህን ኮሚቴ ነፃነት ለመጠበቅ የአባላቱ ጥንቅር ከተለያዩ የሕብረተሠቡ ክፍሎች፣ የሲሺል ተቋሞችና ባለሞያዎች የተውጣጣ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል። ኮሚቴው የመንግስት መገናኛ ብዙሃንን ብቻ ሳይሆን የግል ፕሬስን ጭምር የሚከታተል ነው። የመንግሥትም ሆነ የግል

መገናኛ ብዙሃን ሕዝቡን የማገልገል ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና በእነዚህ ዘርፎች የተሠማሩ ሞያተኞችም የሞያውን ሥነምግባር ጠብቀው እንዲሠሩ ኮሚቴው ትልቅ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል:: በመገናኛ ብዙሃን ለትርፍ የሚሠራ ንግድ ቢኖርም የተቃዋሚውን መብትና ነፃነት የማይጋፋ መሆኑን መከታተልም የኮሚቴው ኃላፊነት ነው:: የግል ፕሬስ የሞያውን ሥነ-ምግባር በተከተለና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መሥራቱን መንግሥትና ሌሎች አካላት ሕዝቡ ያለውን የማወቅ መብት አክብረው ለነፃው ፕሬስ መረጃ በመስጠትም ሆነ የሥራ ትብብር በማድረግ ግዴታቸውን መወጣታቸውን መከታተል ሌላው የኮሚቴው ሥራ ነው:: በዚህ መንገድ መገናኛ ብዙሃን ለአንድ ፓርቲ ብቻ የማይወግኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት ከተቻለ መራጩ ሕዝብ ትክክለኛውን ነገር ለማወቅና በድምጹ ትክክለኛ ውሣኔ ለመወሠን ይችላል:: ከዚህም በተጨማሪ ተቃዋሚዎች በመንግስት መገናኛ ብዙሃን የመጠቀም እኩል እድል ሊመቻችላቸው ይገባል:: የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በመንግስት ብቸኛ ቁጥጥር ስር መሆናቸው በአስቸኳይ ተገትቶ የግል ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ስራ የሚጀምሩበት ሁኔታ በፍጥነት መመቻቸት አለበት::

## 2.5.3 የሲቪክ ትምህርትን ማስፋፋት

በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲኖር ከሚያስፈልጉት ነገሮች መካከል የሲቪክ ትምህርት አንደኛውና ዋነኛው ነው:: የሲቪክ ትምህርት በምርጫ ዋዜማ በመገናኛ ብዙሃን፣ በሲምፖዚየም፣ በፖለቲካ ድርጅቶች የክርክር መድረኮች፣ በስብሰባ አዳራሽ፣ በአደባባይ መግለጫዎች በሚደረግ ጥረት ብቻ የተወሠነ አይደለም:: በሥርዓት-ትምህርቱ ውስጥ መታቀፍ ከሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል የሲቪክ ትምህርት አንዱ ሲሆን ዓላማው የትምህርቱ ተቀባዩች ሁኔታና የትምህርቱ አሠጣጥ ዘዴዎች በሚገባ ተቀርፀው፣ የማስተማር ሥራ የሚያከናውኑት ሰዎች ተገቢ ሥልጠና አግኝተውና ብቁ የማስተማሪያ ቁሣቁሶች ተሟልተው ተከታታይነት ባለው ሥርዓት መሠጠት የሚገባው ትምህርት ነው:: በዚህ ትምህርት አማካይነት ዜጐች መብትና ግዴታቸውን እየተማሩና በዴሞክራሲ አስተሳሰብ እየተኮተኮቱ ሲያድጉ ነፃ ምርጫ ያለውን ፋይዳ በሚገባ ስለሚገነዘቡ የማንም ግፊትና ጉትጐታ ሳያስፈልጋቸው ወይም በጊዜያዊ ክስተቶችና በተለያዩ ተጽዕኖዎች ሳይሸነፉ የቅርብና የሩቅ ጊዜ ጥቅማቸውን እያመዛዘኑ የሚፈልጉትን በነፃ ውሣኔ ለመምረጥ ይችላሉ:: በትምህርት ቤት ውስጥ የሲቪክ ትምህርት እያገኘ የሚወጣው ትውልድ በሚኖርበትና በሚሠራበት ማኅበረሰብ ውስጥ በልዩ ልዩ መንገድ አስተሳሰቡ እንዲሠርፅ የማድረግ ሚና ስለሚኖረው ጠቅላላ የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ ግንዛቤና ተሳትፎ እንዲያድግ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ነፃ ምርጫና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚኖረውም ዜጐች ቢሲቪክ ትምህርት እየተደገፉ ስለ መብትና ግዴታቸው የተሟላ ዕውቀት ሲጨብጡ ነው::

የሲቪክ ትምህርት በትምህርት ቤቶች ብቻ ተወስኖ እንዳይቀርና ሠፊ አድማስ እንዲሸፍን ማድረግ ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: የመገናኛ ብዙሃን፣ የምርጫ ተቋሞች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ፣ ድርጅቶችና ልዩ ልዩ ሕዝባዊ መድረኮች የሲቪክ ትምህርት ሽፍን እንዲሰፋ ከሚያስችሉ መንገዶች ጥቂቶቹ ናቸው:: በኢትጵያ ውስጥ ሥርዓተ ትምህርቱ ያንድ ፓርቲ ርዕዮተ-ዓለም ቅጂ የመሆን አደጋ ስላጋጠመው የሲቪክ ትምህርት ፕሮግራም ለመዘርጋት የመጀመሪያው ቀዳሚ ተግባር የሥርዓተ ትምህርቱ ይዘት ከአንድ ቡድን ጠባብ ሁኔታ የሚላቀቅበትን መፍትሄ መፈለግ ነው:: በዕውቀትና በአካል ብቁ የሆነ፣ ነፃ አመለካከትና የፈጠራ ችሎታ ያለው፣ ለሰው ልጅ መብት የሚቆረቆር፣ ለአገሩ ፍቅር ያለው፣ ለመልካም ታሪኩና ባሕሉ ከበሬታ የሚሰጥ ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓተ ትምህርት መኖር አለበት:: የአገሪቱ ሥርዓተ-ትምህርት ከአንድ ቡድን ርዕዮተ-ዓለም ጋር በተሳሰረ መንገድ እስከተቀረጸ ድረስ ዓላማው ጠባብ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ተልዕኮውም ውስን መሆኑ ስለማይቀር ለሁሉም ዜጐች የሚያገለግልና አገርንም በአጠቃላይ የሚጠቅም ሊሆን አይችልም::

የዚህ ዓይነቱ ሥርዓተ ትምህርት የሚጠቅመው ለተወሠነ የፓለቲካ ቡድን ብቻ ከመሆኑም በተጨማሪ የዚህ ቡድን ርዕዩተ-ዓለም ተቀባይነት ሲያጣ የሥርዓተ-ትምህርቱም አስፈላጊነት አብሮ ያበቃለታል:: ከሁኔታዎች ጋር ራሱን እያስማማና እየታደሰ የሚሄድ ሳይሆን የፓርቲዎች ሥልጣን በተቀያየረ ቁጥር የሚለዋወጥ ሥርዓተ-ትምህርት ለራሱም ሆነ ለአገሩ የሚጠቅም ዜጋ ሊያስገኝ አይችልም:: በዚህ ዓይነቱ ሥርዓተ-ትምርት ላይ የተመሠረተ የሲቪክ ትምህርት እየሰጡ የዴሞክራሲ አስተሳሰብ ያለው ዜጋ መፍጠርና ትውልድ ማነጽ አይታሠብም:: ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠጥ የሲቪክ ትምህርት ተከታታይ በሆነና ዘለቄታ ባለው መንገድ እንዲከናወን ሥርዓተ ትምህርቱን ለአንድ የፖለቲካ ቡድን አጀንዳ ማስፈፀሚያ ከሆነበት ጠባብ

ይዘት አላቆ ትወልድንና አገርን በዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ ለመገንባት በሚያስችል ሠፊ ራዕይና ዓላማ ላይ በተመሠረተ ይዘት መቅረፅ ያስፈልጋል:: በሥርዓተ ትምህርት ዝገጅትና ምርምር ሥራ የተሠለፉትን ተቋሞች ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ተፅዕኖ ነፃ አድርጐ ማደራጀት፣ የሞያተኛና የቴክኒክ አቅማቸውን ማሟላት፣ የፋይናንስ ምንጫቸውን ማስፋትና አሠራራቸውን ሁሉ ዘመናዊ ማድረግ የሥርዓተ-ትምህርቱ አዘገጃጀት ጥራት፣ በይዘቱ ሙሉነትና በዓላማው ስፋት ላይ የሚኖራቸው አስተዋጾ ከፍተኛ መሆኑ ለእነዚህ ጉዳዩች ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው:: እነዚህን መሠረታዊ ሁኔታዎች በማሟላት ዜጐችን በሲቪክ ትምህርት መኮትኮት ለነፃ ምርጫና በዚህ ላይ ተመሥርቶ ለሚገነባ የዴሞክራሲ ሥርዓት መፈጠር ወሣኝ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው መገንዘብ አስፈላጊ ነው:: የነፃ ምርጫና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች በምርጫ ዋዜማ ተጀምረው ከምርጫ ውድድር መጠናቀቅ በኋላ የሚቆሙ የአንድ ሰሞን ሥራዎች አይደሉም:: ወይንም ዘላቂነትና ተከታታይነት በሌለው መንገድ ተጀምረው የሚቋጩ የዘመቻ ሥራዎች አይደሉም:: ጥልቀት ባለው ምርምርና ጥናት ሠፊ ራዕይና የተሟላ ይዘት ባለው ሥርዓተ ትምህርት ላይ በሚመሠረት ተከታታይ የሲቪክ ትምህርት እየታገዙ በተቀናጀ የዜጐች ነፃ ተሣትፎና በሂደት የሚሳኩ ናቸው:: ስለዚህ ለነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሲታሠብ የዜጐችን የተሟላ ንቁ ተሣትፎ ስለሚፈጥረው የሲቪክ ትምህረት ከፍተኛ ትኩረት ሠጥቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው::

አሁን በሥራ ላይ በሚገኘው ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የኢትዮጵያ የምርጫ ሥርዓት ከተወዳዳሪዎች መካከል የተሻለ ድምጽ ያገኘ አንድ ሰው አላፊ የሚሆንበት የአብላጫ ድምጽ ስርዓት መሆኑን በማስረጃ የተደገፈ ማብራሪያ በማቅረብ ለማሣየት ተሞክሯል:: ይኸኛው የምርጫ ሥርዓት ካልተቀየረ በስተቀር በአገሪቱ ነፃ ምርጫ ለማድረግም ሆነ ሰፊ መሰረት ያለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት አስቸጋሪ እንደሚሆን ግልፅ በሆነ መንገድ ቀርቧል:: ከዚሁ የምርጫ ሥርዓት ጋር በተያያዘ አሁን ያሉት ዕውነታዎችና ወደፊትም ሊፈጠሩ የሚችሉት አደጋዎች በበቂ ማስረጃዎች ቀደም ብለው ተተንትነዋል:: የችግሩን ሥፋትና ጥልቀት መረዳት አንድ ጠቃሚ ነገር ቢሆንም ወሣኙ ጉዳይ አማራጭ የሚሆኑ የመፍትሔ ነጥቦችን ማቅረብና ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥልት ማመላከት ነው:: በዚህ ሠነድ ውስጥ በሌላ ራሱን በቻለ ርዕስ እንደተገለፀው፣ ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሚጠቅመው ዝርዝር ተመጣጣኝ ውክልና የሚባለው አማራጭ እንደሆነ ይታመናል::

ተመጣጣኝ ውክልና የምርጫ ሥርዓት በሁሉም መመዘኛዎች ተቀባይነት ያለው ተመጣጣኝ ውክልና በሚገባ የሚነፀባረቅባቸው ምክር ቤቶችን በየደረጃው ለማቋቋም ከሚሰጠው ጥቅም ሌላ አንድ ዓይነት የምርጫ ሥርዓት በመላ አገሪቱና በየትኛውም ደረጃ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል:: ለፌደራል ምክር ቤት አንድ ዓይነት ሥርዓት፣ ለክልል ምክር ቤቶችና ለወረዳ ምክር ቤቶች ደግሞ ሌላ ዓይነት የምርጫ ሥርዓት በመጠቀም የሚከሰተውን የሀብት (የሪሶርስ) መባከንና የአሠራር መዘበራረቅ ያስወግዳል::

## 2.5.4 ማጠቃለያ

እስከአሁን ድረስ ለማብራራት የተሞከረው ከመርህና ከአደረጃጀት ጋር ለተያያዙ የአገሪቱ የምርጫ ችግሮች መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው ስለሚታመንባቸው አማራጮች ነው:: ከዚህ በኋላ ለማየት የሚሞከረው ደግሞ የዚሁ የመርህና የአደረጃጀት ችግር አንድ ገፅታ ሆኖ ስለሚታየው የምርጫ ሥርዓት ችግር ነው::

እስከ አሁን ድረስ የአገራችን ምርጫ ችግሮች ከሆኑት የመርህ፣ አደረጃጀትና የምርጫ ሥርዓት ጉድለቶች መዳን የሚቻልባቸው ዋና ዋና የመፊትሔ አማራጮች ቀርበዋል:: አሁን የሚቀርበው በአፈፃፀምና አሰራር ከሚንፀባረቁት ችግሮች መውጣት የሚቻልበት መፍትሕ ምንድን ነው የሚለው ነጥብ ነው:: በዚህ ነጥብ ላይ እስካሁን ከቀረቡት የመፍትሔ አማራጮች የበለጠ ዋጋ ያለውና ክብደት የሚሰጠው ነገር ማስቀመጥ አይቻልም:: ምክንያቱም በአፈፃፀምና አሠራር የሚታዩ ጉድለቶች መዋቅራዊ ከሆኑትና ከምርጫ ሥርዓቱ ባሕሪይ የሚመነጩ ችግሮች ነፀብራቅ እንጅ ከዚህ ውጭ የተፈጠሩ ባለመሆናቸው ነው::
በምርጫ አስፈፃሚነት አሁን የተሠማሩት ኃይሎች የዕውቀትና የልምድ ችግር ጉልቶ እንደሚታይባቸው ተገልጿል:: ነገር ግን አሁን በሥራ ላይ ባለው የምርጫ ተቋም አወቃቀርና የምርጫ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ይኸንን ጉድለት በማስተካከል ብቻ ነፃና ዴሞክራሲያው

ምርጫ በአገሪቱ ማምጣት አይቻልም፡፡ አሁን ባለው ሕግ ሥር ያሉትን አስፈፃሚ አካላት ዘመናዊ አሠራር እንዲኖራቸው በቴክኖሎጂ፣ በፋይናንስ፣ በሥልጠና አስፈላጊው ድጋፍ ሁሉ ቢሟላ እንኳ አንድን ፓርቲ ከማገልገል በላይ ከሀገሪቱ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መኖር የሚሠጡት አስተዋፅዖ የለም፡፡ አወቃቀሩና መርሁ የአንድ ገናና ፓርቲ የበላይነት እንዲኖሮ የሚያስችል ሆኖ ስለተቀረፀ አስፈጻሚ መስሪያ ቤቱን በኮምፒዩተር፣ በሠለጠነ የሰው ኃይልና በፋይናንስ በመደገፍ ወይንም ብዙ ዓይነት መመሪያዎችንና ደንቦችን በማውጣት ብቻ ነፃ ምርጫ ለማካሄድ የሚያገለግል ዴሞክራሲያዊ ተቋም ማድረግ አይቻልም፡፡

በምርጫው ሂደት ከምርጫ አስፈፃሚው መሥሪያ ቤት በተጨማሪ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ተቋማት ማለትም ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ፣ መገናኛ ብዙሃን ታዛቢዎችና ሌሎች የሲቪል ማህበረሰብ ተቋሞች የፈለገውን ያህል ሥራቸውን አቀናጅተው እንዲያካሄዱ ቢደረግ የአወቃቀር መርሁና የምርጫ ሥርዓቱ ካልተቀየረ በስተቀር ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በአገሪቱ እንዲኖር ማድረግ አይቻላቸውም፡፡ በመርህ ደረጃ በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጡት አደረጃጀቶችና የምርጫ ሥርዓት ዘይቤዎች ሳይለወጡ በድምፅ አሰጣጥ፣ በመራጩ ሕዝብ ነፃ ተሣትፎ፣ በድምጽ ቆጠራ፣ በመረጃ አመዘጋገብ፣ በምርጫ ጉድለቶች አፈታትና በመሳሰሉት የሚከሠቱ ችግሮችን ግልፅ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ በማስወገድ ብቻ የሕግ የበላይነት የሚከበርበትን አሠራር ለማስፈን አይቻልም፡፡ የዴሞክራሲያዊና ፍትሐዊ በሆነ አደረጃጀትና የምርጫ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ እንደነዚህ ዓይነቶቹ የአሠራር የአፈፃፀም ጉድለቶች ሲያጋጥሙ ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሔ በመስጠት ሁኔታዎችን ማሻሻል ይቻላል፡፡ በማንኛውም መልክ የሚፈጠሩ የአፈፃፀም ጉድለቶቹን እያረሙ ይበልጥ ውጤታማና ብቁ የሆነ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ ይቻላል፡፡ የአፈፃፀም ጉድለቶች ከአጠቃላዩ መርህና አደረጃጀት ጋር የተያያዙ በሚሆኑበት ጊዜ ግን የቅደሚያ ቅድሚያ ትኩረት ማድረግ የሚገባው ምንጩን ከመሠረቱ ለማድረቅ መሆን ይገባዋል፡፡

በመጨረሻ ይህ ሁሉ ችግር ተወግዶ የተዘረዘሩት የመፍትሔ አማራጮች በተግባር እንዲውሉ የሚቻልበት መንገድ ምን እንደሆነ በማመላከት ይኸንን ርዕስ ማጠቃለል ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ነጥብ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችል የተመቻቸ ሁኔታ አለመኖሩን ካለጥርጣሬ መረዳት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የመንግሥት ሥርዓት በአገሪቱ ውስጥ አለመኖሩን ማወቅ የመጀመሪያው አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት የሚኖረው ነፃና ፍትሓዊ በሆነ ውድድር የመራጩን ሕዝብ ውክልና ያገኘ መንግሥት ሲቋቋም ብቻ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የመራጩን ሕዝብ ፈቃድ ያላገኘ የመንግሥት ሥርዓት በምንም ተአምር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው የመንግሥት ሥርዓት ሊሆን አይችልም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሂዶ ስለማያውቅ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እንዳለ ለማመን የሚያበቃ መነሻ ፈፅሞ ማግኘት አይቻልም፡፡ አሁን ሥልጣን ላይ የተቀመጠው የአገዛዝ ሥርዓት ነው፡፡ በመጀመሪያ በጠመንጃ ኃይል ወደ ሥልጣን የተንጠባጠለና ከዚያ በኋላ ደግሞ በአንድ በኩል ሰላማዊ ተቃውሞን በኃይል እያፈነ በሌላ በኩል ደግሞ የምርጫ ቲያትር እየሠራ ራሱን በግድ የሾመ የፖሊስ መንግሥት ነው፡፡ የራሱን ፕሮግራም የአገርና የሕዝብ መተዳደሪያ ሕገ-መንግሥት አድርጐ በሕዝብ ላይ በግድ የጫነና በዚህ «ሕገ-መንግሥት» ሽፋን የራሱን የፖለቲካ አጀንዳ በግድ ለማስፈፀም የሚንቀሳቀስ ሕገ-መንግሥታዊ አምባገነን ሥርዓት ነው፡፡ ይኸንን በግልፅ መረዳት በመፍትሔ አፈላለጉ ጥረት የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው አሁን ላለው ችግር መፍትሔ መምጣት ያለበት በሰላማዊ መንገድ በሚካሄድ ትግል መሆን እንዳለበት መረዳት ነው፡፡ አምባገነናዊ አገዛዝ በሰላማዊ ትግል ሊሸነፍ እንደማይችል አድርጐ መገንዘብ ስህተት መሆኑን ማመን ያስፈልጋል፡፡ ሰላማዊ ትግል አሸናፊ መሆን እንዲችል ዋናው ነገር ትግሉ የተደራጀ፣ ቅንጅትና ተከታታይነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የጐደለው ነገር ደግሞ ይኸኛው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት በአገሪቱ ውስጥ እንደሌለ ከሞላ ጐደል መግባባት መኖሩ ባይካድም ከዚህ መገላገል በሚቻልበት መፍትሔ ረገድ ሠፊ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ከልዩነቶቹ መካከል በሰላማዊ ትግል አስፈላጊነትና አሸናፊነት ላይ ያለው ጥርጣሬና ሥጋት አንዱ ነው፡፡ የሰላማዊ ትግል ሲባል አደባባይ ወጥቶ መፈክር በማሰማት ወይንም በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮና በጋዜጣ መግለጫ በማውጣት ብቻ የተወሠነ ነገር አድርገው የሚገምቱ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከዚህ የተሳሳተ ግምገማ በመነሳት እስከአፍንጫው የታጠቀ ሠራዊት እያዘዘ በመላ አገሪቱ

የቁጥጥርና የአፈና መረቡን የዘረጋ አገዛዝ በመግለጫና በመፈክር ከሥልጣን የሚወድቅበት መንገድ አልከሰትላቸው ይልና በሰላማዊ የትግል ዘዴ አሸናፊነት ላይ ዕምነት ማሳደር ይሳናቸዋል:: የሰላማዊ ትግል ሲባል ግን በአደባባይና በአዳራሽ ስብሰባ ከመፎከር በላይ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ መግለጫ ከማውጣት ባሻገር አልፎ የሚሄድ ሠፊና ብርቱ ጥረት የሚጠይቅ ሥራ ነው::

የሕዝቡን ችግሮች በጥልቀት ማወቅ፣ የችግሮቹን ባሕሪይ እንደክብደታቸው መጠን መረዳትና ከችግሮቹ ይዘት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የመፍተሔ አቅጣጫዎች መቀየስ ይጠይቃል:: እነዚህን የችግር መፍቻ መንገዶች የችግሩ ባለቤት የሆነው ሕዝብ በጥልቀት እንዲያውቃቸውና እንዲጨብጣቸው ማድረግ ያስፈልጋል:: የችግሩ ገፈት ቀማሽ የሆነው ሕዝብ በጥልቀት ያወቃቸውንና የተረዳቸውን የመፍትሔ አማራጮች እያንዳንዱ በተናጠል ሳይሆን በጋራና በሕብረት እንዲፈጽማቸው በሚያስችል ዘዴ ማደራጀት ይገባል:: በተደራጀ የሕዝብ ኃይል ለተጨባጩ ሁኔታ የሚመጥኑ ልዩ ልዩ ሰላማዊ የትግል ሥልቶችን መቀየስያስፈልጋል:: ሁኔታው በሚጠይቀው ደረጃ እነዚህን የተለያዩ ሥልቶች በተናጠልና በቅንጅት መጠቀም ያስፈልጋል:: ትግሉ ሥፋት እያገኘና የማያቋርጥ ዕድገት እያሣየ እንዲሄድ የሚያስችል በቂ አመራር መስጠት ይገባል:: ድርጅቱ፣ አመራሩና የትግል ሥልቱ ተጣጥመው ተከታታይ የሆነ ሰላማዊ የሕዝብ ትግል እንዲኖር ማድረግ አለባቸው:: እንዲህ ዓይነት ሠፊ፣ የተደራጀና ብቁ በሆነ አመራር  የሚታገዝ ሰላማዊ የሕዝብ ትግል እንኳንስ ማኅበራዊ መሠረት የሌለውን አምባገነን ሥርዓት ቀርቶ ጥልቅ በሆነ ተፈጥሯዊ መሠረት ላይ የቆመ ተራራንም ቢሆን ቀስ በቀስ ለመሸርሸርና ለመናድ የሚችል ነው:: እንዲህ ዓይነት ሠፊና የተደራጀ ሰላማዊ ትግል አምባገነናዊ ሥርዓቱ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ ከሚመራው ሠራዊት በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እየደለለ በየመስኩ ካሠማራቸው ጀሌዎቹ ቀስ በቀስ መነጠል የሚችል ነው:: በቤቶች መካከል የቆመን አንድ ዛፍ ለመቁረጥ በቅድሚያ ቅጠሉንና ቅርንጫፎቹን ማንሣት፣ ቋሚውን እየከፋፈሉ መቀነስና በመጨረሻም ወደሥሩ ተጠግቶ በመቁረጥ ከባድ ጉዳት በማያስከትል መንገድ መጣል እንደሚቻል ሁሉ በሠፊው ሰላማዊ የሕዝብ ትግል በመሣሪያ ድጋፍ የቆመን አምባገነን አገዛዝ ቀስ በቀስ ከታጣቂ ኃይሉም ጭምር በመነጠል ካለደጋፊ እንዲቀርና እንደገና መነሣት በማይችልበት አኳኋን መጣል ይችላል:: ምሳሌው ግዑዝ የሆነን የማይንፈራገጥና አፀፋ የማይሰጥን ዛፍ በአልሞትባይ ተጋዳይነት ብዙ መከላከልና ጥፋት ሊደርግ ከሚችል አምባገነን ስርዓት ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይነት እንዳለ በማሰብ የቀረበ ሳይሆን አንድን የማይፈለግ ነገር ለማስወገድ የሚደረግ ጥንቃቄ የራሱ ደረጃዎችና በቅደም ተከተል የሚፈፀሙ የአደጋ መቀነሻ ዘዴዎች እንዳሉት ቀላል በሆነ ማሳያ ለማስረዳት ይጠቅም ይሆናል በሚል የቀረበ ነው::

ሰላማዊ ትግል ሠፊና ከባድ ጥረት የሚጠይቅ፣ ተከታታይነት ባለው መንገድ የሚካሄድና በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ዕድገትና ለውጥ ማሣየት የሚገባው መሆን እንዳለበት መግባባት ካለ ቀጣዩ ጉዳይ ሰላማዊ የሕዝብ ትግል እንመራለን በሚሉት የፓለቲካ ኃይሎች መካከል የትግል ትብብር መፍጠር ነው:: የትግል ትብብር ሲባለ በባሕሪይው፣ በደረጃውና በዓላማው የተለያየ ቢሆንም በዚህ ርዕስ ትኩረት መስጠት የተፈለገው በነፃ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት መፍጠር በሚቻልበት ቁምነገር ላይ ስለሆነ ለዚህ ዓላማ መሣካት የሚጠቅመውን ትብብር በሚመለከት ነው:: ተደጋግሞ እንደተብራራው የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ሥርዓት አነስተኛ ቁጥር ባላቸው መራጮች ድጋፍ የሚመሠረት መንግሥት እንዲኖርና የአብዛኛዎቹ መራጮች ድምፅ ዋጋ  እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው:: ይህ ዓይነቱ ችግር ከሚከሠትባቸው ሁኔታዎች መካከል አንደኛው በፓርቲዎች መካከል ጠንካራ ትብብር በሌለበት ሁኔታ፣ መራጩ ለተለያዩ ፓርቲዎች የሚሠጠው ድጋፍ የድምፅ መበታተንን የሚያስከትል መሆኑ ነው::

በ1992 ዓ.ም በተካሄደው የፌደራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ አዲስ አበባ ውስጥ የተፈጠረው ክስተት ለዚህ አባባል ጥሩ ማስረጃ ነው:: ገዥው ፓርቲ የአዲስ አበባን መራጮች አብዛኛ ድጋፍ አላገኘም:: አብዛኛው መራጭ የድጋፍ ድምፁን የሰጠው በምርጫው ውድድር ለተሣተፉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነው:: ነገር በብዙ የማጭበርበርና የአፈና ስልት ታግዞም ቢሆን አሸናፊ መሆን የቻለው አነስተኛ የመራጮች ድጋፍ ያገኘው ገዥው ፓርቲ ሲሆን የተሸነፉት ደግሞ የአብዛኛውን መራጭ ድምፅ ያገኙት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ናቸው:: ለዚህ ዋነኛ ው ምክንያት የመራጩ ሕዝብ ድምጽ ለተለያዩ ተቃዋሚዎች በመበታተኑ ነው:: በዚህም የተነሣ

አብዛኛው የአዲሰ አበባ መራጭ የፓርላማ ውክልና ሳያገኝ ባልመረጣቸው ሰዎች ለመገዛት ተገዷል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል መልክ ባለው ደረጃ ቅንጅት ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ አብዛኛ ው የአዲስ አበባ መራጭ የፓርላማ ውክልና ለማግኘት ይችል ነበር። በአደስ አበባ የአብዛኛው መራጭ ውክልና በፓርላማ ውስጥ ተረጋግጦ ቢሆን ኖሮ ደግሞ ድሉ ለፓርቲዎቹና ለአዲስ አበባ መራጮች ብቻ አልነበረም። በመላ አገሪቱ በሰላማዊ መንገድ በሚካሄድ የሕዝብ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ለመመሥረት ለተጀመረው ትግልና በዚህ ዓይነቱ የትግል ሥልት ውጤት ይመጣል ብሎ ተስፋ ላደረገው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ፋና ወጊ የሚታይ ድል ይሆን ነበር። ለአዲስ አበባ መራጮች ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ ለሚገኙ መራጮች መነቃቃትን የሚፈጥር አደፋፋሪ ድል መሆን ይችል ነበር ነገር ግን እንደተገለፀው የመራጩ ሕዝብ ድምፅ በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በመበታተኑና ፈርጀ ብዙ ማጭበርበሮች በመፈፀማቸው ድል ማድረግ የማይገባው ገዥ ፓርቲ ባለድል ለመሆን በቅቷል።

ከዚህ የሚቀሰም ጠቃሚ ልምድ እንዳለ ማመን አስፈላጊ ነው። ለመጪዎቹ የምርጫ ጊዜያት ተመሳሳይ ስህተት ላለመድገም ተቃዋሚዎች ትርጉም ያለው ትብብር ማድረግ ይኖርባቸዋል። ድጋፍ የሚሠጣቸው መራጭ የሰጠው ድምፅ ውክልና ማስገኘት በማይችልበት ሁኔታ እየተበተነ ዋጋ የሚያጣ ከሆነ ተቃዋሚዎችን ለመምረጥ የሚያደፋፍረው በቂ ምክንያት ይጠፋል። ተስፋ በመቁረጥ ከተሣትፎ ራሱን ወደማራቅ ያመራል። ፓርቲዎቹም ገዥውን ፓርቲ ለማሸነፍ የሚያስችል የድምፅ ድጋፍ ማግኘት ቀርቶ በሕልውና ለመቆየት የሚያበቃቸው የሕዝብ ትብብር ቀስ በቀስ እየተመናመነ ያልቃል። የጭቆና አገዛዝ ደግሞ ካለጠንካራ ተቀናቃኝ መኖር የሚያስችለውን ጊዜ ይገዛል። ሕዝቡም መርጦ ባልወከለው ጨቋኝ አገዛዝ ሥር ወድቆ ሳይወድ በግድ እየተጨቆነ ከመኖር የተለየ ዕድል ያጣል። ስለዚህ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚፈጠር የትግል ትብብር ከአነዚህ የተሣሠሩ ችግሮች ለመውጣት የሚያስችል መፍትሔ ነው። የፖለቲካ ኃይሎች ይኸንን እንቆቅልሽ ለመፍታት ቁርጠኛ ውሣኔ ካደረጉ የሚገኘው ድል ጥቂት የፖርላማ መቀመጫዎችን በማግኘት ብቻ የተወሠነ አይደለም። የትግል ትብብር የሚያስገኘውን ጣፋጭ ፍሬ ለማጣጣም ምቹ ሁኔታ ስለሚፈጥር የመቻቻል ፖለቲካዊ ባሕል እንዲያዳብሩ ይጠቅማል። በረጅሙ ሂደት ደግሞ የገዥውን ፖርቲ ገናናነት የሚሰብር ጠንካራ የፓርላማ ውክልና ቢያገኙ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መድህን የሚሆን የጥምር መንግሥት ለመመሥረት የሚያስችል መሠረት እንዲገነቡ ይረዳል። መራጩ ሕዝብም ቢሆን የተለያዩ አመለካከቶች ተቻችለው የሚኖሩበትን የዴሞክራሲ ባሕል ከተግባር እየተማረ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ምሥረታ የሚያደርገውን ተሣትፎ እንዲያጐለብት አደፋፋሪ ሁኔታ ይፈጠርለታል። በፖለቲካ ኃይሎችና በመራጩ ሕዝብ መካከል ከፍተኛ መተማመንና የማይበጠስ ትስስር ይኖራል። በመጨረሻም ዴሞክራሲ በአገዛዝ ላይ አሸናፊ ሆኖ መውጣቱ ይረጋገጣል።

በፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚፈለገው የትግል ትብብር ከተፈጠረ ሌላው ጉዳዩ የመራጩ ሕዝብ ተሣትፎ እንዲጠናከርና ወሣኝ በሆነ ደረጃ እንዲቀናጅ ማድረግ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥትን የመሾምና የመሻር ሥልጣን የራሱ ብቻ መብት መሆኑን ሕዝቡ በሚገባ ማወቅ አለበት። ይኸንን መብቱን ባለማወቅ ወይንም እያወቀ በአግባቡ ባለመጠቀም የራሱን ድርሻ መወጣት ካልቻለ ለአገዛዝ መመቸቱ የማይቀር ነው። በላዩ ላይ የተጫነበትን ጭቆና የፈጣሪ ቁጣ አድርጐ በማሰብና «እርሱ ያመጣውን እርሱ ይመልሰው» በሚል ፈሊጥ የራሱን ኃላፊነት ሁሉ ለፈጣሪ አሳልፎ ከሰጠ አገዛዝን ከነአስከፊ ውጤቶቹ ለመሸከም እንደተስማማ የሚቆጠር ነው። ወይንም ጭቆናን የማስወገድ ኃላፊነት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ብቻ እንደሆነ አድርጐ በመገመት ከዳር ቆሞ መታዘብን ከመረጠ ከአገዛዝ ወጥመድ ለመውጣት ያለው ዕድል የመነመነ ነው። ለሕዝብ መብትና ነፃነት መረጋገጥ ከራሱ በላይ ኃላፊነት የሚወስድ እንደሌለ ማወቅ የመጀመሪያው ተፈላጊ ነጥብ ነው። ለመብቱና ለነፃነቱ መገኘት ሕዝቡ የሚያደርገው ፖለቲካዊ ተሣትፎ በሌላ ኃይል ሊሸፈን የማይችልና ምትክ የማይገኝለት መሆኑን መገንዘበ ያስፈልጋል። እንዲህ ዓይነት ንቃትና ግንዛቤ ያለው ሕዝብ የራሱን ዕድል የሚወስነው ራሱ መሆኑን ስለሚገነዘብ ጭቆናን ለመሸከም ዝግጁ አይደለም። ካለ እርሱ ፈቃድና ፍላጐት በኃይል የማፈፀምበትን ማንኛውም አይነት ጫና ላለመቀበል ይታገላል። መብቱ ሲጓደልና ነፃነቱ ሲደፈር በቸልታ የማየት ትዕግሥት አይኖረውም። አገዛዝ እንዲያበቃና የጭቆና ቀንበር እንዲሠበር በመሻት በአልገዛም ባይነት መንፈስ አሻፈረኝ ብሎ ከዳር እስከ ዳር ይንቀሳቀሳል። በፖለቲካ ድርጅት የመሰባሰብ አስፈላጊነት ጐልቶ የሚወጣው በዚህ ጊዜ ነው። የሕዝቡ አልገዛም ባይነት[6]

---

[6] ***አልገዛም ባይነት*** ***= Disobediece***

በቅንጅት ጉድለት ምክንያት ለጥቃት እንዳይጋለጥና በአገዛዝ ላይ ማሣረፍ የሚገባው ጠንካራ ተፅዕኖ እየተበታተነ እንዳይዳከም በሥርዓት የተደራጀ ፖለቲካዊ አመራር አስፈላጊነት የማይታለፍ ጥያቄ ሆኖ ይመጣል። የሕዝቡን የትግል ተሣትፎ ማሰባሰብና ወደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ እንዲረባረብ አመራር መስጠት የተደራጀ ፖለቲካዊ ኃይል ድርሻ ይሆናል። የሕዝቡ ትግል ሲበታተን ገዥዎች አንዱን ዓይነት እንቅስቃሴ ከሌላው ለመለየትና የትግል ትስስር ሳይፈጠር እየነጠሉ ተራ በተራ ለመምታት ዕድል ስለሚያገኙ እንዲህ ዓይነቱ ክፍተት እንዳዚጋ ሥልት ማውጣትና አቀናጅቶ መምራት የፖለቲካ ድርጅቶች ኃላፊነት ነው።

በሌላ መንገድ ሊተካ የማይችለው የሕዝብ ፖለቲካዊ ተሣትፎና በቅንጅት ጉድለት የሕዝቡ ትግል እየተበተነ በቀላሉ እንዳይመታ የሚያስችል ብቁ አመራር መስጠት ያለባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች አንድ ሆነው ከተሠለፉ አገዛዝ እንደሚሸነፍ መጠራጠር አይገባም። እንዲህ ዓይነቱ የትግል ቅንብር በምርጫ ሂደት ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲሸጋገር ማድረግ ይቻላል። እያንዳንዱ ዜጋ በምርጫ ተወዳዳሪነት፣ በምርጫ ታዛቢነትና በመራጭነት የሚሰጠው አንድ ድምጽ አገዛዝን ለመጣል ትልቅ ዋጋ እንዳለው አምኖ በምርጫ ጊዜ ተሣትፎ ከማድረግ የማይቆጠብ ከሆነ ለሕዝብ ትግል አሸናፊነት እንደሚደረግ ትልቅ አስተዋፅዖ የሚቆጠር ነው። ሕዝቡ ለዴሞክራሲ ኃይሎች የድጋፍ ድምፁን መስጠት ብቻ ሣይሆን በዴሞክራሲ ስም መብቱንና ነፃነቱን ለነጠቁት አምባገነኖች ደግሞ ድምፁን መንፈግ ከቻለ በእርግጥም የሕዝብ ትግል አሸናፊነት እንደማይቀር መተማመን ይቻላል። በዚህ መንገድ ከሕዝብ የሚገኘው የድጋፍ ድምፅ እየተበታተነ አምባገነኖች በምርጫ ስም የሕዝቡን ሥልጣን እንደነጠቁት እንዳይቀሩ ከተፈለገ ደግሞ የሕዝብ ትግል እንመራለን የሚሉ የፓለቲካ ኃይሎች የየራሳቸው ፓርቲ በብቃት ከማጠናከር በተጨማሪ ቅንጅት መፍጠር ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ በምርጫ ሂደት የአመባገነኖች የበላይነት የማይሠበርበት ምክንያት ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ምርጫን እንደብቸኛ የትግል መሣሪያ ሳይሆን እንደ አንድ ጠቃሚ የትግል መስክ በመውሰድ በዚህ መስክ ለዴሞክራሲ መፈጠር የሚረዳ ቁም ነገር ለመሥራት ከልብ መሥራት ይገባል። ከሌሎች ሠላማዊ የትግል መስኮች ጋር እያቀናጁ ምርጫን እንደ አንድ ጠቃሚ ተግባር መፈፀም ከተቻለ፣ በምርጫ ተግባር ውጤት ማግኘት የሚቻለው ደግሞ በሕዝቡና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ቅንጅት ሲኖር መሆኑ ተቀባይነት ካገኘና በፖለቲካ ኃይሎችም መካከል ትብብር መፍጠር እንደሚገባ መግባባት ላይ ከተደረሰ ምርጫን በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ የተባሉት የመርህ፣ የአደረጃጀት፣ የምርጫ ሥርዓት፣ የአሠራርና የፈፃፀም ችግሮች የማይፈቱበት ምክንያት የለም።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ነፃና ትክክለኛ የምርጫ ስርዓት እንዲኖር ከተፈለገና በተለይም በ1997 ዓ.ም በሀገራችን የሚካሄደው ብሔራዊ ምርጫ ለዴሞክራሲያዊ ሰርዓት ግንባታ ከአሁን በፊት ከተካሄዱት ምርጫዎች የተሻለ ውጤትና ትርጉም እንዲኖረው ከተፈለገ፣ ነገ የምርጫው እለት ሲቃረብ ሳይሆን ዛሬ የምርጫውን ህግ ማሻሻል፣ አዲስና ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ማቋቋም፣ ተቃዋሚዎች በመንግስት መገናኛ ብዙሃን እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እድል ማመቻቸት፣ ተቃዋሚዎች የምርጫ ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችላቸው የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግና አለምአቀፍና አገር አቀፍ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት ከመነሻው ጀምሮ የሚከታተሉበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል። ለነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ ማግኘትም ህዝቡ ሰላማዊ ትግሉን ከወዲሁ በተጠናከረ ሁኔታ ማካሄድ ይኖርበታል።